


# ታዝቤ ዝም ከምል

ደረጀ አለማየሁ (ዶ/ር)

2017 ዓ.ም.

ይህን መጽሐፍ በማንኛውም ኤሌክትሮኒክ መሣርያ
ለማስተላለፍ፣ ለማስቀመጥ፣ በፎቶ ኮፒ ወይም
በሌላ መንገድ ለማባዛት፣ ለማሳተምም ሆነ ለመተርጐም፣
የባለመብቱ ፍቃድ እንዲጠየቅ ሕግ ያስገድዳል።
© 2017 ደረጀ አለማየሁ

ሽፋን ዲዛይን እና የቴክኒክ ድጋፍ፡
ምስጢረ ተመስገን 0940609924

ISBN 9798300437497

www.Teramaj.org

Email: ghagos1969@gmail.com

ታዝቤ ዝም ከምል

# መታሰቢያነቱ

“እግረ መንገዱንም ለዚህ ግልጽ ደብዳቤ ምክንያት የሆነኝ የአቶ ሐጎስ ሽሙጥና የደርግ ጥይት ዒላማ ለነበሩት ወንድሞቼ

- ለከበደ መንገሻ
- ለዳንዔል ታደሰ
- ለምትኩ ተርፋሳ

እንደዚሁም አብሬአቸው በእስር ላይ እያለሁ መንግስቱ ኃይለማርያም ካሰረን ከሁለት ዓመት በኋላ በአንድ ላይ ወስዶ ለገደላቸው ወንድሞቼ

- ለኃይሌ ፊዳ
- ለደስታ ታደሰ
- ለኃይሉ ገርባባ

ለውድ እህቶቼ

- ንግስት አዳነ
- ቆንጂት ከበደ

መታሰቢያ ይሁንልኝ።”

## ማውጫ                                    ገጽ


መግቢያ ...................................................................................5

መቅድም .................................................................................12

ታዝቤ ዝም ከምል.......................................................................15

A Diktat or a Perspective for a Democratic Discourse........133




# መግቢያ

የዶ/ር ደረጀ አለማየሁ ሁለት መጣጥፎች ("ታዝቤ ዝም ከምል" እና "A Diktat or a Perspective for a Democratic Discourse") ከተጻፉ ከ30 ዓመት በላይ ሆናቸው። "ታዝቤ ዝም ከምል" በግል በየሰዉ እጅ በተወሰነ ደረጃ ከመሠራጨቱ ሌላ በወቅቱ አሜሪካን አገር ይታተም የነበረው Ethiopian Review[1] መጽሔት ላይ በተከታታይ ወጥቷል። የእንግሊዘኛ ጽሁፉም ልክ እንደ አማርኛው በየሰዉ እጅ በመጠኑ ከተሰራጨ በኋላ በዚሁ መጽሄት ላይ ለንባብ በቅቷል። በወቅቱ፣ የመጽሔቱ አዘጋጅ ሁለቱም ጽሁፎች ላይ መጠነኛ አርትኦታዊ መሻሻል አድርጎባቸዋል። የእንግሊዘኛው ጽሁፍ ዶ/ር ደረጀ መጀመሪያ በሰጠው ስያሜ ሳይሆን "Genuine Power-Sharing Can Bring Us Closer to Democracy"[2] በሚል ርዕስ ለአንባቢያን ቀርቧል።

እነዚህ ሁለት መጣጥፎች ከወጡ ረጅም ጊዜ ቢሆንም ዛሬም በተለያዩ መድረኮች የመወያያ አጀንዳ ናቸው። በሬዲዮ ፕሮግራሞች ከአንዴም ሁለት ጊዜ ቀርበው ለአድማጮች ተነበዋል። በተለያዩ ድረ-ገጾች ላይም

1. ደረጀ አለማየሁ (ዶ/ር) (1994, July) ታዝቤ ዝም ከምል፣ Ethiopian Review, Volume 4, Number 7-11

2. Dereje Alemayehu (Dr.) (1995) Genuine Power - Sharing Can Bring Us Closer to Democracy, Ethiopian Review, Volume 5 Number 1&2

በጽሁፍና በንባብ መልክ ቀርበዋል። እነዚህ ጽሁፎች ውስጥ የሰፈሩት ሃሳቦች አሁን ኢትዮጵያ ስላለችበት ሁኔታና የወደፊት እጣ ፈንታዋን በተመለከተ ለሚነሱ ጥያቄዎችና በተያያዥም ለሚደረጉ ውይይቶች ፋይዳነት አላቸው ብለን እናምናለን። ቀደም ሲል ስለእነዚህን ጽሁፎች ሰምተው የማንበብ እድል ያላገኙ ወገኖቻችን ጽሁፎቹ የት ሊገኙ እንደሚችሉ በየጊዜው ይጠይቃሉ። ያነበቡትም እንደገና ጽሁፎቹን መልሰው ለመጎብኘት ይፈልጋሉ። በዚህ ምክንያት ነው እኛ የቅርብ ጓደኞቹ ፕሮፌሰር ጴጥሮስ ቶጃ፣ ሞገስ ከበደ እና አስተዋይ መርዕድ ሁለቱን ጽሁፎች በአንድነት በመጽሐፍ መልክ አዘጋጅተን ለማውጣት የተነሳነው።

አንባቢዎች የበለጠ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ይረዳቸዋል ብለን በማሰብ የግርጌ ማስታወሻዎች ጨምረናል። በእንግሊዘኛ ጽሁፉ ላይ አንዳንድ ግልጽ ያልሆኑ አረፍተ ነገሮችና አባባሎችን አሻሽለናል። ከእነዚህ ማሻሻያዎች ውጪ፣ ፊደል ግድፈቶችን ከማረም በስተቀር የይዘትና የንድፈ ሃሳብ አቀራረብ ለውጥ ሊያስከትል የሚችል ምንም እርማት ወይንም ክለሳ ከማድረግ ተቆጥበናል።

የደረጀ የመጀመሪያ ጽሁፍ መነሻ ሃጎስ የተባለ ግለሰብ የኃይሌ ፊዳን ታሪክ አጠልሽቶ "እፎይታ"[3] መጽሄት ላይ ያወጣው ምንባብ ነበር። ኃይሌን አብሬው ከመታሰሬ በፊት በመጠኑ፣ ደርግ ጽ/ቤትና አራተኛ ክ/ጦር ታስረን በነበረ ጊዜ ደግሞ በቅርበት አውቀዋለሁ። የኃይሌን ጥልቅ እውቀት፣ ቅንነትና ደግነት በሚገባ ስለማውቅ፣ ሃጎስ በጥላቻ መንፈስ ለሰነዘራቸው አልባሌና ተራ ክሶች ደረጀ የሰጠው መልስ አንጀቴን እንዳራሰው መሸሸግ አልችልም። ኃይሌ በግፍ ከተገደለ ከስንት

3. እፎይታ - 1ኛ አመት ቁጥር 1 የካቲት 1984





አመት በኋላ፣ የደርግ መርማሪዎች እያሰቃዩ የተቀበሉትን ቃሉንና፣ የመንደር አሉባልታን ጨማምሮ ለጻፈው ለጊዜው ጉልበተኛ ሃጎስ፣ ደረጀ የሰጠው ምላሽ ተገቢ ነበር። በትክክልም ደረጀ እንዳለው "ለቆየ ባላጋራ የታሪክ ፍትህ የሚነፍግ.... ፍትህ አያመጣም። ያለፈን ታሪክ በጥላቻ የሚያጨማልቅ የዛሬን ታሪክ በደም ከማጨማለቅ አይመለስም። ያለፈን ታሪክ ጠምዝዞ መስክርልኝ የሚል፥ ዛሬ የሕዝብን እጅ ጠምዝዞ "ምረጡኝ" ከማለት አይመለስም"።

የዶ/ር ደረጀ ጽሁፍ የኃይሌ ፊዳን ማንነትና ስብዕና ለአንባቢያን በማካፈል አይቆምም። በዚሁ ጽኁፉ የኢትዮጵያ ጊዜያዊ ሁኔታና ፖለቲካ ላይ ያለውን አስተያየት በሰፊው ያቀርብልናል። በተለይም በሃይል ወይም በጉልበት (እሱ ካላሺን ይለዋል) የኢትዮጵያን ሰላምና አንድነት ማምጣት እንደማይቻል በሚተነትነው ጽሁፉ ታሪክንና የራሱንም ተመክሮ እያካፈለን፣ ዴሞክራሲያዊ ስርዓትን በቅንነት መቀበልና በስራ ላይ ማዋል እንደሚያዋጣ ያስገነዝበናል። ዴሞክራሲን ለጊዜያዊ ድል ሳይሆን ለዘላቂ ሰላምና አንድነት መሠረታችን ሊሆን እንደሚገባው ያሳስበናል።

መቼም በዛሬው ዘመን በጉልበትና በማጭበርበር ሥልጣን የያዙ አብዛኞቹ አምባገነኖች ደፍረው ዴሞክራሲን አይቃወሙም። በ1960ዎቹ መጨረሻ፣ በግሪክ አገር በመፈንቅለ መንግሥት ሥልጣን ከያዙ በኋላ፣ ዴሞክራሲ የተወለደባትን አገራችውን "ለዴሞክራሲ አልበቃችም" ብለው እንደተሳለቁት የግሪክ ኮሎኔሎች ዴሞክራሲን በአደባባይ አያጥላሉም። እንዲያውም ዴሞክራሲ ለተነፈገው ሕዝብ ዴሞክራሲን ለማስፈን "ከላይ" የወረድን መሲህ ነን ነው የሚሉት። ዴሞክራሲን ይዘምራሉ፤ የዴሞክራሲን ዋና ተሟጋችና ጠባቂ ነን ብለው ራሳቸውን ይሾማሉ።

የሥልጣን ዘመናቸውም ሳይገደብ እንዲራዘም ሕገ መንግሥታቸው ውስጥ ማሻሻያ አንቀጾች ይጨምራሉ። ደራርበውም ለሕግ የበላይነት እንደሚገዙ ያበስራሉ። "ዴሞክራሲያዊ ምርጫ" ይፈቅዳሉ፣ ግን እራሳቸው የሚያዘጋጁት ምርጫ ላይ፣ የምርጫ ኮሮጆ ይሰርቃሉ። ተቃዋሚዎቻቸውን ያስፈራራሉ፣ ይከሳሉ፣ ያስራሉ፣ ይገድላሉ። ለይስሙላ ተፎካካሪ ተብሎ ከቀረበ ፓርቲ ጋር ተወዳድረው ከ99% በላይ ድምጽ አግኝተን አሸነፍን ብለው ይለፍፋሉ። ይህንን በጠራራ ፀሐይ የተፈጸመ ስርቆትን ተቃውሞ የሚወጣውን በሽበርተኝነት፣ በድሮ ስርዓት ናፋቂነት፣ በጽንፈኝነትና በመሳሰሉት ክሶች እስር ቤት ይወረውራሉ።

ለአንድ አገር ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ዘላቂነት እንዲኖረውና የፖለቲካ መረጋጋት እንዲሰምር፣ ዶ/ር ደረጀ መሠረታዊ የሚላቸውን ሁለት መርሆች ያስቀምጣል።

አንደኛው፣ ዴሞክራሲ ጉልበተኞች ሲሳካላቸው የሚቀበሉት ካልተሳካላቸው የሚያፈርሱት፣ ወይንም ተፎካካሪ ጉልበተኞች ጦር ተማዘው እርስ በእርስ የሚፋለሙበት ሳይሆን፣ ለሕዝብ ድምፅ ተገዢ የሚሆኑበት ሥርዓት መሆኑን ነው።

ሁለተኛው፣ ዴሞክራሲ ከአሸናፊዎችም በላይ የተሸናፊዎች መብት የሚከበርበት ሥርዓት እንደሆነም ጭምር ነው። ተሸናፊዎች የአሸናፊዎች ወከባና አፈና ሳይደርስባቸው፣ ለሚቀጥለው ዙር ምርጫ ለመወዳደር የሚዘጋጁበት ሁኔታዎችን የሚያረጋግጥ የፖለቲካ ሥርዓት ነው። "ዴሞክራሲ የአሸናፊዎች መፈንጫ ሳይሆን፣ የተሸናፊዎች መብት ማረጋገጫ ነው"።





መሬት ላራሹ፣ ንጉሣዊ አገዛዝ ይወገድ፤ የሴቶች፣ የሠራተኞች፣ የብሄረሰቦችና የሃይማኖት መብቶችና እኩልነት ይከበር በሚሉ መፈክሮች ስር የተደረጉ ትግሎች የዴሞክራሲና የፍትሕ ትግል አካሎች ናቸው። የኢትዮጵያ ሕዝቦች ባለፉት አመታት ያገኟቸው የማይናቁ ፖለቲካዊ ድሎች ቢኖሩም፣ አሁንም ጥያቄዎቻቸው ሙሉ ለሙሉ ምላሽ አግኝተዋል ማለት አይቻልም። የኢትዮጵያ ሕዝቦች አሁንም ለመብታቸው የሚያደርጉትን ትግል ሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ መቀጠል አለባቸው። ኢትዮጵያ ነፍጥ ያነገቡ "ጀግኖች" የሚፋለሙበት የጦር ሜዳ መሆኗ መቆም አለበት። በመሳሪያ ኃይል የሚደረግ ትግል ብዙ ወገኖቻችንን የሚያስጨርስና ወደ ዘላቂ መፍትሄ የማያደርስ በመሆኑ ሊበረታታ አይገባውም። ለዚህ ነው ደረጀ ጽሁፉን ሲያጠቃልል፣ "ሕዝቧ ጀግና ሆኖ የሚባላባት ሳትሆን፣ ፈሪ ሆኖ በልቶ የሚያድርባትን ኢትዮጵያን እንመስርት" ብሎ የሚደመድመው።

አገራችን ውስጥ በቅንነትና በግልጽ የፖለቲካ ውይይቶች ማካሄድና ልዩነቶችን ሰላማዊ በሆነ መንገድ የመፍታት ባህል፣ ለፖለቲካ ፓርቲዎችና ቡድኖች አሁንም ባዕድ ነው። ልዩነቶችን በጉልበት ሲያስተናግዱ ከነበሩ ከንጉሡ፣ ከደርግና ከኢሕአዴግ አገዛዝና ውድቀት ትምሕርት የተወሰደ አይመስልም። አሁንም ልዩነቶችን በዴሞክራሲያዊ ውይይት ሳይሆን በኃይል ለመፍታት ሙከራ ሲደረግ ይታያል። በዚህም ምክንያት፣ ከትውልድ ትውልድ ከማያባሩ ግጭቶችና ጦርነቶች እሽክርክሪት መውጣት አልቻልንም። ዛሬም የብሄረሰቦች መብት ጉዳይና በብሄረሰቦች መካከል ሊኖር ስለሚገባው ግንኙነት ተወያይቶ ለመስማማትና ሁሉንም አካታችና አስማሚ የሆነ ብሔራዊ እቅድ መንደፍ አልተቻለም።

የኢትዮጵያ አንድነት በፈቃደኝነትና በእኩልነት ላይ መመስረት እንዳለበት እሙን ነው። የአንድን ብሄረሰብ ታሪክና ባህል ታላቅነት አሳብጦ፣ የሌሎችን አጥላልቶና ንቆ አንድነትን ማምጣት አይቻልም። የአንድን ብሄረሰብ ገናናነት መቀበል የኢትዮጵያዊነት መለኪያም መሆን የለበትም። እዚያው ብሄረሰቡ ውስጥ የተወለደ ድርጅትን አዳክሞ፣ በገዢው ፓርቲ የተጠፈጠፈ ድርጀት የብሄረሰቡ ብቸኛ ተወካይ አድርጎ ማቅረብና ቅቡልነትን እንዲያገኝ ማስገደድ ፀረ ዴሞክራሲያዊና ወደ ሌላ አለመግባባትና እልቂት የሚያመራ ውሱን የፖለቲካ ታክቲክ ነው።

የእንግሊዘኛ ጽሁፉ፣ በወቅቱ (እስከዛሬም ማለት ይቻላል) ልሂቃንን ያነጋገር የነበረው የብሄረሰቦች ጥያቄ፣ የአገር ምሥረታና የኢትዮጵያ አንድነትን ጠለቅ አድርጎ ይመረምራል። የደረጀ አውደ ሃሳብ የሚያውጠነጥነው፣ ከኢትዮጵያ አንድነት በፊት በብሄረሰቦቿ መሃል ያለው ግኑኝነት የተረጋጋ፣ ሰላማዊና መግባባት ላይ የተመሠረተ እንዲሆን የሚደረገው ስራ ቅድሚያ ሊሰጠው እንደሚገባ ነው። በብሄረሰቦች መሃል በእኩልነትና በዴሞክራሲያዊ መርህ ላይ የተመሠረተ ግንኙነት መገንባት ከተቻለ፣ የአገሪቱ አንድነት በታሪካዊ ሂደት በራሱ ይመጣል። የአገር አንድነትን አስቀድመን በብሄረሰቦች መሃል ያለውን ቅራኔ ለወደፊት እንፈታዋለን ካልን፣ አንዱንም ሳናሳካ ወደ እርስ በርስ ጦርነት እናመራለን ይላል ዶ/ር ደረጀ።

የደረጀ አቀራረብ በመጠኑ ምልልስ (polemic) ይበዘዋል ሊባል ይቻላል። አንዳንድ አንባቢዎች ምልልሱ በዛ ብለው መተቸታቸው አይቀርም ብዬ እገምታለሁ። ደረጀ ራሱ ጽሁፉ ለሕዝብ ከተዳረሰ በኋላ፣ በጻፈው መግቢያ





ላይ እንዳለው "የአቶ ሐጎስ ጽሁፍ የቀሰቀሰብኝ ሀዘንና ንዴት ጋብ ስላለልኝ ስሜታዊ የሆንኩባቸውን አንዳንድ ቦታዎች ትንሽ ለዘብ ላደርግ በቻልኩ ነበር" ይላል። ከዚያም በመቀጠል ጽሁፉን እንዳለ ሳያርም እንዲወጣ የወሰነበትን ምክንያት ሲያብራራ "ከእጅ የወጣ ጽሁፍ ለአቅመ አዳም ደርሶ የራሱን ጎጆ የመሰረተ ልጅ ማለት ነው። ....... እንደገና አርሜ ልጻፍህ ብለው የልቤ ሳይሆን የአንጎሌ ውጤት፤ በሌላ አነጋገር ሌላ ጽሁፍ ይሆንብኛል ብዬ ሰጋሁ" ይለናል። ስለሆነም መጣጥፎቹ ትኩሳታቸው ሳይበርድ እንዳለ ቀርበዋል።

መጣጥፎቹ ምልልስ ይበዛባቸዋል ቢባልም፣ ደረጀ እጅግ ብዙ ርዕሶች ላይ ጥልቀት ያላቸው ሃስቦችን ስለሚሰነዝር፣ አንባቢ ከእንካ ሰላምትያው ባሻገር ያሉት ሃስቦች ላይ እንዲያተኩር አሳስባለሁ። ይልቁንስ፣ በየመሃሉ የሚያስገባቸው ኩነቶች፣ ትረካዎች (anecdotes) ምሳሌዎችና ገጠመኞቹ ጽሁፉ ይበልጥ ትርጉም እንዲኖረውና አንባቢም ሃሳቡን በቀላሉ እንዲረዳለት አስችሎታል እላለሁ።

ዶ/ር ደረጀ ጽሁፎቹ ላይ፣ በተደጋጋሚ "ይህንን ለወደፊት እመለስበታለሁ"፣ እያለ ያለፋቸው ጉዳዮች አሉ። በእርግጥም የነካካቸውን ጉዳዮች ሁሉ በአንድ ጽሑፍ ማጠቃለል የሚቻል አልነበረም። ሆኖም ግን "አብራራቸዋለሁ"፣ "እመለስባቸዋለው" ብሎ ቃል የገባልንን ጽሁፎች ሳናይ 30 ዓመታት እንደ ቀልድ እንዳለፉ ልብ ይሏል። "ምነው ዝም አልክ ጻፍ እንጂ" ብለው ከሚወተውቱት ወዳጆቹ መሃል አንዱ ብሆንም፣ ከአገር አገር የሚያንከራትተው ስራው ፋታ እንዳልሰጠው እረዳለሁ። ጡረታ ወጥቶ ጊዜ እንደልብ ሲታደለው "እመለስባቸዋለሁ" ያላቸው

ርዕሶች ላይም ሆነ ሌሎች ጉዳዮች ላይ ያሉትን አስተያየቶች አንባቢዎች የማየት እድል ይኖረን ይሆናል ብዬም ተስፋ አደርጋለሁ። ምናልባት እነዚህ ጽሁፎቹ በመጽሐፍ መልክ መውጣታቸውስ መንፈሱን አነሳስተው ያንቀላፋ ብዕሩን እንደገና ያነቃቁት ይሆን?

አስተዋይ መርዕድ

አሌክሳንድርያ፣ ቨርጂኒያ፡ አሜሪካ (2017)





# መቅድም

ይህ ግልጽ ደብዳቤ "እፎይታ" በሚባል እንደምገምተው የTPLF መጽሄት ውስጥ ኃይሌ ፊዳ በደርግ እስር ቤት በሰጠው ቃል ላይ ተመርኩዞ በተጻፈ ጽሁፍ አነሳሽነት የጻፍኩት ነው። እራሴው ጥቂት ኮፒዎች አባዝቼ ለማውቃቸው ወዶጆቼ ከላኩ በኋላ፣ ወዳጆቼ ብቻ ሳይሆኑ በይዘቱ ከሞላ ጎደል የሚስማሙ የማላውቃቸውም ሰዎች ጭምር በትነውት ከጠበቅሁት በላይ ተሰራጭቷል። የመታተም እድል ግን እስካሁን አልገጠመውም። አሳጥረውና በመጽሄታችን ላይ እናውጣልህ ያሉኝ ነበሩ በልዩ ልዩ ምክንያቶች አላመቸኝም።

አሁን ነገሩ ዓመት ከአለፈው በኋላ እንደገና የተመለስኩበት በአንድ ሊያስቅ በሚችል ምክንያት ነው። ኮምፒዩተሬ ላይ የአማርኛ ፕሮግራም አስገባሁና ፕሮግራሙንም በደንብ ለማወቅና እጄንም ለማፍታታት ጥቂት ደብዳቤዎች ጽፌ አልበቃኝ አለ። ከዚያ ለምን ያንን "በተራ ታይፕ" የተመታ ጽሁፍ ወስጄ መለማመጃ አላደርገውም አልኩና ከመተኛቴ በፊት በቀን በቀን አንድም ሁለትም ገጽ እየመታሁ ጨረስኩት። አይ እንግዲያው እንዲህ "ካማረ" የመታተም እድል ያግኝ አልኩና ላሳትመው ወሰንኩ።

አንድን ጽሁፍ ከተጻፈ ከዓመት በኋላ ሲመለሱበት ብዙ መለወጥ የሚገባቸው ነገሮች ይኖራሉ። በመጠኑም ቢሆን በኢትዮጵያ የፖለቲካ ሁኔታ ውስጥ የተለዋወጡና የዚህን ደብዳቤ ይዘት የሚመለከቱ ጉዳዮች አሉ። የመጀመሪያውን የኢትዮጵያ “ዲሞክራሲያዊ ምርጫ” TPLF[4] (The Tigray People’s Liberation Front) በOLF[5] (Oromo Liberation Front) ላይ ያገኘውን የመጀመሪያ ድል በዚህ ጽሁፌ ከሞከርኩት “ትንቢ” ጋር ለማገናዘብ እችል ነበር። የአቶ ሐጎስ ጽሁፍ የቀሰቀሰብኝ ሀዘንና ንዴት ጋብ ስላለልኝ ስሜታዊ የሆንኩባቸውን አንዳንድ ቦታዎች ትንሽ ለዘብ ላደርግ በቻልኩ ነበር። አንዳንድ ከትግራይ የሆኑ ወዳጆቼ ሳይቀሩ በጽሁፌ ውስጥ አጉልቼ ለማቅረብ የሞከርኩትን የTPLF ፍራቻዬን ወደ ትግሬ ጥላቻ እስከመመንዘር ስለሄዱ ለዚህም ማብራሪያ መጨምር በተገባኝ ነበር። አሁን ሳየው ከOLF ብቻ ሳይሆን ከሌሎቹም ፀረ TPLF የፖለቲካ ኃይሎች (መኢሶን ኢድኃቅን ጨምሮ) ያለኝን ርቀት ትንሽ ላተኩርበት በወደድኩ ነበር። ይህንን ሁሉ ሳላደርግ ግልጽ የሆኑ የታይፕ ግድፈቶች በማረም ነው የተወሰንኩት። ጽሁፉን ሳልቀይር ያቀረብኩበት ብዙ ምክንያቶች አሉኝ። አንዱም ብዙ መቶ ወዳጅና ባዳ ያነበበውን ጽሁፍ እዚህና እዚያ መለዋወጡ ትርጉም ስለሌለው ነው። ከእጅ የወጣ ጽሁፍ ለአቅመአዳም ደርሶ የራሱን ጎጆ የመሰረተ ልጅ ማለት ነው። ድሮ ቤት እያለ መምከር ነው እንጂ የሚቻል፤ የራሱን ሕይወት ከጀመረ በኋላ ና ተመለስ ማለት የማይሆን ግብ ግብ መፍጠር ነው። እንዲሁም እንደገና አርሜ ልጻፍህ ብለው

4. ህዝባዊ ወያነ ሓርነት ትግራይ (ህወሓት)

5. የኦሮሞ ነጻነት ግንባር (ኦነግ)





የልቤ ሳይሆን የአንጎሌ ውጤት፤ በሌላ አነጋገር ሌላ ጽሁፍ ይሆንብኛል ብዬ ሰጋሁ። ለሱ ለሱ ደግሞ አንባቢን ለማሰልቸት ወደፊትም እድል ስለማላጣ፤ ይህንን እንዳለ በስሜታዊነቱ መተው ይሻላል አልኩኝ።

ብዙ ወዳጆቼ አንዳንዱም የማላውቃቸው ሰዎች ጽሁፉን እንደወደዱልኝ በስልክም በደብዳቤም ገልጸውልኛል። ስለወደዱልኝ ደስ እንዳለኝ መደበቁ ውሸት ነው የሚሆን። ለሙገሳ ሲሉ መስራት ነው እንጂ መጥፎ ለተለፋበት የሥራ ውጤት ሙገሳን መቀበሉ ክፋት የለውም። ከሁሉም በላይ ግን በብዙ አካባቢዎች ይዘቱ ማከራከሩ ነው የበለጠ ደስ ያለኝ። ስጽፈውም ከዚህ የተለየ ዓላማ አልነበረኝም። በዚህ ጽሁፍም ሆነ ወደፊት ችሎታዬ እስከ ፈቀደልኝ ድረስ የምሞክረው ማከራከር ማጠራጠር ነው። ካላሳመንኩ ሞቼ እገኛለሁ የሚል ወይ ቄስ ወይ ካድሬ ነው። የመጀመሪያውን ሆኜ አላውቅም፤ ሁለተኛውን መሆን ካቆምኩ ደግሞ ቆየሁ።

ደረጀ ዓለማየሁ (በርሊን፣ ሰኔ 1985- June 1993)

ጀግና የማያስፈልጋት አገር የታደለች ነች
(በርቶልድ ብሬሽት[6])

# ታዝቤ ዝም ከምል

ይድረስ ለአቶ ሐጎስ ፃዕዳ
በካላሺን አንጋሽነት "ቅቡልነት" አገኘን ብለው አራት ኪሎ ከሚገኙት ጀግኖች አንዱ

"የኃይሌ ፊዳ መሸፈትና የመኢሶን እጣ" በሚል የፃፍከውን በቅርቡ አነበብኩኝ። ከ13 ዓመታት በፊት ካጠገቤ ተወስዶ የተገደለውን ወንድሜን ወዳጄን ባልሰራው ስትወነጅለው፣ ሳታውቀው ስትዘልፈው፣ የአሸናፊነት ትዕቢትህ አናዶኝ ሬሳውን ከመቃብር አውጥተህ በጥላቻ ካራ ስትገዘግዘው ሳይ የዋሁ፣ ቅኑ፣ ሰብዓዊው ኃይሌ ትዝ ብሎኝ አለቀስኩኝ።

በመሰረቱ ፖለቲካ ትቼ አካዳሚክ ዓለም ገብቼ መኖር ከጀመርኩ ቆየሁ። ከመናደድና ከማልቀስ ያለፈ ለኃይሌ የጓደኝነት ትዝታ ላደርግለት የምችለው እንደገና የፖለቲካ ብዕሬን ማንሳት ብቻ ነበር። ላንተ ትዕቢት ያለኝን ንቀት፤ ለአስተሳሰብህ ያለኝን ፍራቻና ጥላቻ፤ ለኃይሌ ያለኝን ፍቅርና አክብሮት በአደባባይ እንድትገልጽልኝ ይህቺን ግልፅ ደብዳቤ ልጽፍ ወሰንኩ።

6. Bertolt Brecht. (1939). Life of Galileo "Unhappy the land that has no heroes" sc. 13





ከኢትዮጵያ ፖለቲከኞች አብዛኞቻችሁ የጎበጠን ከማቃናት ይልቅ ለመስበር፣ የተለኮሰን ከማጥፋት ይልቅ ለማራገብ በምትራወጡበት ባሁኑ ወቅት፤ የሁላችሁም የትግል መንገድ አያዋጣም" ብዬ ለመጮህ ሳስብ አቅመ ቢስነት እየተሰማኝ ሆደ ባሻ አድርጎኛል። በዚህ ሆደ ባሻነቴ ላይ ነው ያንተ ጽሁፍ መጥቶ ንዴቴንና ሀዘኔን የቀሰቀሰው። እነዚህ ሁሉ ሁኔታዎች ተደማምረው ለግልጽ ደብዳቤዬ የተለየ የፖለሚክ መልክ ስለሰጡት ደብዳቤዬ የያዛቸው አንዳንድ መልእክቶች ሊሸፈኑ ይችሉ ይሆናል። በዚህ ምክንያት ግን ከሆዴ ምርር ብሎኝ የፃፍኩትን ወደአንጎሌ መልሼ ላለዝበው አልፈለግሁም። ዘባራቂ ምሁር እንጂ ታክቲከኛ ፖለቲከኛ የመሆን ፍላጎት የለኝም።

ስለሆነም "ኃይለ ቃሉን" ሰበብ ሳታደርግ ይህን ግልጽ ደብዳቤ ዲሞክራሲን ሊያስተምር በተነሳው መጽሄታችሁ ላይ ወይንም ከመንግስት ልሳንነት ወደ "ሕዝባዊ" ልሳንነት ዞረዋል ከሚባሉት ጋዜጦቻችሁ በአንደኛው ላይ አስወጣልኝ ለእናንተም ቢሆን በጀግና መንደራችሁ ያንኑ የፉከራ ቴፕ ከመደጋገም አንዳንዴም ከፈሪዎች አምባ ምን እንደሚዘፈን ማወቁ አይጎዳችሁም። እናንተ እምቢ ካላችሁ "የራሴ ልሳን" ስለሌለኝ እኔው 50 ያህል ቅጂዎች አባዝቼ "አንብቡ አስነብቡ" ብዬ እበትናታለሁ። በአገራችን ዛሬም እንደትላንቱ ሁሉ ከሺህ የብዕር ጋጋታ የአንድ ካላሺን እሩምታ የበለጠ ውጤታማ ስለሆነ በተንኩ አልበተንኩ ዋጋ የለው ይሆናል። ሳያድላት ቀርቶ ያለጀግና በማታፈራ አገራችን የአንድ ፈሪ ድምጽ ተሰማ አልተሰማ ምን ለውጥ ያመጣል? ለብሶቴ ያህል ትንሽ ከተነፈስኩ ይበቃኛል።

እግረ መንገዱንም ለዚህ ግልጽ ደብዳቤ ምክንያት የሆነኝ የአቶ ሐጎስ ሽሙጥና የደርግ ጥይት ዒላማ ለነበሩት ወንድሞቼ ለከበደ መንገሻ፤ ለዳንዔል ታደሰና ለምትኩ ተርፋሳ 15ኛ የሙት ዓመት[7]፤ እንደዚሁም አብሬአቸው በእስር ላይ እያለሁ መንግስቱ ኃይለማርያም ካሰረን ከሁለት ዓመት በኋላ በአንድ ላይ ወስዶ ለገደላቸው ወንድሞቼ ለኃይሌ ፊዳ ለደስታ ታደሰና ለኃይሉ ገርባባ፤ ለውድ እህቶቼ ለንግስት አዳነና ለቆንጂት ከበደ[8] 13ኛ የሙት ዓመት መታሰቢያ ይሁንልኝ።

7. ነሐሴ 30፣ 1969 ዓ.ም. የመኢሶን አመራር የነበሩት ዶ/ር ከበደ መንገሻና ዳንኤል ታደሰ፣ አብረዋቸው ከነበሩት ከምትኩ ተርፋሳ፣ ደንቢ ዲሳሳና ደንበል አየለ ጋር የተሸሸጉበት ቤት በደርግ ወታደሮች ሲከበብ ዶ/ር ከበደ መንገሻና ዳንኤል ታደሰ በያዙት መሳሪያ እራሳቸውን ሰዉ። የተቀሩት ሦስቱ ተታኩሰው ሞቱ።

8. የመኢሶን አመራር የነበሩት ኃይሌ ፊዳና ንግሥት አዳነ እንዲሁም ደስታ ታደሰ፣ ኃይሉ ገርባባና ቆንጂት ከበደ ሐምሌ 1971 ዓ.ም. ከ4ኛ ክፍለ ጦር ዋና መምሪያና ከከርቸሌ እስር ቤቶች ተወስደው በደርግ ትእዛዝ በግፍ ተረሸኑ።





# ክፍል አንድ

## 1. የጽሁፍህ ዓላማ

መጀመሪያ ነገር አቶ ሐጎስ ከሞተ ከ13 ዓመት በኋላ የኃይሌ ፊዳን ሬሳ እንደ አጋንንት ከመቃብር ቤት እንድትፈልግ ያደረገህ ምንድነው? በኔ ግምት ከኃይሌ ፊዳ ማንነት ጋር የተያያዙ ሁለት ምክንያቶች አሉህ። አንደኛ፣ ኃይሌ የመኢሶን አባልና ከመሪዎቹ አንዱ ነበር። መኢሶን ደግሞ (ያደረግኩት ሰፊና ወካይ መጠይቅ ባይኖርም) ካጋጠመኝና ከምሰማው ተነስቼ እንደምገምተው በብዙ የአዲስ አበባ ንዑስ ከበርቴ በተለይም በወጣቱ ዘንድ (ለካ ያኔ ነው ወጣት የነበሩት፣ ዛሬማ እነሱ ጎልማሶች እኛ ሽማግሌዎች ሆነናል!) ከአብዮቱ በፊትና በአብዮቱ ወቅት ከአገር ወጥተው ውጭ አገር በሚኖሩ ብዙ ኢትዮጵያውያን ዘንድ የተጠላ ድርጅት ነው። ለምን ተጠላ ብዬ የበኩሌን ትንተና ለማቅረብ እዚህ ቦታው አይደለም፣ የዚያ ሰው ካለኝ አንድ ቀን በሌላ አጋጣሚ እመለስበት ይሆናል። ለአሁኑ ያህል በነጥብ መልክ ላቅርባቸው።

**አንደኛ፡** በደርግ የ15 ዓመታት አገዛዝ ውስጥ መኢሶን አንድ ዓመት ያህል በሂሳዊ ድጋፍ መሰረት ላይ ከደርግ ጋር ስለሰራ ድርጅቱ ለዚህ አብሮ መስራቱ ሊወስደው ከሚገባ የፖለቲካ ሀላፊነት አልፎ፣ ደርግ በዚህ የአገዛዝ ዘመኑ የፈሰው ሁሉ በመኢሶን ስለሚላከክ ነው።

**ሁለተኛ፡** ድርጅቱ እራሱ ያደረጋቸው ስህተቶች፣ እነዚህን ሠራ የሚባሉትን ስህተቶችም እስካሁን በሕዝብ ፊት ለመወያየት አለመቻሉ ለጥላቻው ተስፋፍቶ መቆየት አስተዋጽኦ አድርጓል።

**ሶስተኛ፡** እኔም እራሴ በወሬ እንጂ በተጨባጭ የማውቀው ባይኖረኝም አንዳንድ አባላቱና ደጋፊዎቹ፣ በተለይም በድርጅቱ አባልነትና ደጋፊነት የሚገመቱ ሰዎች የፈፀሟቸው ወንጀሎች ይኖራሉ።

**አራተኛ፡** በተለያዩ ምክንያቶች ጠላቶቹ የሆኑ ድርጅቶችና ግለሰቦች ሆን ብለው ያካሄዱበት የስም ማጥፋት ዘመቻ ለመኢሶን በተወሰኑ ክፍሎች ዘንድ መጠላት ትልቅ አስተዋፅኦ አለው። ይህም ዘመቻ "in dubio pro reo" (ተከሳሹ ድርጊቱን ላለመፈጸሙ ጥርጣሬ እስካለ ድረስ ከክሱ ነፃ እንደሆነ ይቆጠራል) የሚለው፣ ለሐሰት ክስና ለፍርደ ገምድል ዳኝነት ማገጃ የሆነ የፍትህ መርህ በርግጥም ላቲን ለሆነበት፤ የሰማውን ወሬ ወይንም ክስ በዚህ መርህ መሰረት ለመመዘን ይቅርና ከኢትዮጵያ አብዮት ቅደም ተከተል (chronology) ጋር እንኳን ማገናዘብ በማይችለው መሀይም የኢትዮጵያ ምሁር ክፍል ዘንድ ከፍተኛ ተቀባይነት አግኝቷል። (በነገራችን ላይ በር እየዘጋሁ ልሂድና





ከዚህ አባባሌ የኢትዮጵያ ምሁር መሀይም ነው፣ የኢትዮጵያ ምሁር መኢሶንን ይጠላል ወይንም መውደድ ነበረበት የሚል አይከተልም)።

ይህ ሁሉ ከተነሳሁበት ነጥብ ጋር ምን ግንኙነት አለው? ትል ይሆናል አቶ ሐጎስ በተለያዩ ምክንያቶች መኢሶንን ከሚጠላው ክፍል ውስጥ ትግሬ ከሆነው በስተቀር አብዛኛው እናንተንም ይጠላል። (በውጭ በግልጽ፣ አገር ውስጥ ደግሞ ቢያንስ በሆዱ)። እናንተና መኢሶን ጠላት ከሆናችሁ እንዴት የጋራ ጠይዎች ልታተርፉ ቻላችሁ? አሁንም ዝርዝር ውስጥ አልገባም፤ የሚታዩኝን ሶስት ምክንያቶች በነጥብ መልክ ላስቀምጣቸው።

**አንደኛ:** የብሄረሰብ ምክንያት አለበት። መኢሶን ባልሆነው "የጋ* ድርጅት" እየተባለ፣ (ለኦሮሞዎች ደግሞ ቢበዛ ጎበናዎችን የያዘ የነፍጠኛ ድርጅት ነበር።) እናንተ ደግሞ በሆናችሁት የትግሬ ድርጅትነታችሁ በአመዛኙ ከአማራ በሆነው ንዑስ ከበርቴ ዘንድ አትወደዱም።

**ሁለተኛ:** ሁለታችሁም ትከተሉት በነበረው፣ መኢሶን በረዥም ጊዜ ውስጥ በኤሊ ፍጥነት፤ እናንተም ቀልጣፎች እንደመሆናችሁ ከመቅጽበትና በጄት ፍጥነት ተውነው ባላችሁት ማርክሲዝም ሌኒኒዝም ምክንያት የዘመናዊውን ጥራዝ ነጠቅ ፀረ ኮሙኒስትና የባህላዊውን ፀረ ጉግ ማንጉግ አስተሳሰብ ተከታዮች የጋራ ጥላቻ አትርፋችኋል።

**ሶስተኛ:** የአገሪቷ ባህላዊ የስልጣን ተዋረድ ሕግ በሚፈቅደው የእድገት ቅደም ተከተል ሳይሆን ከውጭ መጥታችሁ፤ (መኢሶን የፓለቲካ አጋጣሚን በመጠቀም፣ እናንተም በጉልበተኛ አሸናፊነት) ቢሮክራሲውን በእጃችሁ ለማስገባት በመሞከራችሁ (እናንተማ በማስገባት ላይ ስላላችሁ) በዚህ መዋቅር ውስጥ ባሉና ከትምህርት ተቋሞች ወጥተው ወደዚያው በሚያመሩ ዘንድ ጥላቻ አትርፋችኋል። ቢሮክራሲው የአገሪቷ ዋነኛ የሀብት፣ የስልጣንና የስራ አከፋፋይ እንደመሆኑ ውስጡ ያሉት ሆኑ ከትምህርት ተቋሞች ወጥተው እዚያ ለመግባት የሚጠባበቁት ብዙሀን፣ ቢሮክራሲው ውስጥ ያለው ቦታ እንደ ፖለቲካ አመቺነቱ በዘፈቀደ እየተበወዘ የሚታደል ካርታ ሳይሆን፣ የተለምዶን ሕግና ስርዓት ተከትሎ ሞያና ችሎታ በሚፈቅደው መሰረት የሚታደግበት መሰላል እንዲሆንለት ይፈልጋል።

ለማንኛውም የሰጠሁዋቸው ምክንያቶች ልክ ይሁኑም አይሁኑ ያለ ነዚህ መኢሶንንም እናንተንም የማይቀበሉ የህብረተሰብ ክፍሎች ኢትዮጵያን መግዛት ስለማይቻል ድጋፋቸውን ለማግኘት እየለፋችሁ ነው። በዚህ ደጋፊ ማብዛት ወይንም ቢያንስ ተቃዋሚ መቀነስ የሚባል የታክቲክ ስሌት ውስጥ በቅርቡ የኃይለ ሥላሴን ሬሳ መሸጥ የፖለቲካ ትርፍ ስላስገኘ የኃይሌ ፊዳንም ሬሳ አውጥቶ በጥላቻ ማጨማለቅ ትንሽም ቢሆን ገቢ ያስገኝ ይሆናል ብላችሁ ነው።

ሁለተኛው ምክንያት ከኃይሌ ኦሮሞነት ጋር የተያያዘ ነው። ኦሮሞ በተለይ በትምክህተኞች ዘንድ በብዛቱ የተፈራ እንደናንተ ገና





ጀግንነቱን ስላላስመሰከረ (ማለትም ነፃ አውጭ ድርጅቱ የናንተን ያህል ካላሺን ስለሌለውና የጦር ሜዳ ድሎች ስላላስመዘገበ)፣ የሚናቅ ብሄረ ሰብ ነው። ኃይሌ ፊዳ ደግሞ በኦሮሞነቱ የዚህ ክፍል ፍራቻ፣ ንቀትና ጥላቻ ተጣምረው ያረፉበት ሰው ነበር። አቶ ሐጎስ በጽሁፍህ የተጠቀምክባትን "እውር ቢሸፍት ከዱሮ አያልፍም" የምትል አባባል እኔ እስር ላይ እያለን ከኃይሌ ገዳዮችም ሰምቻት ነበር። እነርሱ ግን በትዕቢት ባትተናነሱም ያንተን ያህል ትንሽ መደበቅ ስላልታያቸው፡ "ጋ*" ቢሸፍት ከሱሉልታ አያልፍም" ብለው ተሳልቀውብን ነበር። ለማንኛውም ከኦሮሞ ግንባር ጋር ዛሬ ባላችሁ ከታች በምመለስበት በአመዛኝ የካላሺን ቆጠራ ጠብ፣ ይህ ኃይሌ ፊዳን የሚጠላን ክፍል ደንበኛ ለማድረግ እየጣራችሁ ስለሆነ፤ ውስጥ ውስጡን መሸጥ ለጀመራችሁት "እኛ ከሌለን ኦሮሞ ያርዳችኋል" የሚለው አዲስ ሸቀጥ የኃይሌ ሬሳ ጥሩ መጠቅለያ ይሆናችኋል።

ለኔ ደግሞ ኃይሌ በሙሉ ልቤ መኢሶንነቱን፤ በግማሽ ጎኔ ኦሮሞነቱን፤ ዛሬ አንተ እጅ የወደቀውን ቃል የደርግ ሰው ማረጃ ቄራ ውስጥ ሲሰጥና ከዚያም በእስር ቤት ካሳለፍኳቸው አምስት ዓመታት መንግስቱ ኃይለማርያም ወስዶ እስኪገድለው ድረስ የመጀመሪያዎቹን ሁለት ዓመታት እጣውን የተካፈልኩት ሰው ነበር። በእርሱ ሞት አንድ ታላቅ ጓደኛ ብቻ አይደለም ያጣሁት በወጣትነት ዘመኔ የኔም የነበረው የአንድ ትውልድ ቆንጆ ሕልም ነው አብሮ የከሰመብኝ።

## 2. የኔ ጽሁፍ ዓላማ

እኔ በኃይሌና በሌሎች የመኢሶን ወዳጆቼ ሞት እርር ድብን ብዬ የምኖረውን ያህል በነርሱ ሞት የፈነደቁ፤ በጠቅላላው በመኢሶን ላይ በደረሰው ውድቀት የተደሰቱ በተለይ ከኢትዮጵያ ከወጣሁ ወዲህ ብዙ አጋጥመውኛል። ለብዙዎቹ መኢሶን ላይ ላላቸው ክስ እንኳን በጽሁፍ በአፍም መልስ ለመስጠት አልሞከርኩም ገና የመኢሶን ዓላማ ይህ ነበር፤ የሞከረው ይህንን ነው፤ የተሳሳተው ያንን ነው፤ ከአቅሙ በላይ የሆኑት ደግሞ እነዚህ ናቸው ብዬ መከራከር ስጀምር ለእውነትና ለእውቀት ቦታ የለም" የሚል ሰሌዳ ግንባራቸው ላይ የተጻፈ ያህል እየታየኝ ከነርሱጋር መዳረቁ ዋጋ የለውም በማለት ነው የተውኩት። የፍትህ፤ የእውቀትና የእውነት ፍቅር የሚገበይበት አደባባይ ሳይሆን ሐሜትና ጥላቻ ብቻ የሚቃረምበት ልክስክስ ቦታ ስለሚውሉ የተጠናወታቸው ፀረ መኢሶን ሰይጣን ብቻ ሳይሆን የድንቁርና ጋኔን ጭምር መሆኑን በመረዳቴ ነው። የተለከፉት በትልቁ የድንቁርና ጋኔን ሆኖ ሳለ እኔ በመኢሶን ካድሬነት ሚጢጢዋን ፀረ መኢሶን ሰይጣን ለመጋተር መሞከሩ አልታየኝም። ትልቁ ሊቀ አጋንንት ደግሞ ከአቅሜ በላይ ሆኖ ተስፋ አስቆረጠኝ። "እውነተኛው ጋኔን" የሚባረረው በድርሳነ ሚካኤል እንደሆነ ሁሉ፣ ይህንንም ብዙውን የአገራችን ምሁር የተጠናወተውን የድንቁርና ጋኔን የሚያባርሩት ድርሳነ እውቀትና ድርሳነ እውነት ብቻ ናቸው። ስለሆነም ላገሬ በካላሺን የደለቡ ጀግኖች ሳይሆን፣ እነዚህን ድርሳኖች የሚጽፉ ሐዋርያት በድርሳኖቹ አማካይነትም እነዚህን የድንቁርና አጋንንት የሚያባርሩ አባ ወልደተንሳዮች ተመኘሁላት።





ይህ እንግዲህ ቅንፍ ውስጥ ነው አቶ ሐጎስ ወደ አንተ ልመለስና አንተንም ከነዚህ ፀረ መኢሶኖች ለይቼ አላየሁህም የኃይሌ ፊዳን እሬሳ ልትሳለቅበት ስታወጣ "ይህኛው ደግሞ መቃብር ቤት ድረስ የሚያስገባ ጥላቻ ነው የተጠናወተው" በሚል ትዝብት ላልፈው በተግባኝ ነበር። ከኔ መልስ የማግኘት "ክብር" ያገኘኸው በሚቀጥሉት ሁለት ምክንያቶች ነው።

አንደኛው ምክንያት ትእቢተኛውን ልብህን ጥላቻ የሞላውን ያህል ብዕር የማያምርበት እጅህ ካላሺን ስላነገተ ነው። የዱርዬ እብሪት ካላሺንና ጥላቻ ሲዋሀዱ የሚያስፋፉትን ድንቁርናና እልቂት የቅርብ ጊዜ ታሪካችን እስኪዘገንነን ድረስ አሳይቶናል። የእነዚህ ሶስት እርኩስ ነገሮች ውህደት አሁንም እንዳንዝበበብን ነው። የዚህ ደብዳቤዬ ዓላማ፤ እያነበብከው ስትሄድ ግልጽ እንደሚሆነው፤የኃይሌን ጀግንነት ሆነ የመኢሶንን ትክክለኛነት ለማሳየት ሳይሆን፤ መኢሶንን ወደደ ጠላ ለማየት ለሚፈልግ ሁሉ የዚህን አደጋ ቅርብነት ለመጠቆም ነው።

ሰው ሁሉ እንደኔ ኃይሌን ይውደድ፤ እንደኔ ኃይሌን ያክብር ማለት የማልችለውን ያህል ሰው ሁሉ መኢሶንን ይደግፍ ማለት አልችልም። መኢሶንን ያልደገፈ የኢትዮጵያ ጠላት ነው የሚል እብደትም አይከጅለኝም። ኃይሌ ጀግና ይሁን ፈሪ፣ በግፍ የተገደለ ሰው ሬሳ ላይ መሳለቅ እንደማይገባ ሁሉ፤ የፈለገውን ስህተት ቢያደርግ የፖለቲካ ጭፍጨፋ የተካሄደበት ድርጅት ላይ እንደገና የታሪክ ወንጀል ሊፈጸምበት አይገባም ባይ ነኝ። በዚህ መልኩ ብቻ ነው ጽሁፌ ከኃይሌና ከመኢሶን ጋር በቀጥታ የሚገናኘው። ለኔ ጉዳዩ ከኃይሌ አልፎ ከመኢሶን አልፎ

በአጠቃላይ የሰብዓዊነትና የፖለቲካ ፍትህ ጥያቄ ይሆናል። የትላንት ለቅሶ ምክንያት ምን ነበር ከሚል የታሪክ ጥያቄ ዛሬ ምን እየተደገሰልን ነው ወደሚል የፖለቲካ ጥያቄ ይሻገራል። ይህ ደግሞ የተገደሉብን ወይንም በህይወት የተረፍነው መኢሶኖች ጥያቄ ወይንም ጉዳይ ብቻ ሳይሆን የዚህች አገር ከእልቂት ማጥ አለመውጣት የሚያሳስባቸው ወገኖች ሁሉ ጥያቄ ነው።

ለዚህ ነው አቶ ሐጎስ ባንተ ጽሁፍ አሳብ ለእነዚህ ወገኖች አንዳንድ አስተያየቶች ማቅረብ የፈለግሁት፣ እኔ የፖለቲካው ብቻ ሳይሆን የግል ህይወቴ በሺህ ድሮች ከመኢሶን ጋር ስለሚያያይዘኝ መኢሶን ሁለተኛው ቤተሰቤ ሆኗል። መኢሶን ነክ በሆነ ጉዳይ ሁሉ የማሳየው መቆርቆር “በመኢሶን የመጣ በዓይኔ መጣ” ከሚል አቋም የመነጨ ሊመስልብኝ ይችላል። መኢሶንን በፈለገው ምክንያት ለምትጠሉ፣ ኢትያጵያን ለምትወዱ ያለኝ መልዕክት መኢሶንን ውደዱልኝ የሚል አይደለም። ትልቁ ምኞቴ በገዳዳ የአሸናፊ መነጽር ሳይሆን፤ ከፊታችን የተደቀነውን ጨለማ በሚያበራ፣ በጥላቻ ሳይሆን በእውነት በተሞላ የታሪክ ባትሪ የትናንት ጉዞአችንና አገራችን ያለፈችበት የእልቂትና የመከራ ዘመን እንዲመረመር ነው።

እነ አቶ ሐጎስ የትላንቱ ጥላቻና ጥርጣሬ ዛሬ ቢያገረሽበት ትልቅ የፓለቲካ ጥቅም ያገኙበታል። መኢሶንን በፈለጋችሁት ምክንያት የምትቃወሙ ሁሉ ይህን በመኢሶን ላይ የሚካሄደውን የTPLF ዘመቻ “መኢሶን ሲታማ ለኔ ብለህ ስማ” እንደሚባለው ብታደርጉ ያዋጣችኋል ባይ ነኝ። ያቅምስልኝ ደግ አደረገ፣ እኔን ምን ቸገረኝ ከምትሉ “ነግ በኔ”





ብትሉ ለኢትያጵያ ይበጃታል ባይ ነኝ። ለቆየ ባላጋራ የታሪክ ፍትህ የሚነፍግ፣ ለዛሬ ተቃዋሚ (እነ ጆርጅ ቡሽ ጋ ያስጉጠኛል ከሚላቸው በስተቀር) ፍትህ አያመጣም። ያለፈን ታሪክ በጥላቻ የሚያጨማልቅ የዛሬን ታሪክ በደም ከማጨማለቅ አይመለስም። ያለፈን ታሪክ ጠምዝዞ መስክርልኝ የሚል፣ ዛሬ የሕዝብን እጅ ጠምዝዞ “ምረጡኝ” ከማለት አይመለስም።

አቶ ሐጎስ እንግዲህ ይህን ግልጽ ደብዳቤ ለመፃፍ የነበረኝ የፖለቲካ ምክንያት ይህ ነው። ሁለተኛው ምክንያት ግን በጣም የግል ጉዳይ ነው የኃይሌ ጉዳይ ሆኖብኝ ነው።

ይህን ጽሁፍ እንድጽፈው ምን እንዳነሳሳኝና ለምን እንደጻፍኩት ካሳወቅሁህ በኋላ ወደ ጽሁፉ ልገባ እችላለሁ። ከዚያ በፊት ግን ይዘቱን ይህን የያዘውን መልክ ስለሰጡት፣ በቀጥታ ባንተ ጽሁፍ ላይ ሳይሆን “በአካባቢ መረጃዎች” ላይ ስለሚመረኮዙ ግምቶቼ አንዳንድ ማብራሪያዎች ልስጥህ።

## 3. ተጨባጭ መረጃ ላይ ያልተመረኮዙ ግምቶቼ

መጀመሪያ ነገር፣ ምንም ተጨባጭ መረጃ ሳይኖረኝ ስላንተ አንዳንድ ግምቶች ወስጃለሁ። አንደኛ ከአሲምባ ወደ አዲስ አበባ ባደረጋችሁት “ታሪካዊ ጉዞ” የት ላይ እንደተሳፈርክ አላውቅም እንጂ የአሸናፊው የTPLF አባል ነህ ብዬ ገምቻለሁ። ከአሸናፊዎች አንዱ ባትሆን ኖሮ ይህን ከደርግ አልፎ አነሰም በዛ የታሪክ ንብረት የሆነ “ማጋለጫ”

በግልህ ወስደህ ለግል መጽሄትህ መጠቀሚያና ለድርጅትህ ቂም መወጫ ልታደርገው ባልቻልክም ነበር። በተጨማሪም፣ የደርግ ገራፊዎችና ገዳዮች የስራ ውጤት አንተ እጅ ከገባ፣ አንተም በTPLF ውስጥ "የፀጥታ" ሀላፊነት የተጣለብህ ነህ ብዬ ጠረጠርኩ። (መጽሄት ላይ "ጽሁፍ" ማውጣትህ ምሁርነትህን ስለሚያሳይ እንደነ ተኮላ[9] ተራ ገራፊ አይደለህ ይሆናል)። ሳላውቅህ ከደርግ ጨካኞች ጋር ላመሳስልህ ያበቃኝ የነርሱን የስራ ፍሬ ለገበያ በማቅረብህ ብቻ አይደለም በኒቸ አባባል አንድ አሰቃቂ ታሪክ ሲነበብ ስለአሰቃቂው ክንውን ብቻ ሳይሆን ስለተራኪውም ብዙ ማወቅ ስለሚቻል ነው።

ከአሸናፊዎቹ አንዱ መሆንህን ያሳየኝ ሌላ እሩቅ የማያስኬድ ነገር እፎይታ የሚለው የመጽሄታችሁ ስም ነው። ያንተኑ መደዴ ፖለሚክ አንተው ላይ ልጠቀምና፣ ዛሬ እፎይ ሊል የሚችለው የኢትየጵያ ሕዝብ ሳይሆን ከአሲምባ ተነስቶ ከትናንት ወዲያ የኃይለ ሥላሴ ትላንት የደርግ የነበረው ዙፋን ላይ "ቂጥ" ለማለት የበቃው TPLF ብቻ ነው። በተራችሁ ሌሎችን ወደ አሲምባዎች እያባረራችሁ ስለሆነ ብዙው ኢትዮጵያዊ ሌላ የ15 ዓመት አስከፊ የደም መፋሰስ ዘመን ይከተላል የሚል ስጋት ውስጥ ነው ሊኖር የሚችለው።

በዚህ ደብዳቤ ውስጥ ደጋግሜ ስለታክቲካችሁና ስለአስተሳሰባችሁ በማወራበት ጊዜ እናንተ መሀል ሆኜ የሰማሁ ያህል እርግጠኛ ሆኜ እጽፋለሁ። ይህን የሚያስችሉኝ ሁለት የተያያዙ "ችሎታዎች" ናቸው።

9. ተኮላ ማሞ የደርግ ምርመራ ክፍል ውስጥ እስረኞችን በጭካኔ በማሰቃየትና በማንገላታት ይታወቀ የነበረ ጨቃኝ ገራፊ ነበር። ኢህአዴግ ሥልጣን ከያዘ በኋላ ባቋቋመው ፍርድ ቤት አሥራ ሁለት ዓመት ተፈርዶበታል።





አንደኛ ነገር፣ ሰሜን ሸዋ እስክትደርሱ ድረስ ትከተሉት በነበረው ርእዩተ ዓለም እናንተ ሀሁ ስትቆጥሩ እኔ ፍካሬ ዘፃድቃን ደርሼ ነበረ። (የችሎታን ሳይሆን የዕድሜን ልዩነት ለመጠቆም ያህል ነው። ከፕሮግሬስ ፐብሊሸርስ አደዳቢ ፓምፍሌቶች ሳይሆን ከምንጩ መቋደሴ ሌላም ልዩነት ያመጣ ይሆናል) ለማንኛውም ግን፣ የፒካሶን ስዕሎች በደንብ የሚያውቅ ሰው የተኮረዠ የፒካሶ ስዕል ሲያይ ቅጂው ከየትኛው ስዕል እንደሆነና ከዋናው ስዕል እንዴት እንደሚለያይ ያውቃል። በልዩነቱም እንደሁኔታው ይስቃል ወይንም ይበሽቃል። እኔም የናንተን የትንተና ቅጂዎች ሳይ፣ ከየት እንደተኮረዡ ስለማውቅ ከዋናው ጋር እያስተያየሁ አዲስ አበባ እስክትደርሱ ድረስ እስቅባቸው ነበር። አዲስ አበባ ከገባችሁ ጀምሮ ግን ያሰጉኝ ጀምረዋል።

ስትማከሩ ሳልሰማ አስተሳሰባችሁን የሚያሳውቀኝን ሌላ ልዩ ችሎታ ከየት እንዳመጣሁት ደግሞ በአንድ ከልጅነት ታሪኬ በተወሰደ ምሳሌ ላሳይህ። እንደምታውቀው በኛ ዘመን፣ በኛ አገር ያለውም ቤተሰብ ቢሆን ለተማሪ የኪስ ገንዘብ አይሰጥም። ገንዘብ ለማግኘት ቤተሰብ ማታለል ያስፈልግ ነበር። ታድያ እኔ አባትና እናቴን እንጂ የነርሱ ታናናሽ የሆኑትን አጎቶቼን መሸወድ አይቻለኝም ነበር። ምክንያቱም እነሱም አንዳንዶቹን ዘዴዎች አያቴ ላይ ተጠቅመው ስለነበር ወይንም ስለነዚህ ዘዴዎች አሰራር የራሳቸው "ትምህርት" ስለነበራቸው ወዲያው ይነቁብኝ ነበር። አንደኛውን "ጋሽ በዙ፤ ለሺት ለትምህርት ቤት መዋጮ ፍራንክ አምጡ ተብለናል" ስለው "ሲኒማ መግባት አምሮሻል አይደል?'' ይልና ከቻለ ይሰጠኝ ነበር። ወደአንተና ወደኔ ልመለስና አቶ ሐጎስ፣ ከሌኒን እስከ ማኦ ያሉት የስልጣን ኮሙኒስቶች

ስለ ሕብረተሰብ የሚሰጡት ትምህርት እጅግም ነው። ጽሁፎቻቸውን ዘጠና በመቶ የሞላው የስልጣን መያዣና ማቆያ ዘዴዎች መፈብረኪያ መመሪያ ብቻ ነው። 'የተግባር" መመሪያ አገኝባቸዋለሁ ብዬ አምን የነበረ ዘመን ከላይ እስከታች "ፉት" ብያቸዋለሁ። ስለዚህም ከነሱ ትምህርት ቤት በተገኘ ዕውቀትና ዘዴ አንዲት ጭረት ስታስቀምጥ የትኛውን ስዕል ልትሰራ እንደተነሳህ አውቀዋለሁ።

(በነገራችን ላይ ይህን ሁሉ ስል የነጆርጅ ቡሽ ዘመን የድህረ ኮሙኒዝም ፀረ ኮሙኒስት ስለሆንኩ አይደለም። ዛሬ ሌኒንና ማኦን እንደገና ለማንበብ ሥራ አልፈታም። ሆኖም ጳውሎስ ኞኞ በጥላሁን ገሰሰ ቲፎዞነቱ ካስር ላሌ ጉማ አንድ ሞናሊዛ" እንዳለው እኔም ከአስር የሌኒን "ምን መደረግ አለበት?"[10] አንድ የማርክስ "አስራ ስምንተኛው ብሩሜር"[11] ይበልጣል ባይ ሆኛለሁ ለማለት ነው)። ድሮ የማርክስ ወራሽ አድርጌ የወሰድኩት ሌኒን ዛሬ ለምን የማርክስ አፍራሽ ሆኖ እንደሚታየኝ ለማብራራት እዚህ ቦታው አይደለም። ከታች ትንሽ ነካ አደርገዋለሁ። ዋናውን ማብራሪያ ግን ለሌላ አጋጣሚና ለሌላ ጽሁፍ እተወዋለሁ።)

## 4. አሮጌ ጠላ በአዲስ ጋን

አቶ ሐጎስ አንተን ማለት የፈለግሁት የፕሮፖጋንዳ ፋብሪካችሁ የሚያወጣቸውን ሸቀጦች ሁሉ ለምን ዓላማ እንደተነደፉና እንዴት እንደተሰሩ አውቃለሁ ለማለት ነው። ሸቀጡ ያው ሆኖ "ጊዜው

10. Vladimir Ilyich Lenin. (1902). What Is To Be Done?

11. Karl Marx. (1852). The Eighteenth Brumaire of Louis Bonaparte.





ያለፈበትን" መጠቅለያ አውልቃችሁ በአዲስ ሞድ አሽብርቃችሁ ስታቀርቡትም፣ አቶ ሐጎስ ይህቺን ለሌላ፤ ጋኑ ነው እንጂ አዲስ፣ ጠላው ያው የድሮው ነው ለማለት እችላለሁ ለማለት ነው።

የኢትዮጵያ ሕዝብ አዲስ ጋን ምንም አያደርግለትም። ያማረው እስከዛሬ ቀምሶት የማያውቀው አዲስ ጠላ ነው። ይህ ጠላ እንዴት እንደሚጠመቅ አላውቅም። አዲስ ጠላ የመጥመቅ ሙከራ ውስጥ ግን ተሳትፌ አውቃለሁ። የዛሬ አስራ ስምንት ዓመት ግድም እዚሁ አሁን ይህን ደብዳቤ የምጽፍበት ከተማ እያለሁ አገሬ አዲስ ጠላ ለመጥመቅ ጥንስስ መጠንሰሱን ሰማሁ። ሞተውም እረፍት ከነሳሀቸው ወዳጆቼ ጋር ያኔ በነበረችን አቅምና ችሎታ ጌሾ ወቀጣው ላይ ለማገዝ ተመለስን። በዋና ጠማቂነት በታሪክ ተሹሜአለሁ ይል የነበረው የያኔው ባለካላሺን፣ ከፋም ለማ ጥሩ ጠላ ይውጣው አይውጣው ሳይታወቅ፣ ዓመት ያህል ጌሾ ወቀጣው ላይ እንደተሳተፍን ጌሾ እንዲህ አይወቀጥም ብሎ አንተ በአልባሌነት ሞቱ የምትላቸውን ወዳጆቼን ጨረሰ። እኛ በዚህ ጥንስስ ዝግጅት ውስጥ መሳተፍ ከተውን ወዲህ ብዙ የውጭና የውስጥ ጠላ ጠማቂ ጠበብቶች ተሳትፈውበት የወጣው ጠላ የሚኮመጥጥ እንደነበረ፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ ይህንኑ ቆምጣጣ ጠላ "ይጣፍጣል እያልክ ጠጣ" ሲባል እንደከረመ ይታወቃል።

አቶ ሐጎስ ስለዚህ የጠላ ታሪክ ያንተ አስተያየት እንግዲህ ሌላ ነው። አንተ ድሮውንም ጠላውን ለመጠጣት እንጂ ለጌሾ ወቀጣ አይደለም የተመለሳችሁት ባይ ነህ። ለተወሰነ ጊዜ አብረነው ጌሾ መውቀጥ እንችል ይሆናል ብለን ከነበርነው ጉልበተኛ ጋር የተጣላነው በጠላው

አጠማመቅ ላይ ሳይሆን በጠላው ክፍያ ላይ ነው ባይ ነህ። በበኩሌ ዛሬም በሙሉ እምነት ለጌሾ ወቀጣ እንደተመለስን እመሰክራለሁ። ለደርግ የኮመጠጠ ጠላ የአመት ጌሾ ወቀጣ ሊያዋጣ የሚችለውን ያህል አስተዋጽኦ አድርገናል። ጥንስሱ በጣም የተበላሸው ከባህር ማዶ ቅመማ ቅመም መምጣት ከጀመረ በኋላ፤ ያገር ቤቱም ጠማቂ "ያለኔ ጠማቂ ላሳር ነው" ማለት ከጀመረ በኋላ ይመስለኛል። ኮምጣጣነቱ ዛሬ ስለማያጠራጥር ጠማቂውም ስለተወገደ ይህ ሁሉ ቀስ ብሎ የሚጣራ የታሪክ ጥያቄ በሆነ ነበር። ክርክሩን ጊዜያዊ የሚያደርገው አንተ አዲስ ጠላ መጥመቅ ጀምሬአለሁ ስለምትል ነው።

አቶ ሐጎስ፣ እናንተ አገሪቱ ከናንተ የተሻለ ጠላ ጠማቂ አፍርታ እንደማታውቅ ከናንተ በፊት ጠላ ለመጥመቅ የሞከረ ሁሉ የደርግ ዓይነት የኮመጠጠ ጠላ ብቻ ሊያቀርብ ይችል እንደነበር፤ የናንተ ጠላ ብቻ የኢትዮጵያን ሕዝብ የሚያረካ እንደሆነ የምትለፍፉበት ምክንያት አላችሁ። እኔ ደግሞ ከላይ የጠቀስኩት የጌሾ ወቀጣ ልምድ ብቻ ሳይሆን ስለጠላ ጠመቃ ከዚያ ወዲህ ካደረግሁት ጥናት ተነስቼ ስለአዲስ ጥንስስ ሲወራ ተጠራጣሪ መሆን ጀምሬአለሁ። የእውነቱ ጠላ ይሁን የምሳሌ ጠላዬ እንዴት እንደሚጠመቅ አላውቅም። የኢትዮጵያ ሕዝብ እየወደቀ እየተነሳ፣ በሀሳብ እየተጣላ፣ እየታረቀ፣ እየተሳሰተና እያረመ በሚያበቅለው ብቅል አማካይነት ብቻ ነው ሊጠመቅ የሚችል የሚል አጠቃላይ ግምት ብቻ ነው ያለኝ። ለዚህ ደግሞ ካላሺን ከኢትዮጵያ የውስጥ የፖለቲካ መድረክ መውጣት አለበት። በእርግጠኛነት የማውቀው ነገር ቢኖር ካላሺን ያነገተ ጥሩ





ጠላ ጠማቂ ሊሆን እንደማይችል ነው። "ጠላ የሚያስገኝ እስከሆነ ድረስ የፈለገውን ቅጠል መቀንጠስ ይቻላል" በሚለው የተለመደ ዘዴ፣ በጀግንነትና በወኔ ጌሾነት እንዲሁም በካላሺን ወቃጭነት ከሚጠመቅ ጥንስስ ኮምጣጣ ጠላ ብቻ ነው መጠበቅ የሚቻል። የናንተም ጥንስስ በአዲስ ጋን ቀረበ እንጂ ኮምጣጣ ጠላ ነው የምታቀርቡልን፤ ከዚያም እንደደርግ ሁሉ ይጣፍጣል ጠጡ እያላችሁ ሳታስገድዱን አትቀሩም ለማለት የምደፍርበትን ምክንያቶች እንግዲህ ከዚህ ቀጥዬ አቀርባለሁ። እስከዚያው ድረስ ግን በዚህ ጽሁፍ መጨረሻ የማቀርብልህ ጠላ እስኪደርስ ድረስ ጉሹን አየተጎነጨህ እንድትቆይ ያህል እነሆ።

## የኢትዮጵያ ሕዝብ ዋና ጠላት ካላሺንኮቭ ነው!!

ርዕሰ ብሄርህ የሚናገረው ቋንቋ አይደለም ዋናው ነገር፤ የአንጋቹ ዓላማ መታየት አለበት ይላል። መንግስቱ ኃይለማርያምም ከመሰሪያው ጀርባ ስላለው ዓላማና ወኔ ይለፈልፍ ነበር። እኔ ስለ ካላሺን አንጋች ወኔ ሆነ፣ ስለሚከተለው ዓላማ መመራመርም አልፈልግ። የሐጎስ ዓላማ ቅዱስ ነው፤ የፈይሳ ዓላማ እርኩስ ነው፤ ማንም ማንንም የማይረታበትና ማለቂያ የሌለው የፍልስፍና ጥያቄ ነው። የሐጎስም ጥይት ይገድላል፤ የፈይሳም ጥይት ይገድላል። የሚሞተው ሰው ነው። ይህ ነው የማያከራክር። ስለዚህም ከሰላም ወዳዱ ፀረ ፋሺስት ከካርል ክራውስ ጋራ" ካላሺን ያነገተ ሁሉ ተጠባባቂ ነፍሰ ገዳይ ነው" እላለሁ።

በሚቀጥሉት ገጾች እንግዲህ ስለምን ካላሺን ያነገተ ሁሉ ለሕዝብ የሚሆን ጠላ ሊጠምቅ አይችልም እንደምልና በጠቅላላው ከካላሺን

ጋር ስላለኝ ጠብ፣ እንዲሁም አንተ እጅ ዲሞክራሲ አዲስ ጋን ብቻ እንደሆነ፣ ለምን ውስጡ ያለው ጥንስስ ኮምጣጣ ጠላ እንደሚያስገኝ አስረዳለሁ። ወደዚሁ ከማለፌ በፊት ግን ሁለት የመጨረሻ አጫጭር የግል ማስታወሻዎች አሉኝ።

**አንደኛ፡** በዚህ ጽሁፍ ስለጀግንነትና ስለፍርሀት ሳወራ፣ በግል ሕይወት ውስጥ ስለሚኖረው የሐጎስ ጀግንነት፣ የደረጀ ፈሪነት እንዳልሆነ ይገባሀል ብዬ እገምታለሁ። ከተማ መኮንን አብዮቱ ሳይገባቸውና ሳያገባቸው፣ እንዲሁ ብቻ ሲያስጨንቃቸው የከረመውን በርካታ ወዳጆቼን አስመልክቶ

> መገን ያራዳ ልጅ ጠመንጃም የላቸው
> በየደረሱበት መለኪያ ቦምባቸው

ብሎ እንደዘፈነላቸው ዓይነት እነመዓዛ ቤት መድረክ ላይ በከተማ መኮንን ትርጉሙ ይህን ቦምብ የምትጥል ጀግና ብትሆን እንኳን ላገር ለኔም አሳሳቢ አትሆንም ነበር። እነመዓዛ ራሳቸው አንተንም እስኪበርድልህ ድረስ ግፋ ቢል ሁለተኛ ፖሊስ ጣቢያ አሳድረው በነጋታው የተጣላኸውን ወንድምህን ሁለት መለኪያ አስጋብዘው የሚጨርሱት ጉዳይ ነው። እኔ የፖለቲካውን ጀግንነት ማለቴ ነው።

ይህን ለሕዝብ ለመሰዋት ዝግጁ ነኝ አስብሎ፣ የሕዝብ ጠላት ነው የተባለ ላይ እውነተኛ ቦምብ የሚያስጥለውን ወኔ ነው ለአገር መዘዘኛ ነው የምለው። እኔማ አንተ ጀግናው ያነገትከው "ነፃ አውጬ" ቦምብ



ታዝቤ ዝም ከምል

ነው እንጂ የሚዘገንነኝ የአራዳ ልጆችስ ቦምብ አልፎ አልፎ ትዝ ሲለኝ ይናፍቀኛል።

**ሁለተኛ፡** ፍርሀትንም በሚመለከት ሼክስፒር በኔ ትንሽ ገዳዳ ትርጉም

> ፈሪ ሳይሞትም በፊት ደጋግሞ ሲሞት ነው የሚኖር
> እኔን በጣም የሚገርመኝ በዚህች ምድር
> አጅሬ ሞት አንዱን ቀን መምጣቱ ላይቀር
> ነው የሰዎች እርሱን ፈርቶ መሸበር

እንዳለው፤ የተፈጥሮን ሕግ ተከትሎ የሚመጣን፣ ወይም ሳይታሰብ በመኪና አደጋ በአረቄ መዘዝ ወዘተ ምክንያት የሚመጣን ሞት ፈርቶ ሲሸበሩ መኖር ኑሮ አይደለም። እኔ ከፖለቲካ የሀላፊነት ስሜት የሚመነጨ በፖለቲካ ምክንያት የሚደርስን ሞት ፍርሀት ማለቴ ነው። ጀግና ሆኖ በፈሪ ጥይት፣ ፈሪ ሆኖ በጀግና ጥይት አንድም ሰው በፖለቲካ ምክንያት በሚሞትባት ኢትዮጵያ የፖለቲካ ነፃነትና ማህበራዊ እድገት ሊኖር አይችልም። በፖለቲካ ምክንያት ሰው የማይሞትባት ኢትዮጵያን ለማምጣት ደግሞ ለፖለቲካ ዓላማ ለመሞት ዝግጁ መሆንን መተው አለብን፤ በዚህ መንፈሱ ሞትን መፍራት አለብን ለማለት ነው። ለምሳሌ "ዲሞክራሲ ወይንም ሞት፤ እናት አገር ወይንም ሞት"

የሚለውን መፈክር እንኳን ላነግበው ስሰማው እራሱ ያስፈራኛል። እኔ ኢትዮጵያን እወዳለሁ ልኖርባትም እፈልጋለሁ። ልሞትላትም፤ ልገድልላትም ግን ዝግጁ አይደለሁም። ጀግኖች ልጆቿ ናቸው እንጂ

እርስዋማ መናገር ብትችል ኖሮ ይህን ከኔ አትጠብቅም ነበር። ጀግና ሆነ ፈሪ ካህሳይ ተባለ መገርሳ ሟችም ገዳይም ያው ልጅዋ ነው። አገር ልጆችዋ እንዲኖሩባት፣ እንዲኖሩላት እንጂ እንዲሞቱላትና እንዲጋደሉላት አትፈልግም።

በዚሁ እንግዲህ ስለአዲሱ ጋንህ ወደማውራቱ ልለፍ።





# ክፍል ሁለት

## 1. ዲሞክራሲ የተሸናፊ መብት ማረጋገጫ ነው

ኮምጣጣ ይሁን ጫፋጭ ፖለቲከኛ የተባለ ዛሬ ጠላውን የሚያቀርብበት ጋን ዲሞክራሲ ሆኗል። የናንተም የእፎይታ መጽሄት አዘጋጅ ቡድን ዓላማው “ዲሞክራሲያዊ ባህል በመሀላችን ሰርጾ እንዲገባ ማድረግ ነው” ይላል።

እናንተ አዲስ አበባን ከያዛችሁ በኋላ (አውቄ ነው ያዛችሁ የምለው አቶ ሐጎስ። ትግራይን ነፃ አውጥታችኋል፤ አዲስ አበባን ግን ከሌሎች ጋር በእኩልነት እስካልገዛችኋት ድረስ እንደያዛችኋት ነው የምቆጥረው።) ኢትዮጵያ ገብቶ የወጣ አንድ ጀርመን ጋዜጠኛ የመፈክሮችን ጋጋታና አገሪቷ ያለችበትን የፖለቲካ ሁኔታ አገናዝቦ “ያለዲሞክራቶች ዲሞክራሲን” ለመገንባት እንደመነሳት አድርጎ ስለቆይታው አንድ ረዘም ያለ ጽሁፍ ጽፎ ነበር። ታሪኩ፤ ባህሉ፤ ልምዱ፣ የሕብረተሰብ ስርዓቱ ዲሞክራሲን የማያውቅና ለዲሞክራሲ የማያመች አገር ነው ያለን። ሁኔታዎች ዲሞክራሲን እንዲያግዙ ሆነው መለወጥ አለባቸው። በፖለቲካ ብቻ ሳይሆን በባሕል ልዩ ልዩ ዘርፎች ዲሞክራሲያዊ ልምድ

መስፋፋት አለበት። እዚህ ላይ እንግዲህ ወጣቱ ማርክስ ከይርባህፉ ቴሲሶቹ በአንደኛው ውስጥ የሚለውን ማስታወስ ለእንዳንተና ለእንደኔ ዓይነቱ ጥሩ ነው አቶ ሐጎስ።

> **“የተለወጠ ሁኔታና አዲስ ትምህርት ሰውን ይለውጣል ብለው የሚያምኑ የሚዘነጉት ሁኔታዎችን የሚለውጡት ሰዎች መሆናቸውንና እናስተምራለን ባዮቹ እራሳቸው አስቀድመው መማር እንዳለባቸው ነው”**[12]

ዴሞክራሲን አውቀናል ሌላውን ማሳወቅ ብቻ ነው የቀረን የሚል ግብዝነት እንዳይሰፍን ነው፤ ይህን “ጊዜው ያለፈበት” ፈላስፋ የጠቀስኩት። ዛሬ በዚህ ጽሁፍ የምሞክረውም ዲሞክራሲን ለማስተማር አይደለም። እራሴም በሕይወት ት/ቤት እየተማርኩት ስለሆነ ላስተምረው ብቁ ነኝ የምለው ርዕስ አይደለም፤ በማስተምረው ትምህርት ራሱ ያለፉት ዓመታት ልምዴ ያስተማረኝ፣ ይህን ያህልም “ሳይንሱን” ማስተማር ሳይሆን፣ ተማሪው በራሱ ለመማር የሚያስችሉትን ጥያቄዎች እንዲያነሳ መርዳት የበለጠ ጥቅም እንዳለው ነው። ስለሆነም አቶ ሐጎስ በእውነት ስለዲሞክራሲ ለመማርና ለማስተማር ከተነሳህ ከሚከተሉት ሁለት ጥያቄዎች አንፃር አቋምህን እንድትመረምር ላሳስብህ ነው የምሞክረው።

12. Karl Marx – Theses on Feuerbach





**አንደኛ፡** ዲሞክራሲ የአሸናፊ መፈንጫ ሳይሆን፣ የተሸናፊ መብት ማረጋገጫ ነው።

**ሁለተኛ፡** ዲሞክራሲ ሽጉጥ የሚማዘዙ ጀግኖች ሲያሰኛቸው ይዋጣልን የሚሉበት ሳይሆን፤ “በምንም ዓይነት ሁኔታ ሽጉጥ ላለመማዘዝ የወሰኑ ፈሪዎች ተከባብረው በሰላም አብረው ለመኖር የሚፈጥሩት የፖለቲካ ስርዓት ነው።

አቶ ሐጎስ እንግዲህ አንደኛ አሸናፊ ስለሆንክ፣ ሁለተኛ ጀግና ስለሆንክ ዲሞክራት ለመሆንና ለዲሞክራሲ ለመታገል ከኔ የበለጠ ያስቸግርሀል። “ካላሸኔ እስካለ ተወው ይለፍልፍ፤ ካላሸን እስከሌለው ተወው ይደራጅ የት እንዳይደርስ ነው” የሚል የይስሙላ ዲሞክራትነት ለአገር ዲሞክራሲን አያመጣም። እንዲያውም “ልገድለው ስችል ምን አዳረቀኝ” ወደሚል እብሪት ሊለወጥ ይችላል። ከታገስከኝ እነዚህን ነጥቦች ተራ በተራ ለማብራራት እሞክራለሁ።

“ዲሞክራሲ የተሸናፊ መብት ማረጋገጫ ነው” የሚለውን ቀጥዬ ከጀርመንኛው ተርጉሜ ከምጠቅሰው ከታላቋ ሮዛ ሉክሰምቡርግ ያገኘሁት ትምህርት ነው። ከላይም ትንሽ እንደጠቆምኩት ስልጣን ይዘው ከማያውቁ ኮሙኒስቶች ጋር ዛሬም ብዙ ጠብ የለኝም። ሌኒንና ትሮትስኪ ወደዱት ጠሉት በሕዝብ የተመረጠን ፓርላማ “በቡርዧዋው አገዛዝ ስር የተደረገ፣ የወዛደሩን ፍላጎት የማያንፀባርቅ ምርጫ ውጤት ነው” በሚል ሰበብ በጠመንጃ ኃይል በትነው በወዛደሩ አምባገነንነት ስም የፓርቲያቸውን ስልጣን ማደላደል ላይ በነበሩበት ወቅት ሮዛ

ሉክሰንበር ተቃዋሚያቸው ሆነች። ይህንን ጥቅሴን ያወጣሁበትን “ስለሩስያ አብዮት” የሚል ጽሁፍ (እስር ቤት ሆና!) ጻፈች። ሙሉ ጽሁፉ ሲነበብ፣ ስልጣን ላይ ለመውጣት ወይንም ለመቆየት እገሌን እንያዘው የእገሌን ድርጅት እናቅርብ፣ እናሽሽ የሚል የዘይት ነጋዴ ስሌት ካላጠበበው፤ ለነፃነትና ለእኩልነት ስለሚደረግ ትግል ሀቁን ደርሼበታለሁ የሚል ግብዝነት ካላደደበው ብሩህ አንጎል ብቻ ሊወጣ እንደሚችል ያስታውቃል።

ካልኩት ነጥብ ጋር በቀጥታ የሚያያዘውን እንደሚከተለው ተርጉሜዋለሁ።

> **“ነፃነት ቁጥራቸው የፈለገውን ያህል በርካታ ቢሆን ለመንግስት ደጋፊዎችና ለፓርቲ አባሎች ብቻ የሚሰጥ መብት አይደለም። ነፃነት ሁልጊዜም የተለየና ተቃዋሚ ሀሳብ ያለው ወገን መብት ነው። ይህን የምለው ለፍትህና ለርትዕ ልዩና አምልኮ ባዕዳዊ ፍቅር አድሮብኝ አይደለም። የፖለቲካ ነፃነት ሕብረተሰብን የሚያድስ የሚፈውስና የሚያፀዳ ኃይል የሚሆነው፣ በዚህ ሀቅ ላይ ሲመሰረት ብቻ በመሆኑ ነው። ነፃነት የተወሰኑ ምርጥ ወገኖች ልዩ መብት (ፕሪቪሌጅ) ከሆነ የይስሙላ ነፃነት ነው የሚሆነው።”** [13]

ዲሞክራሲን ለተወሰነ ክፍል ልዩ መብት ማድረግ የሰፊውን ሕዝብ የልብ ትርታ አድማጭ ነን ባዮች መጀመሪያ ላይ ተቃዋሚዎቻቸውን፣ ከዚያም ሕዝቡን እራሱን የሚያፍኑበት ስርዓት እንደሚያመጣ ሮዛ

13. Rosa Luxemburg (1918). On the Russian Revolution. (Online Version: marxists.org. 1999. Page 33)





ገና በጥንስሱ ነቅታበት ነበር። የሰባ ዓመታት የሶሺያሊዝም ምርጫ ኮመዲ የሚያሳየውም ይህንኑ ነው። ወድቀው ከታሪክ ፊት በሀፍረት ሊሰናበቱ ሳምንት ሲቀራቸው ሁሉ 98 ከመቶ በሆነ ድምጽ ይመረጡ የነበሩት የምስራቅ አውሮፓ “ዲሞክራቶች” “ዲሞክራሲያዊ ምርጫ” የይስሙላ ያደርገው የነበረውም ይኸው ነው። 90 በመቶም በላይ ድምፅ እያገኘ በሕዝብ ዘንድ ይጠላ የነበረውን የ(ምስራቅ) ጀርመን ኮሙኒስት ፓርቲ አስመልክቶ “ሕዝቡ ሌላ ፓርቲ መምረጥ ካልቻለ ፓርቲው ሌላ ሕዝብ ይምረጣ እንግዲህ’ ብሎ ቀልዶ ነበር በርቶልድ ብሬሽት።

የፖለቲካ ነፃነት መግለጫ የተቃዋሚ መብት መረጋገጥ የሆነውን ያህል የፖለቲካ ዲሞክራሲ እንዲሰራ የተሸናፊ መብት መረጋገጥ አለበት- “አሸናፊ ሁሉንም በበላይነት የሚያጋብስ ከሆነ፣ ተሸናፊ ውልቁን የሚወጣ ከሆነ ዲሞክራሲ ዜሮ ይወጣል። አሸናፊ በአሸናፊነት ካልቆየ ተሸንፎ ሁሉንም ስለሚያጣ የአሸናፊነት ቦታውን ላለመልቀቅ ከምንም ወንጀል አይመለስም። ተሸናፊ ካላሸነፈ ለጥቅሙ መጠበቅ ዋስትና ስለሌለው በማንኛውም መንገድ የግድ ስልጣን መያዝ አለብኝ ብሎ ይነሳል:: የዲሞክራሲ “ጨዋታ” እንዲጀመር የጨዋታው ሕጎች የተሸናፊን መብት እንደሚያስጠብቁ ዋስትና መገኘት ይኖርበታል።

ከዚህ ላይ ላዩን ሲያዩት ጥልቀት ያለው የማይመስል የዲሞክራሲ ማስመዝገቢያዬ አንፃር የኢትዮጵያን ሁኔታ በምንመለከትበት ጊዜ፣ የወቅቱ የፖለቲካ ቅራኔ የዚህ የዲሞክራሲ መሰረት መታጣት ያስከተለው ጭምር መሆኑን ማየት ይቻላል።

አቶ ሐጎስ፣ እናንተ ከተሸነፍን የ15 ዓመት ትግል ከንቱ ይቀራል የሚል ተገቢ ፍርሀት አለባችሁ። በድርጅታዊ ጥንካሬና በካላሺን ብዛት የማይስተካከሉዋችሁ ተቃዋሚዎቻችሁ ደግሞ ስልጣን ካልያዝን TPLF ሲፈልገው የሚችረን "መብት" ብቻ እንጂ ዋስትና ያለው ጥቅም ማስከበሪያ የለንም የሚል ተገቢ ስጋት አለባቸው። በሌላ አነጋገር፣ በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ የሚካሄደው የፖለቲካ ሽኩቻና ትግል በአንድ በኩል እንደሁኔታው በማስፈራራት፣ በመለማመጥ፣ በመከፋፈልና በተራ ጮሌነት የበላይነታችሁን ለማጠናከር በምትሞክሩት በናንተና በሌላ በኩል ደግሞ "ለታክቲክ" የናንተን የበላይነት ተቀብለው ውስጥ ውስጡን ሌላ ሕብረቶች መፍጠር በሚሞክሩት፣ እንዲሁም ፊት ለፊት በተቃዋሚነት ወጥተው እስከ መሳሪያ ትግልም ድረስ ሊሄድ ለሚችል ተቃውሞ በሚሰናዱ ወገኖች መካከል የሚካሄድ ሽኩቻና ትግል ነው። ይህንን የናንተን የተደበቀ ምስጢር ማጋለጥ ሊባል የማይችል "ስውር" ሽኩቻ አፍ አውጥተን በስም ብንጠራው የሚከተለውን ስዕል እናገኛለን።

በይበልጥ በኤርትራ ግንባርና በናንተ ግፊት፣ ሆኖም ደግሞ በራሱም የውስጥ ቅራኔዎች ምክንያት ደርግ ሲዳከም ኢትዮጵያን "በሙሉ ነፃ ለማውጣት" በሌላ አነጋገር ወደ አዲስ አበባና ወደ ደቡብ ማምራት እንደሚቻል እስክታዩ ድረስ የትግራይ ነፃ አውጭ ነበራችሁ። የአዲስ አበባውን መንገድ ስትጀምሩ የኢትዮጵያ ነፃ አውጭ ሆናችሁ፤ ኢሕአዴግ በሉት እንጂ አዲስ አበባ ሆኖ በበላይነት የሚገዛው TPLF እንደሆነ እነማሙሽም ያውቁታል። ይህን በጠመንጃ ኃይል





ያገኛችሁትን ስልጣን በሕዝቡ 'ዲሞክራሲያዊ" ፈቃድ ልታስፀድቁት ትፈልጋላችሁ። (ይህ በአሜሪካኖች ግፊት ይሁን እናንተ ስትፈጠሩ ጀምሮ ለዲሞክራሲ በገባችሁት የማይታጠፍ "ቃል ኪዳን" ምክንያት የሁለተኛ ደረጃ ጥያቄ ነው።)

ችግሩ የሚመጣው የትግራይ ሕዝብ በሚኖርበት አካባቢ እንጂ ከዚያ ውጭ ለእናንተ በቀጥታ እንድትገዙ ዲሞክራሲያዊ ፈቃድ የሚሰጥ ሕዝብ ይኖራል ወይ የሚለው ጥያቄ ላይ ነው። አቶ ሐጎስ አስፈቅድልኝና ለምሳሌ ያህል እንሞክረው የኔ ኤጀርሳ ጎሮ በሆነው በወለጋ ካንተ ጋር አይደለም ከአቶ መለስ ዜናዊ ጋር ለምርጫ እንወዳደርና አሸንፈዋለሁ። እርግጥ እኔም ከኖርኩበት ይቅርና በእግሬ ከረገጥኩት ወደ 25 ዓመት ግድም ስለሆነኝ ለሕዝቡ አቶ መለስም እኔም እንግዳ ሳንሆንበት አንቀር ይሆናል። ሆኖም ግን፡ ቋንቋውን የምናገር የወንዙ ልጅ በመሆኔ እኔን ይመርጣል ብዬ እገምታለሁ። ወይንም የወለጋ ኦሮሞ በጣም ነቅቶ ዓለም አቀፋዊ ከመሆኑ የተነሳ ከማያውቀው ኦሮሞ ይልቅ የማያውቀውን ትግሬ ይመርጣል ካልተባለ በስተቀር። በሌሎች ብሄረሰቦች አካባቢም ከዚህ የተለየ አይመስለኝም። TPLF በኪነ ጥበቡ የማውቃትን ኢትዮጵያ ለውጧት ካልሆነ። ለማንኛውም፤ አቶ መለስ በድፍን ኢትዮጵያ የትግሬዎችና "በዘር የማያምኑ ንፁህ ኢትዮጵያውያን" ድምጽ ተደማምሮ 30 በመቶ ቸር ብንሆን 40 በመቶ ቢያገኝ ትልቅ ውጤት ነው። ስለዚህም ይህ የፊት ለፊት ውድድር የማያዋጣ መሆኑ እንኳን ለእናንተ ለነማሙሽም ስለማይሰወር፤ ብዙም ዘወር ባላለና ባልተራቀቀ ተዘዋዋሪ መንገድ የናንተን የበላይነት ለማጸደቅ

የምትከተሉት ዘዴ አለ። ይኸውም እናንተ በቀጥታ ከየብሄረሰቡ ጋር ማካሄድ የማይቻላችሁን ትግል ወደየብሄረሰቡ ማስገባት የሚል ነው። እርሱም የሚከተለውን መልክ ይይዛል፤ ወይንም እየያዘ ነው።

የናንተን የበላይነት ተቀብሎ "ትግሉ ያስገኘውን ድል ለኦሮሞ ሕዝብ ለማስከበር" በተዘጋጀው በሚደቅሳና ከተቻለ የብሄረሰቡ ተመጣጣኝ፣ አለበለዚያም ቢያንስ የናንተን የሚያክል ኃይል ተገን አድርጎ ከቻለ ተራውን የበላይነት ይዞ፣ ቢያንስ ግን "አንቱ ተብሎ በእኩልነት" ሥልጣን ለመጋራት በሚፈልገው ደቻሳ መሀል፤ በኦርኬስትራችሁ ውስጥ ሶስተኛ ረድፍ ላይ ሆኖ ፒያኖ ቢመታ በሚበቃው በማዴበና አብሮ ካልቃኘ ሙዚቃ በማይጥመው በአሰፋ ጫቦ መሀል፤ "ለጊዜው" በናንተ የበላይነት ሥር ቢሆንም ሥልጣን ቢጋራ ኤርትራም ብትሄድ የተቀረችውን "ክርስቲያን" ኢትዮጵያ አንድነትና የሶስት ሺህ ዘመን ታሪክ አስቆያለሁ በሚለው በአላምረውና አጋሜን መልሼ ተከዜን ሳላሻግር እንቅልፍ አይወስደኝም በሚለው በወሰን የለህ መሀል የጦፈ ትግል ይካሄዳል። እናንተም ሲያስፈልግ በግልጽ፣ ይበልጡን በተዘዋዋሪ ሚደቅሳን ማዴበንና አላምረውን በመደገፍ ኢትዮጵያን "ለዲሞክራሲ" ታዘጋጃላችሁ። ስሌቱ ሰምሮ ሚደቅሳ ማዴበና አላምረው በየፊናቸው ካሸነፉ አቶ መለስ 30በመቶ ወይም 40በመቶ ብቻ ሳይሆን 90በመቶ የሕዝብ ድጋፍ ያገኛል:: ከዚያም የነጆርጅ ቡሽ የደስታ መግለጫ ቴሌግራም ከተነበበ በኋላ የሚከተለው መግለጫ ይሰጣል።





**"ይህ ሰላም ወዳድ ሕዝብ የፈነጠቀለትን የዲሞክራሲ ሥራ ሊያዳፍኑበት ከውጭ የዲሞክራሲ ጠላቶች በሚያገኙት እርዳታ የልመና አቆማዳቸውን ሞልተው ሊያወናብዱት የተፈታተኑትን፤ የሰላም ዘንባባ የዘረጋላቸውን የኢሕአዴግ እጅ የነከሱትን እነደቻሳን እነአሰፋ ጫቦንና እነወሰን የለህን የታሪክ የውድቀት ማቅ በማልበስ ለረዥም ጊዜ የናፈቀውን የዲሞክራሲ ካባ ለመጎናፀፍ በቅቷል። አቶ መለስ ዜናዊ ይህን የሕዝብ አደራ ሲቀበሉ ባደረጉት ንግግር ..."**

በማዘጋጀት ላይ ያላችሁት እንደዚህ ዓይነት ቲያትር ነው። ብሄራዊ ቲያትር የሚቀርብ ቢሆን ኖሮ፣ ገና በደንብ ሳይጀምር መጨረሻው የሚያስታውቅና የማያጓጓ የቀሽም ደራሲ ቲያትር ነው በሚል ሂስ እንገላገለው ነበር። አሳሳቢ የሚያደርገው የኢትዮጵያን የፖለቲካ መድረክ ለሚቀጥለው ትራጀዲ የሚያዘጋጅ ከመዲ መሆኑ ነው።

ዋናው ጥያቄ፣ እናንተ የምታወጡትን የዲሞክራሲ ኮሶ ሕዝቡ ጠጥቶም እነደቻሳን፣ እነአሰፋ ጫቦን፣ እነወሰን የለህን ያልተፋ እንደሆነ ነው። የአዲስ አበባን ጋዜጦች ሰሞኑን ሳይ ሰፊው ሕዝብ እነደቻሳን እንዲተፋ በጣም እያሳሰባችሁት ነው። ፍጥነቱን እንዲጨምርም ትዕግስታችሁ እያለቀ መሆኑን እያስገነዘባችሁት ነው። እናንተን ሲያስነጥስ ጉንፋን የማይዘው የሕብረት አባል ሊኖራችሁ ስለማይችል ሚደቅሳዎቻችሁም "እኛ እንደነደቻሳ አይደለንም" የሚል ውትወታና ስሞታ ጀምረዋል። እነ ደቻሳም ኢትዮጵያ ውስጥ በሕዝብ ተተፍተሀል ተብሎ ላለመመታት እስካሁን ዓይነተኛ መመከቻ የሆነውን የካላሺን ኃይላቸውን ለማደለብ እየጣሩ ይመስላል። ጥያቄው ድሮውንም የኦሮሞና የትግራይ ሕዝብ

እንዴት በአንድ አገር አብሮ መኖር ይችላል አልነበረም። የአማራ፣ የኦሮሞ፣ የትግራይ...ወዘተ የፖለቲካ ኤሊት የአገሪቱን ሥልጣንና ሀብት እንዴት ቢከፋፈል ነው በሰላም አብሮ መኖር የሚችል የሚል ነበር።

ይህ በጠረጴዛ ዙሪያ ብቻ የሚፈታ ጥያቄ ከትግሬና ከኦሮሞ ንዑስ ከበርቴ ማን የበለጠ ካላሺን ያዛል ወደሚል ወደጦር ሜዳ ብቻ የሚወስድ የ"ወንድነት" ጥያቄ ተጣበ መጥቷል። ከኦሮሞው ኤሊት የተወሰነው ክፍል፣ የናንተን ያህል ካላሺን ካላሰለፍን እንደ አማራ የበላይነታችሁን ታሰፍኑብናላችሁ ብሎ ስለሚሰጋ የድርጅትና የካላሺን የበላይነታችሁ ወደዘላቂና ጠንካራ የፖለቲካ የበላይነት ሳይተላለፍ በድርጅትና በካላሺን ለመጠናከር እየተሯሯጠ ይመስላል። እናንተን "በጀግንነት" ለመስተካከል በሚያደርገው ጥረት፣ አህያውን መምታት እስኪችል ድረስ በዳውላው እየተለማመደ ነው አሉ። እናንተ ደግሞ በድርጅትና በመሳሪያ ኃይል፣ በዓለም ዐቀፍ ግንኙነት (አሜሪካ ኤርትራ ሱዳን) ከየትኛውም የኢትዮጵያ ብሄረሰብ የላቀ ሁኔታ ላይ ስለምትገኙ፣ በረዥሙ ሲታይ ግን የትግራይ ብሄረሰብ በቁጥር አነስተኛ ስለሆነና የበላይነታችሁ ከሌሎች ብሄረሰቦች አንድ ወጥ በሆነ ባህላዊና ድርጅታዊ መዋቅር ውስጥ አለመጠናከር ጋር የተያያዘ በመሆኑ፣ በተለይ የኦሮሞ ብሄረሰብ ከቁጥሩ ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ድርጅታዊና ወታደራዊ ኃይል ሳያገኝ በፊት በእንጭጩ ለመቅጨት ተነሳስታችኋል። ችግሩ ወደ ካላሺን ቆጠራ ወርዷል ያልኩትን የሚያረጋግጥ፣ ይህን የጽሁፌ መነሻ





የሆነውን የአቶ ሐጎስ "ማጋለጫ" ያገኘሁበት መጽሄት ውስጥ ሰፍሮ ይገኛል።

በአንድ ምልልስ ውስጥ ዶክተር ገብረአብ የሚባል ሰው እንደሚከተለው ተጠቅሷል።

> **"ሆኖም ብዙ ድርጅቶች ቀድሞ ያልነበራቸውን ኃይል ሰራዊታችን ነው በማለት ላይ ይገኛሉ። አንድ ብርጌድ የማይሞላ ጦር የነበራቸው ሶስትና አራት ብርጌዶች አሉን ማለት ጀምረዋል።"**

በዚህ የመጀመሪያ የካላሺን ግጥሚያ "ግማሽ ሚሊዮን ወታደሮች የበተነ ጀግና" ሰራዊት ስላላችሁ አሜሪካኖችም በናንተ በኩል ስለሚሆኑ እናንተ ታሸንፋላችሁ። ግን ብዙ ይሁን ጥቂት ግጥሚያዎችን እንጂ ጦርነቱን ማሸነፍ የምትችሉ አይመስለኝም፤ በብሄረሰቦች ስምና መሀል በሚደረግ ጦርነት መተላለቅ እንጂ መሸናነፍ አይቻልም። ከኦሮሞውም ቢሆን ሁሉም እንደተሳለቅህበት ወንድሜ "ከሱሉልታ የማያልፍ እውር" አይሆንም። "በደቡብም አሲምባ አለ" የሚል እየበረከተ ይሄዳል። የኦሮሞውን ምሁር ሁሉ አምባሳደርና ሚኒስትር አድርጋችሁ አትዘልቁትምና የሚያኮርፋችሁ እየበዛ ይሄዳል። ሰሜን ሸዋን ካለፋችሁ ወዲህ በጣም እያፈቀራችኋት የሄዳችኋት ኢትዮጵያ ጠላት ትሆንባችሁና ልታስሯት ትነሳላችሁ። በእናንተ እጅ አልባሌ ሞት ከሚሞት በደቡብ አሲምባ ሊሞት የተዘጋጀ የኦሮሞ ጀግና ይበራከታል። ለእናንተ የዲሞክራሲ ማጠናከሪያ ከአሜሪካ ሲዘንብ ከአፍጋኒስታን የተረፈ ለምሥራቅ ኦሮምያ ያካፋ ይሆናል። አሜሪካ

በናንተ በኩል ስለሆነ በምዕራብም የጋዳፊ እጅ ይደርስ ይሆናል፤ (ሱዳን ላይ ተስፋ አትጣሉ። ጋራንግን ሸጦ ኢህአፓን ማስወጣት ይቻላል፤ የጋዳፊ ሚሊዮን ካርቱም ከገባስ?)። ለማንኛውም አፍሪካ ለተጫረሰ መሳሪያ የሚሰጥ ይጠፋል ብለህ ነው አቶ ሐጎስ? እኔም አንዱን ሳምንት የአባቴን ዘመዶች አንዱን ሳምንት ደግሞ የናቴን ዘመዶች መርዶ እየሰማሁ አውሮፓ እያረርኩ እኖራለሁ። (በነገራችን ላይ ቅድም ኃይሌን በግማሽ ጎኔ ኦሮሞነቱን እካፈለዋለሁ ስል መቸም ለዛሬ የኢትዮጵያ ፖለቲካ ዘር ቆጠራ ወደድን ጠላን ወሳኝ ሆኗልና: አንዱ ጎን ምን ትሆን ብለህ ይሆናል። ካንተም የጀግንነት ማእረግ ባላገኝበት ለኢትዮጵያ ሕዝብ የነፃነት ትግል አስተዋፅኦ አደርጋለሁ ብዬ በተነሳሁበት ዘመን በመጣብኝ መዘዝ በሚገባ ሳልጦራት ፍቅሯን ሳልመልስላት እስር ቤትና ስደት መጥተው አንድ ልጅዋን ከአጠገብዋ በማጣቷ በሀዘን ያለዕድሜዋ የተለየችኝ ውድ እናቴ ያንተ ዘመድ ነበረች።)

የሆነው ሆኖ አቶ ሐጎስ የጦርነት ስዕሌን ልቀጥልና ጦር ሜዳ እግሩ ረግጦ የማያውቅ ፈሪ ስለጀግና መዋያ ሲያወራ ቢያስቅህም ታግሰህ አንብበው። የዛሬ አስር ወይም አስራአምስት ዓመት የኦሮሞ ግንባር ሰራዊት ቢሾፍቱ ሲደርስ የለንደን ሁለት ስብሰባ ይጠራል። ዳግማዊ ኮኸን "ዌል ሚስተር መለስ ለሰላምና ለመረጋጋት የሚበጀው የሚስተር ደቻሳ ወታደሮች አዲስ አበባ ሲገቡ ስለሆነ የኛ ሙሉ ድጋፍ ይኖረዋል" ይላል። አቶ መለስ ደግሞ ወዴት እንደሚሄድ አላውቅም። ብቻ የአቶ ደቻሳ ሰራዊት "ፊንፊኔ" ሲገባ፣ አቶ ድፋባቸውና አቶ ኪሮስ





"ታፍራና ተከብራ የኖረችውን የክርስቲያን ደሴት ከጋ* አገዛዝ ነፃ ለማውጣት በሰሜንም አሲምባ አለ" ብለው ረዥሙን መራራ ትግል ይያያዙታል። ውሀ ቅዳ ውሀ መልስ! ለሚሊዮኖች እልቂት ምክንያት የሚሆን የሕፃን ጨዋታ!!

ይኸውልህ አቶ ሐጎስ እንደዚህ ዓይነቱን ሁኔታ በዓይነ ሕሊናዬ እያየሁ ከአገሬ ልመክተው ባለመቻሌ ነው አቅመቢስነት እየተሰማኝ ሆደባሻ የሆንኩት። ስጋት ላይ መሆን አለብን፣ ለእፎይታ ገና አልደረስንም የምለው።

እናንተ በአሸናፊነት ለመቆየት ቆርጣችሁ ስለተነሳችሁ ከተራ ፊንታ እስከ ካላሺን ቃታ "ዲሞክራሲን" ለማምጣት የማትሞክሩት የለም። «ጀግኖቹን ፈሪ በማለት ወንጀል» ተጠያቂ ልሁንና እንዳትሸነፉ ሰግታችሁ የፈሪ አባራሪ ሆናችኋል። ተቃዋሚዎቻችሁ ደግሞ የእኩልነት ዋስትና ስለሌለ፣ ጥቅምና መብታቸውን ለማስጠበቅ የግድ እናንተን ማሸነፍ እንዳለባቸው እያመኑ ነው። እናንተን የተቃወመ ሁሉ የኢሠፓ ደጋፊ ነው ብትሉ፣ ደርግን ይህ ሁሉ ከደገፈ እንዴት እንደወደቀ መገረም ሊኖርባችሁ ነው። የይስሙላ ዲሞክረሲ፣ የይስሙላ ምርጫ ኢትዮጵያ ውስጥ ዲሞክራሲንና ሰላምን አያመጣም። የአንድን ቡድን የአንድን ብሄረሰብ የበላይነት ከእውር በማይጋርድ መጋረጃ ከአብዛኛው ሕዝብ መሸፈን አይቻልም።

ስለሆነም የዛሬ አሸናፊዎች ሆናችሁ፣ ተቃዋሚዎች "ዲሞክራሲ የሕዝብ ልዕልና ነው" ከሚል የመዝገበ ቃላት ትርጉም ምንም እርምጃ

ወደፊት መሄድ አልቻላችሁም። በሆነ መንገድ በተመረጠ ፓርላማ ውስጥ ከተለያዩ ጥቃቅን ቡድኖች ጋር ተጣምሮ 51 በመቶ ድምጽ በዚህ ዓይነት ፓርላማ ውስጥ ማግኘት ዲሞክራሲ ነው የሚል ስሌት የሰላምንና የዲሞክራሲን መንገድ አያስይዝም። በካላሽን የሕዝብ ቅቡልነት አግኝቶ ካላሺን የሌለውን ወይንም በበቂ የሌለውን በሕዝብ አስተፍቶ ምርጫ ማሸነፍ ብዙ ቦታ ታይቷል። ዲሞክራሲን ግን ሰላምን ግን አላስገኘም። ከዚህ ሕዝብ ከማታለል አልፎ እራስን ወደማታለል ከሄደ ጨዋታ ወጥታችሁ በምን መንገድ፤ በየትኞቹ ጉዳዮች ላይ አሸናፊና ተሸናፊ የማይኖርበት ሁኔታ ይፈጠራል፤ በየትኞቹ ጉዳዮች ላይ ደግሞ ተሸናፊ ውልቁን የማይወጣበት አሸናፊ የማይፈነጨበት ሁኔታ እንዲፈጠር ማን ዋስትና መስጠት አለበት ወደሚሉ የዲሞክራሲን ጎዳና የሚያስጀምሩ ውይይቶች ከተቃዋሚዎቻችሁ ጋር መጀመር መቻል አለባችሁ። ይህም ደግሞ በምን መንገድ ካላሺን ከኢትዮጵያ የውስጥ ፖለቲካ ይወጣል ከሚለው፣ ካላሺን የምትቆጥሩትን ጀግኖች ብቻ ሳይሆን በኢትዮጵያ ፖለቲካ ያገባኛል የሚልን ካላሺን አልባ ምሁር ሁሉ ጨምሮ መካሄድ ያለበት ውይይት ነው።

በምዕራብ አውሮፓ መኖር የምዕራብ ዲሞክራሲ አምላኪ አላደረገኝም። ማርክስ የበረዘው ትምህርቴ ብቻ ሳይሆን፣ የዕለት ተዕለት ኑሮዬም የዚህን ዲሞክራሲ ውስንነትና ቅራኔዎች ያሳየኛል። ብዙው እኩልነት የይስሙላ ነው። ማህበራዊ ፍትህ የተዛባ ነው:: ቢሆንም ግን፣ ይህ ዲሞክራሲ ተፃራሪ ጥቅሞችን ተቻችለው እንዲኖሩ ማድረግ የተቃራኒ ወገኖች የራሳቸው የጋራ ሀላፊነት ነው በሚል መሰረት ላይ ከቆመ





ወዲህ የፖለቲካ ግጭቶች ፍጅትን አያስከትሉም። የኢኮኖሚና ባህላዊ መበላለጦችን ከፖለቲካ እኩልነት ጋር በማጣጣሙ ዓይን ያወጣ የፖለቲካ ጭቆና የለም። የስርዓቱ ሰባኪዎች በምዕራብ ዲሞክራሲ ከሰፈነ ዘመን የሌለው ያስመስላሉ እንጂ በነሱም አገር ከብዙ ፍጅት በኋላ የተሸናፊውን መብት በማስጠበቅ ተሸናፊው ስርዓቱን ለመለወጥ የሚነሳበት ምክንያት እንዳይኖረው ካደረጉ በኋላ በአባቶቻችን እድሜ ነው ዲሞክራሲ የዛሬ መልኩን የያዘው። ለማንኛውም እዚህ ይህን ያነሳሁት ስለምዕራብ ዲሞክራሲ በሰፊው ለማውራት አይደለም። ምናልባት ወደፊት በካላሺን ሳይሆን በብእር ለዲሞክራሲ አስተዋፅኦ ለማድረግ የሚፈልጉ ‘‘ምን ዓይነት ዲሞክራሲ በኢትዮጵያ” በሚል ውይይት ሲያደርጉ በዚሁ ጉዳይ የማቀርበው አስተዋፅኦ ይኖረኝ ይሆናል። አሁን ያነሳሁት ከምዕራብ ዲሞክራሲ “የሚያስቀናኝን” አንድ ነገር ጠቅሼ ለማለፍ ነው። መቼ ይሆን ይህን አገሬ የማየው የሚያሰኘኝ፣ ምርጫ በተደረገ ቁጥር የተሸናፊው ፓርቲ መሪ አሸናፊውን እንኳን ደስ አለህ ብሎ ይህን ያንን ስለተሳሳትን ነው ያሸነፍከን ቆይ የዛሬ አራት ዓመት በሌላ ምርጫ እንገናኝ ብሎ “ዝቶበት” ሲለያዩ ሳይ ነው።

በኔ ግምት የሳንዲኒስቶች ታላቅ ሰዓት ሶሞዛን አሸንፈው ማናግዋ የገቡ እለት ብቻ አይደለም። አሳዛኙ፣ ነገር ግን እኩልም ታላቁ ሰዓታቸው፣ ጉልበተኛው የአሜሪካ መንግስት የተበተበው ሴራ ያንበረከከው የኒካራግዋ ሕዝብ፣ ለናፈቀው ሰላም ሲል የሚወደውን ፓርቲ ትቶ የሬጋን ምልምል ቻሞሮን ሲመርጥ፣ ሕዝቡ ጦርነት በቃኝ ማለቱ መሆኑን በማክበር ሥልጣን በሰላም ያስረከቡ ዕለት ጭምር

ነው። ይህንን ሰላማዊ የሥልጣን ሽግግርም ያስቻለው አስቀድሞ እነሱን መልሶ ወደ ኒካራግዋ አሲምባ የሚመልስ ሁኔታ ስለተወገደ ነው።

የዚህ ምሳሌዬ ዓላማ እናንተን ለሳንዲኒስቶች እጣ ተዘጋጁ ለማለት አይደለም። እንድትሰፉ እንጂ እንድትተኩ አልፈልግም። በትግሬ የበላይነት ሰላም ሊመጣ የማይችለውን ያህል፡ ትግሬን የሚያዳክም፣ የሚያሸንፍ፣ የሚጥል ወዘተ ኃይልም ለጦርነት ብቻ ነው የሚጋብዝ። መለስ ዜናዊ እንደትግሬ ድርጅት መሪ በዚህ ሰላምና ዲሞክራሲ ፍለጋ ውስጥ ትልቅ ሚና ከሚገባቸው መሪዎች አንዱ ነው። ነገር የሚያበላሸው የድፍን ኢትዮጵያ መሪ ነኝ ወይም ልሁን ሲል ነው። ትግሬ ያልሆኑ የኢትዮጵያ ብሄረሰቦች ሁሉ ደርግን ጣልክልን በሚል ውለታ ለመክፈል ብለው አንድን ትግሬ በመሪነት ይቀበላሉ ብዬ አልገምትም። (የውለታ ነገር ከተነሳ ቸርችል ከዋነኛ የሂትለር አሸናፊዎች አንዱ ስለሆነ፣ ልክ ጦርነቱ እንዳለቀ በተደረገው ምርጫ ሕዝቡ ለቸርችል ይህን ውለታ ይቆጥርለታል ተብሎ ተጠብቆ ነበር። ተቃዋሚው የሌበር ፓርቲ አሸነፈ። ቸርችልም በሆዱ ውለታ ቢስ ሕዝብ ሳይል አልቀረም። እናንተ ግን የኢትዮጵያ ሕዝብ ውለታውን ካልከፈልኩ ብሎ እንደሚያስቸግራችሁ እየለፈፋችሁ ነው።)

እኔ የሕዝቡን ለእናንተ ውለታ ለመክፈል ዝግጁነት እጠራጠራለሁ የምለው ስለኢትዮጵያ የብሄረሰቦች ቅራኔ አውቃለሁ ብዬ ከምገምተው፣ ከኢትዮጵያ በወሬ ከምሰማውና እዚህ ውጭ ደግሞ በዓይኔ ከማየው ተነስቼ ነው። እዚህ ውጭ ትግሬ ሆኖ እናንተን የሚቃወምና





ትግሬ ሳይሆን እናንተን የሚደግፍ ለማግኘት እግር እስኪነቃ መዞር ያስፈልጋል። (አዲስ አበባን እንደያዛችሁ እናንተን የሚደግፉ ሺህ ያህል ሰዎች ቦን ሰልፍ ወጥተው ነበር የሚባል ወሬ ሰማሁና እዚያው አጠገብ ለሚኖር ጓደኛዬ ይህ ሁሉ ደጋፊ ከየት መጣ ብዬ ለመጠየቅ ደወልኩለት። የቱርክ ዓለም ዐቀፋዊ ኮሙኒስቶች ነበሩ አብዛኞቹ ብሎ የበተኑትን ወረቀት ላከልኝ። ከዓለም ወዛደሮች ግንባር ቀደም ፓርቲዎች አንዱ በሆነው በትግራይ ኮሙኒስቶች ፓርቲ መሪነት የኢትዮጵያ ሕዝብ የሶቭየትን ዘመናዊ ከላሽነትና የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝምን ድባቅ መትቶ፣ ሶሺያሊዝም አልቆለታል የሚለውን የፀረ ኮሙኒስቶች ፕሮፓጋንዳ ውድቅ በማድረግ ስለአሸነፈ ደስታቸውን ለመግለፅ መሰለፋቸውን የሚያበስር ወረቀት ነበር። ትልቅ አለመግባባት ብዬ ሳቅሁ።)

አቶ ሐጎስ፣ እኔ ዋነኛ የሚባሉት (ከቁጥራቸው አንፃር) የኢትዮጵያ ብሄረሰቦች በምን መንገድ የአገሪቱን ሀብትና ማዕከላዊ ሥልጣን ቢከፋፈሉ ሰላም ሊወርድ እንደሚችል አላውቅም። የቁጥር መበላለጥ የመብትን መበላለጥ በማያስከትልበት መንገድ ተግባብተው መኖር አለባቸው። የአገሪቷም ሀብት ሆነ በልመና የሚገኘው በዚህ ትብብር ላይ በተመረኮዘ የሰለጠነ መንገድ የየብሄረሰቡ አባሎች በማንኪያ የሚቋደሱት “ገንፎ” እንዲሆን ነው ምኞቴ። በማዕከላዊ ሥልጣን ውስጥ የሚኖረውን የአንድ ብሄረሰብ ክብደት የካላሺን ብዛት የሚወስን ከሆነ፤ የአገሪቱ ሀብት የየብሄረሰቡ ንዑስ ከበርቴ በካላሺን ሳንጃ ቆርጦ የሚከፋፈለው “ድፎ ዳቦ” እስከሆነ ድረስ ሰላምና ዲሞክራሲ ሊኖር

አይችልም። ዋናው የሥልጣን ክብደት በካላሺን ኃይል ተደግፎ የአንዱን ብሄረሰብ አባል የዚህ ምኒስትር፣ የዛኛውን የዚያ ምኒስትር ማድረግ ዓይን እያየ መሸዋወድ እንጂ የትም አያደርስም። የአቶ አማኑኤል በአንድ ወቅት የአገሪቷ ሁለተኛ ሰው መሆን ምን ለውጥ አመጣ? የፍስሀ ደስታ “ምክትል ርዕሰ ብሄር” መሆንስ? ዛሬም፣ በትግሬ የበላይነት ስር ከፍተኛ የሀላፊነት ቦታ ያለው ኦሮሞ በኦሮሞ ምሁራን ዘንድ ከዝቅተኛ የትግሬዎች ጎበናነት ስያሜ አያልፍም። ስለሆነም፤ ምናልባት ማዕከላዊውን ሥልጣን ለካላሺን ከመልቀቅ፣ እንደማርያም ፅዋ ማዞሩ ያዋጣ ይሆኖል። የማርያም ፅዋ በየወሩ ስለሚዞር ከማህበርተኞቹ ውስጥ የታሪክ አጋጣሚ ሆኖ ወይንም የምዕመኑን ቅቡልነት በማግኘት “ይህን ፅዋ በናንተ ስም የማስተዳድር እኔ ነኝ፤ አንቺ ጃንጥላ ያዥ ነሽ፤ አንተ ድፎ ዳቦ ተሸካሚ ነህ” የሚል ስለሌለ እነእቴቴ በእኩልነት ማሪያማቸውን ሲያመልኩ ነው የኖሩት።

አቶ ሐጎስ በዚህ ክፍል ያደረግሁት የትንቢት ሙከራ ሁሉ ስጋቴን ለመግለፅ እንጂ እነዚህን ሁኔታዎች ለአገሬ በመመኘት እንዳልሆነ እንኳን ሌላ አንባቢ አንተም ተረድተህልኝ ይሆናል። በዚህ ለኔ ጽሁፍ መነሻ በሆነኝ መጽሄታችሁ እንደምትሞክሩት እነዚህ ሁሉ የስጋት ምንጮች ለእናንተ በጎ የማያስቡ ሰዎች ምኞት መሆናቸውን በመለፈፍ መፍትሄ ልታገኙላቸው አትችሉም። የካላሺኑን ሙከራ ትታችሁ በድርጊት ግምቶቹን ፉርሽ አድርጋችሁ “ውሸታም” ብታደርጉኝ ግን የኔን ያህል ደስተኛ አታገኝም።





በነዚህ ትንቢታዊ ግምቶቼ ውስጥ ከመለስ ዜናዊና ከአሰፋ ጫቦ በስተቀር የተቀሩት ስሞች የኔው ፈጠራ ናቸው። ምናልባት ስለነዚህ ሁለት የኢትዮጵያ ፖለቲከኞች በግል አንስቼ የማስበውን ብገልፅ ስልጣን ላይ ያላችሁትም ሆናችሁ ተቃዋሚዎች ስላለባችሁ ሀላፊነት የሚሰማኝን ለማስቀመጥ ይረዳኝ ይሆናል።

አቶ መለስን ለመውደድም ለመጥላትም ምክንያት የለኝም። ስሙንም ከነመፈጠሩም የሰማሁት አዲስ አበባ ልትገቡ ሁለት ወር ሲቀራችሁ ነው። እንድፈራው ያደረገኝ ባለፈው ሀምሌ ይሁን ነሐሴ ወር በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ ያነበብኩት መልሱ ነው። “ኢሕአዴግ ግራ ጉንጩን ሲመቱት ቀኙን የመስጠት ልምድ የለውም፤ ኢሕአዴግ ሁሉንም እንደአመጣጡ የመመለስ ልምድ ነው ያለው” የሚል ፉከራ ነበር። መንግስቱ ኃይለማርያም “ለምሳ ያሰቡኝን ለቁርስ አደርጋቸዋለሁ” ያለውን ትዝ አሰኘኝ። በአዲስ አበባ የተደረገውን ለውጥ “ታሪካዊ” ከሚያደርጉት ነገሮች አንዱ የጅማው ዱርዬ በአድዋው ጮሌ መተካቱ ሆኖ ተሰማኝ።[14] አገሬን የሚያስፈልጋት፣ ከፈለግህ ሶስተኛውንም ጉንጬን ጠፍጥፍ እንጂ አትፋጃትም ብሎ ከቡድኖች፤ ከብሄረሰቦች፣ ከውስን ታክቲካዊ ግቦች ከፍ ብሎ፤ ባጭሩ በመንደር ደረጃ የሰፈር አዛውንት የሚኖረውን ሚና በአገር ደረጃ ለመጫወት የሚሞክር ገላጋይ ሆኖ ሳለ በመጀመሪያው ረድፍ ላይ ሆኖ የሚያዋጋ ጀግና መሪ እንደመጣባት ገባኝ።

14. ጅማ ተምሬአለሁ የሚሉትን ኮ/ል መንግሥቱ ኃይለ ማርያምንና የአድዋውን ልጅ ጠ/ሚ መለስ ዜናዊ ለማለት ነው።

አቶ አሰፋን ከልጅነቴም ጀምሮ በመጠኑ አውቀዋለሁ። እርሱም ከኔ የበለጠ ለጭቁኑ የሚቀርብ የለም ስለሚል እኔም መኢሶን በዚህ ጉዳይ ከማንም አያንስም ባይ ስለሆንኩ የቅርብ የፖለቲካ ትውውቅ የለንም። “ዲሞክራሲያዊ” ሸንጎአችሁ ውስጥ ትንሽም የተቃውሞ ድምፅ የርሱ ስለነበረ፣ የአቶ አሰፋ ተቃውሞ ሳይሆን የናንተን ቅቡልነት የማግኘት ፍጥነት ነበር ያደነቅሁት። ከዚያም እሱ እናንተ ላይ ያለው ተቃውሞ እየጨመረ ሲሄድ፣ እናንተም እርሱን በጣም “ማጋለጥ” እንደጀመራችሁ እሰማ ነበር። በጀርመን ያለፈ ጊዜ ንግግሮቹን አልሰማሁም፤ የተበተኑ ፅሁፎቹን አንብቤአለሁ። በግል የደረሱበትም ጉዳዮች አሉበት። የፖለቲካ ተቃውሞዎቹን በሚመለከት ለመደገፍ ችግር አልነበረብኝም:: ችግር ያለኝ በተለይ በብሄረ ሰብ ጉዳይ ከናንተ ጋር የተቃረነ ከማን ጋር ህብረት ይፈጥራል የሚለው ጥያቄ ላይ ነው። የኢትዮጵያ ብሄረሰቦች ሁሉ ተባብረው የሚኖሩባት ኢትዮጵያ ብቻ ነች ሰላም የሚኖርባት። ማንኛውም ሁለት ወይንም ሶስት ብሄረሰብ በአንድ ወይንም ሁለት ሌሎች ብሄረሰቦች ላይ የሚያደርጉት ህብረት ግጭቶች ጦርነቶች የሚጋብዝ ህብረት ነው። ከጭቁን ብሄረሰቦች ጋር አማራን ማዳከም ወይንም ደግሞ ከአማራ ጋር ትግሬን ማዳከም፣ ወይንም ከአማራ ጋር ኦሮሞን ማዳከም ወዘተ የሚሉ ታክቲኮች ወደሰላም አይወስዱንም። የትግሬን የበላይነት ለመቃወም ተብሎ የሚቋቋምን የማንኛቸውንም ሁለት ብሄሮች የጋራ ግንባር መቃወም፣ የትግሬን የበላይነት ለማጠናከር TPLF ከማንኛውም ብሄር ጋር የሚያደርገውን





የጋራ ግንባር መቃወም፤ በዚህ መሰረት ላይ ብቻ ነው ለብሄረሰቦች ችግር ሰላማዊ መፍትሄ ማግኘት የሚቻለው።

እዚህ ውጭ ካሉ ደጋፊዎቻችሁ እንደምሰማው ይህን ያህልም ዲሞክራሲ የፈቀዳችሁት እናንተ በመሆናችሁ እንጂ ሥልጣን በጉልበት እጃችሁ ያስገባችሁት ንብረታችሁ ነው። ርዕሰ ብሄራችሁም ከነመስፍን ወልደማርያም ጋር ባደረገው “ክርክር” ያለው ብዙ ከዚህ የሚርቅ አይደለም። የያዛችሁትን ስልጣን እንደፈውዳሉ ኃይለ ሥላሴ በግል ንብረትነት ስለምታዩት እንደእርሱም ልትጠቀሙበት እየሞከራችሁ ነው። ኃይለ ሥላሴ “መልካም ፈቃዱ ሆኖ” አርባ ሀምሳ ቀላድ ላይ ፊታውራሪ ያደርግ እንደነበር ሁሉ እናንተም ሶስት ወይም አራት መቀመጫ ትሰጣላችሁ። ኃይለ ሥላሴ በከፋፍለህና አቻችለህ ግዛ ፖሊሲው እገሌን ይሾም እገሌን ይሽር ነበር። እናንተም ባንድ ወቅት “መልካም ፈቃዳችሁ” ሆኖ አቶ አሰፋን የጋሞ ሕዝብ ተወካይ አድርጋችሁ ሾማችሁት:: በሌላ ወቅት ደግሞ አልመች ስላለ የጋሞ ሕዝብ እራሱ “እንዲተፋው” አስደረጋችሁ።እዚህ ላይ አሰፋ ጫበን መብት የመንሳት መብት የላችሁም ብቻ አይደለም የምለው። ከአሰፋ ጫቦ ጋር መተባበር የናንተ መልካም ፈቃድ ጉዳይ ሳይሆን ለኢትዮጵያ ሰላምና ዲሞክራሲ አስተዋፅኦ ማድረግ ከፈለጋችሁ ግዴታችሁም ጭምር ነው።

## 2. ዲሞክራሲና የጀግንነት መዘዝ

አሁን ደግሞ "ዲሞክራሲ የፈሪዎች ስርዓት ነው" ወደሚለው ነጥቤ ልግባ። ይህንኑ አባባል በሌላ መልክ ባስቀምጠው፣ ዲሞክራሲ ሰው ለእምነቱ ሲል ሆነ በእምነቱ ምክንያት የማይሞትበት ስርዓት ነው ማለት ነው። አቶ ሐጎስ እንግዲህ ጀግና ነህ፤ ኃይሌን ልትሳለቅበት የተነሳኸውና ባንተው አባባል "አልባሌ" ሰው ያደረገብህ በገደሉት መርማሪዎች ፊት እውነቷን ለመናገር ያንዲት ቅፅበት "ወኔ" በማጣቱ ነው። በእምነት ምክንያት ከሚገድል የፖለቲካ ስርዓት እኩል ለእምነቱ ሲል መሞት ፈራ የምትለውን ነው የምታወግዘው። ይህ የምትጠቅሰው የታሪክ "መረጃ" የኃይሌን ወኔ ቢስነት ያሳያል ቢባልልህ እንኳ ይህ ቃል በምን ሁኔታ እንደተወሰደ ላንድ አፍታ ቆም ብለህ ለማሰብ ሞክረሀል? ስታሊን "በታላቁ መሪ በስታሊን ላይ በማመጼ ይቅርታ" እያስባለ ስለገደላቸው ስለነቡካሪን ቃል አወሳሰድ ሰምተህ ታውቃለህ? በፈሪነታቸው ስቀህባቸው አለፍክ ወይስ የስታሊን ዘዴ ዘገነነህ? ቡካሪን ከተገደለ ከሀምሳ ዓመታት በኋላ ሚስቱ ያኔ የጻፈላትንና እንደምንም እንዲደርሳት ያደረገውን የመሰናበቻ ደብዳቤ የስታሊን ነፍሰ ገዳዮች እንዳያገኙባት ይዘቱን ሸምድዳ ካቃጠለችው በኋላ፣ እንዳትረሳው እነዚህን ሁሉ ዓመታት እንደዳዊት እያነበነበችው ከርማ በቅርቡ ያሳተመችውን ስታነብ አላሳዘነህም? ጀግና ስለሆንክ የማይገቡህ ጥያቄዎች ናቸው። ("ገ" ጠብቆም ላልቶም።)





ገዳዮቹ ፊት ስለኃይሌ "ወኔቢስነት" ስታወራ ይህን "ማስረጃ" ያወረሱህን ገዳዮች አስታወስከኝ። ይህ ቃል የተወሰደው ዋነኛው የመግረፊያና የመግደያ ማዕከል በነበረው ደርግ ጽ/ቤት በሚገኘው እስር ቤት ውስጥ ነበር። ሁለት ወር ያህል እዚያ በቆየንበት ወቅት ብዙዎች ሊገደሉ ሲወሰዱ፣ ተገርፈው ሲመለሱ ብዙ ጊዜ እንሰማ አንዳንዴም እናይ ነበር። እኛም ተራ ጠባቂዎች ነበርን። ከሁለቴም ሶስቴ ቃል ለመስጠት ወይንም የሆነ ጥያቄ ለመመለስ ገራፊዎች ቢሮ ተወስጄ እነተኮላና እነካሳሁን[15] ከግድያ ወይንም ከግርፊያ መልስ እርስ በርሳቸው ሲያወሩ ሰምቼ አውቃለሁ። የcowboy ፊልም አይተው የወጡ ነበር የሚመስለው። "ወንድ ነበረች፣ አየሀት ውሀ ስጡኝ እንጂ ሌላ ሳትተነፍስ ሄደች" እያሉ "በጀግንነት" ለሞተ አድናቆታቸውን ሲገልፁ፤ "አላየህም እንዴ አስታወከኮ" እያሉ ሲስቁ ሰምቻለሁ። እስከዛሬ ይዘገንነኛል። ስለነተኮላ ሳቅ ኃይሌም አንዴ ያጫወተን ትዝ አለኝ። ይህ አንተ እጅ የገባ ቃሉ ከተወሰደና ወደ አራተኛ ክፍለ ጦር ከተዛወርን ከሁለት ሶስት ወሮች በኋላ ኃይሌን ወስደው ገርፈውት ነበር። መጀመሪያ እንደተያዝን ከአምስታችን አንዳችንም አልተገረፍንም ነበር። ይህንኑ ለማጣጣት ነው መሰለኝ ሁለቱ የእግሩ አውራ ጣቶች ተበጥሰው ሊወድቁ ትንሽ እስኪቀራቸው ነበር የተለተሉት። ኃይሌም በዚያች መከፈስ በማታውቅ አንደበቱ ስለግርፊያው ሲያወራን በጣም ያማል፤እንዳትነቃነቅ በእጅ እንዳትከላከል እጅህ ታስሯል፤ የማደርገው ሲጠፋኝ ኧረ በእግዚአብሄር ተውኝ አልኳቸውና አንተ አይዲያሊስት

15. ካሣሁን ደምሴ ደርግ ጽ/ቤት የነበረ በጭካኔውና ሰው በማንገላታት ይታወቅ የነበረ መርማሪ ሲሆን፣ ኢሕአዴግ ባቋቋመው ፍርድ ቤት በሌለበት የሞት ፍርድ ተፈርዶበታል።

ነህ ለካ ብለው እየሳቁ ግርፊያቸውን ቀጠሉ” ብሎን ነበር። ያኔ ኃይሌ በሕይወት ከኛ ጋር ስለነበረ፣ ግርፊያውን ረስተን በገራፊዎቹ ድንቁርና ሳቅን። በደንቆሮነታቸው የሳቅንባቸው በጨካኝነታቸው ኃይሌን ገደሉት። እነሱ በገደሉት የሚሳለቅ ተካቸው።

እነ ተኮላ በሚገድሉበትና በሚገርፉበት ቦታ ብቻ አይደለም በእጃቸው በገባ፣ እራሱን ሊከላከል በማይችል ሰው ላይ የሚሳለቁት። ከብርሀነ መስቀል ረዳ የወሰዱትንም ቃል “ለምሁር” አለቆቻቸው ሰጥተው፣ እነርሱም የብርሀነ መስቀልን በሕዝብ መተፋትና “ለፈስፋሳነት” ለማጋለጥ አውጥተውት ነበር። (የታሪክ ምፀት ሆኖ ኃይሌና ብርሀነ መስቀል በአንድ አስገዳይ እጅ በአንድ ሰሞን ነበር የሞቱት)።

አቶ ሐጎስ፣ ለኃይሌ ወኔቢስነት ማረጋገጫህ “እንኳንስ እንደመኢሶን ያለው ለጋ ድርጅት ይቅርና የረዥም ጊዜ ልምድ ያላቸው ኮሙኒስት ፓርቲዎችም (…) የፖለቲካ ስህተቶችን በማድረጋቸው ከፍተኛ ውድቀት ደርሶባቸዋል። ምናልባት የመኢሶንን ሁኔታ ከነዚህ ፓርቲዎች የሚለየው እነሱ በፋሺስታዊ ጁንታዎች እጅ ሲወድቁ መኢሶን ግን በማርክሲዝም ሌኒኒዝም በሚያምን መንግስት እጅ ወድቋል። ስለዚህም በኔ ግምት ከእነዚህ የተሻለ እድል ያጋጥመዋል ብዬ አምናለሁ” የሚለው ነው። የኃይሌ ቃል ነው ብዬ በእርግጠኛነት ልመሰክር ባልችልም ሊሆን ይችላል ብዬ እቀበለዋለሁ።

ጆርጅ ቡሽ ሰሜን ሸዋ ስትደርሱ ባያስጥላችሁ ኖሮ ዋናው ክስህ ለኛ የሚገባንን የማርክሲዝም ሌኒኒዝም ካባ ለደርግ አለበሰ ይሆን ነበር።





እንግዲህ ኃይሌ ይህን ያለው ለታክቲክ ብሎ ነው ብለህ አንተም ታምናለህ። አልበሌ ሊያስብለው የሚገባ ደርግን ማርክሲስት ሌኒኒስት የማለት አሮጌ ታክቲኩን ከመቃብር ለመውጣት ስለተጠቀመበት ነው ትላለህና።

ይህን አንተ እጅ የገባውን ቃል ሲሰጥ ኃይሌ ከኛ የበለጠ መርማሪዎች ጋ ይቆይ ስለነበረ ‘’ምን እያደረግህ ነው” ስንለው የሰፊው ሕዝብ ድምፅን ቁጥር 60 እና 61 እየደገምኩላቸው ነው ይለን ነበር። (ቁጥሮቹን ልሳሳት እችላለሁ፤ አንደኛው ስለመኢሶን ታሪክ፣ አንደኛው ደግሞ ስለመኢሶን የትግል ስልት ለውጥ የተፃፉ ነበሩ።) ለማንኛውም ስለመኢሶን ሕቡዕ መግባት የወጣው የሰፊው ሕዝብ ድምፅ በጣም ለዘብ ባለ ቋንቋ የተፃፈ እንደነበር ዛሬም ትዝ ይለኛል። ይህም የሆነው መኢሶን ደንፊ ጽሁፎች አውጥቶ ስለማያውቅ ብቻ አይደለም። መኢሶን ሕቡዕ ለመግባት ሲወስን የአገሪቱ የፖለቲካ ሁኔታ ለመኢሶን ምቹ እንዳልነበረ፣ (በተለይ በሱማሌ ወረራ ምክንያት)፤ ድርጅታዊ ዝግጅቱ ገና በቂ እንዳልነበረ፣ (የትጥቁንማ ጥያቄ አናንሳው!)፤ ብዙ የተጋለጡ አባሎቹ ገና ሕጋዊ መድረክ ላይ እንደነበሩ ለሁላችንም ግልፅ ነበር። ስለዚህም መኢሶን ከደርግ ጋር ያለውን ልዩነቶች ሳይሸፍን ቅራኔዎቹን ግን ሳያጎላ ለማቅረብ የተገደደበት ሁኔታ ነበር። እርምጃው እራሱ፣ የትግል ስልት ለውጥ” የሚል አሻሚ ስያሜ ማግኘቱ ከዚህ የመጣ ይመስለኛል። ስለሆነም ይህ የተጠቀሰው የኃይሌ አባባል ኃይሌ ለራሱ ሕይወት ፈርቶ የወተወተበት ሳይሆን አንድ ድርጅት ልክ ይሁን

ስህተት የኢትዮጵያን የፖለቲካ ሁኔታ ገምግሞ ለጊዜው ልከተለው ይገባል ብሎ የነደፈው ታክቲክ ውጤት ነው።

ኃይሌ ደግሞ ከድርጅቱ ጋር በአንድ አይን ስለሚታይ፣ ይህን የድርጅቱን የታክቲክ ምርጫ ብቻ ሳይሆን "በፊዲስትነት" ደርግ እጅ ለወደቁ ብዙ ወጣቶች፣ በመኢሶንነት ተጋልጠው ገና ሕጋዊ መድረክ ላይ ላሉ ሲል ከርሱ የተሻለ እድል እንዲገጥማቸው "ለአንዲት ቅጽበት" የሚያምነውን አለመናገር የሚከብደው ሰው አልነበረም። ከታች እንደምመለስበት ኃይሌ ይህን ቃል ሲሰጥ እራሱ በሕይወት እንደማይተርፍ ያውቀው ነበር። እንኳን የአንድን ድርጅት መሪ፣ "ወረቀት በተንክ" ብሎ የሚገድል መንግስት እጅ ሆኖ የግል ሕይወትን ለማትረፍ ምንም ማድረግ እንደማይቻል ሳይረዳ ይቀራል ብለህ ነው? እንኳን እሱ ወዳጅና ጠላት የአንድ ንቅናቄ መሪ ያደረጉት ይቅርና እኔም በዚያን ቃል በምንሰጥበት ወቅት ሞት እንደማይቀርልን አምን ነበር። እነተኮላ ምን ትጠቅማለች ብለው ጥለዋት ካልሆነ የኔንም ቃል አብረሀ ወርሰሀልና ብታያት የሌላን ሰው እድል ስለማትነካ በኔና በተኮላ መሀል ያለቀች ጉዳይ ነች። ስለፍርሀትም ስለጀግንነትም ምንም ነገር አታገኝባትም "ፋሺስት ደርግ" ብልም ኖሮ፣ ተጨማሪ የተኮላ ጥፊ እንጂ ተመዝግባ ዛሬ ካንተ "ጀግና" የሚል ሹመት የምታሰጠኝ አትሆንም ነበር። ደርግ ሆይ ማረኝ ለማለትም አንበሳ ፊት ተወርውሮ "ጋሽ አንበሳ አትብላኝ" ብሎ የመለመን ያህል ይሆንብኝ ነበር። (ሟች ነው እንጂ ፈሪ ገዳይ አንበሳ ነው አይደል አቶ ሐጎስ?)





ለማንኛውም አቶ ሐጎስ፣ የኃይሌን ጅግንነት ለመመስከር አልተነሳሁም። ከፈለግህ ኃይሌ የሸፈተው 15 ቀን ብቻ ስለሆነ ያንተ ደግሞ ምናልባት 15 ዓመቶች ስለሆነ፣ አንተ ከኃይሌ [(15x365)-15] ጊዜ የበለጠ ጀግና ነህ፤ ደስ ይበልህ። በገዳይ ፊት ጀግንነትህን ለማስመስከር የምትገደድበት ሁኔታ እንዳይመጣብህ፣ እንዲሁ በጀግንነትህ እንደፎከርክ እንድትኖር እመኝልሀለሁ። ለአገሬ ደግሞ መኢሶኖች ሆኑ ኦሮሞዎች እጅህ ገብተው ቅፅበታዊ ወኔ አጡ ብለህ ልትሳለቅባቸው የምትችልበት ሁኔታ እንዳይመጣባት እመኝላታለሁ።

እያንዳንዱ ሰው በየራሱ መንገድ እንደሚኖር ሁሉ ከሞትም ጋር በየራሱ መንገድ የሚፋጠጥ ይመስለኛል። ሞት፣ ሼክስፒር በሐምሌት አንደበት እንዳለው የሄደ መንገደኛ ተመልሶ ያልመጣበት አገር ስለሆነ "ስትሞት እንዴት ነበር" ብሎ መጠየቅ አይቻልም። ኃይሌ ሲሞት "መቃብሩ አፋፍ ላይ ሆኖ ቅፅበታዊ ወኔ ጎድሎት እንደሆነ አላውቅም። እየፎከረ ሊሞት የሚችል ሰው እንዳልሆነ አውቃለሁ። ከፉከራ ጋር አይተዋወቅም። ተለማምጦ የግል ሕይወቱን ለማትረፍ የሚሞክር ሰውም አይመስለኝም። ይህንንም አንተ እጅ የገባው ቃሉን በሰጠበት ወቅትና ከዚያም በፊት እንደምንገደል መቶ በመቶ እርግጠኛ ሆነን አብረን ያሳለፍናቸው ቀኖች ስለነበሩ ካየሁት ልመሰክር እችላለሁ። ጀግናም ሳይሆን በሁኔታዎች አስገዳጅነት ሊሞት የተገደደና በዚሁ ምክንያት ሞትን የተቀበለ ሰው ሊሰማው የሚችለውን በራሴም ደርሶ ስለማውቀው አንተም ለጀግኖች ወዳጆችህ ማስደሰቻ እንደኮሜዲ ያቀረብከውን የታሪካችን አንድ ምዕራፍ ትንሽ ላሟላልህና በደንብ ሳቁ።

ከሞላ ጎደል አንተ በጠቀስከው የኃይሌ ቃል ውስጥ እንደሰፈረው ነው የተያዝነው። ከዚያ በፊት የደርግ ወታደሮች እጅ ሳንገባ አዲስ አበባ ለመድረስ ያለን ዕድል እየጠበበ ሲመጣ፣ ምን እናድርግ ብለን ብዙ ጊዜ እንነጋገር ነበር። ኃይሌ አንዴ እራሳችንን እንግደል የሚል ሀሳብ አቅርቦ ነበር። "እራሳችንን ከምንገድል ደርግ ቢገድለን ይሻላል" በሚል በመጀመሪያ ይህንን ሀሳብ የተቃወምኩት እኔ ነበርኩ። በሕይወት እንተርፋለን የሚል ግምት ኖሮኝ ሳይሆን ያኔ ሙሉ በሙሉ የፖለቲካ ትግል ውስጥ ስለነበርኩ ኖረን በሕይወታችን ለአብዮት አስተዋፅዖ ማድረግ ካቃተን ሬሳችን እንኳ ትንሽ ፖለቲካ እንዲሰራ በማሰብ ነበር። የደርግ ወታደሮች እጅ ስንገባም የጠበቅነው ስለደረሰ ብዙም አልተደናገጥንም፤ እንደሚገድሉን እርግጠኞች ነበርን። ከአንደኛ ክፍለጦር የሚወስዱን ወታደሮች እስኪመጡ ኬላው ላይ በቁጥጥር ሥር በነበርንበት ጊዜ ነው ገና ሁለት ዓመት አብረን እንደምንቆይ ስላላወቅሁ፣ የኃይሌ የመጨረሻ ቃል የመሰለኝን የሰማሁት። "ዌል የተቻለንን ሞክረናል እንግዲህ" የምትል ተስፋ መቁረጥን የምታሰማ ቃል ነበረች።

ከዚያም ደስታ፤ ሀዘን፣ ቁጣ የማይነበብበት ዓይናቸው ሰው ላይ ሲያርፍ ሰው በልተው የሚያድሩ የሚያስመስላቸው ቅልብ ወታደሮች ደርሰው በነፍስ ወከፍ አንዳንድ ታጣፊ ካላሺን ደግነውብን መኪና ውስጥ አስገብተው እንደተደገነብን የአዲስ አበባን ቁልቁለት መውረድ ጀመርን። ኬላው ላይ "ኃይሌ ፊዳ ተያዘ" የሚለው ዜና ወዲያው በመስፋፋቱ አላፊው በሙሉ ተሰብስቦ ስለነበረ ሰው ፊት ከሚሆንብን





ብለው ነው፤ ወደታች ወረድ አድርገው ይገድሉናል ብለን እርግጠኞች ነበርን። ከዚያም ዘልቀን የድሮ ክብር ዘበኛ መምሪያ የነበረው ፎቅ ስንደርስ፣ ምድር ቤት አስገብተው ይገድሉናል ብለን ጠበቅን :: በኋላም ጄኔራል አበበ የሚባለው ቢሮ ሆነን ሳለ ስልክ ከሆነ ቦታ ተደውሎ ደርግ ጽ/ቤት ወዳለው እስር ቤት ተወሰድን። እንተርፋለን የሚል ጥርጣሬ እንኳን ቢኖረን ኖሮ እዚያ በተወገደ ነበር። ቀስ በቀስ ቃልም ሰጥተን ከጨረስን በኋላ ከቤተሰብም ስንቅ እንዲቀርብልን ከተፈቀደ በኋላ አሁን ካሁን ይገድሉናል ከሚል አንዱን ቀን ወስደው ይገድሉናል ወደሚል ግምት ተሸጋግረን "መደበኛ" የእስር ኑሮ ጀመርን:: በአንድ ላይ ከተያዝነው አራታችን በሕይወት ስንተርፍ ኃይሌን ከአንድ ዓመት ከአስር ወር በኋላ ወስደው ገደሉት።

በእነዚህ እስካሁን በገለፅካቸው ጊዜያት እነርሱም ቢሆኑ ሊገድሉን ወስነው እንደነበር ሀሳባቸውን የቀየሩት ቆይተው እንደሆነ ዛሬም አምናለሁ። ኃይሌንም ያኔ ትተው ለምን ከሁለት ዓመት በኋላ እንደገደሉት ግምት እንጂ የማውቀው ነገር የለኝም። በዚያን ወቅት ተወስደው የተገደሉ የቆዩ እስረኞች ዝርዝር ሲታይ፣ (ከኛ እነኃይሌና እነንግሥት ከኢህአፓ እነብርሀነ መስቀልና የኢህአወሊ መሪዎች የነበሩት እነቲቶ ሕሩይ ፤ከቀድሞ ባለሥልጣኖች እነአቶ ካሳ ወልደማርያም እንዲሁም አቡነ ቴዎፍሎስ ነበሩበት)። መንግስቱ ኃይለማርያም በእስር ላይ ካሉት ለየትኛውም ዓይነት ንቅናቄ መሪ ሊሆኑ የሚችሉትን ጨርሼ የተረፈው ቀኑን ይቁጠር ብሎ በመወሰን የገደላቸው ይመስላል። አቶ ሐጎስ ከኔ ይልቅ አንተ ነበርክ ይህን ልታጣራ የምትችል አይዞህ የአንድ "አልባሌ

ሰው” አሟሟት ሁኔታ አጣራልኝ ብዬ የጀግና ጊዜህን አላስጠፋህም። በሕይወቴ እያለሁ ሰውን ሁሉ በእኩልነት የሚያዩ፣ የማንም ሰው በፖለቲካ ምክንያት መሞት የሚዘገንናቸው ሰብዐዊ ፖለቲከኞች አገሬ የፖለቲካ ሥልጣን የያዙ እንደሆነ እንዲጣራልኝ እጠይቅ ይሆናል።

ለማንኛውም አቶ ሐጎስ መቃብር ውስጥ በአንድ እግር ቆሞ ስለሚኖር ወኔ ወደማውራቱ እንመለስ። በእነዚህ ጊዜያቶች ሁሉ ከአምስታችን አንዳችንም ወደውጭ የሚታይ ስሜት ያሳየ ወይንም ድምፅ ያሰማ አልነበረም። ጄኔራሉ ቢሮ ሆነን፣ ከዚያም ደርግ ጽ/ቤት ቃል መስጫው ቢሮ ውስጥ ሲጃራ ማጨስ ሲፈቀድ አራታችን በላይ በላዩ እናጨስ እንደነበር ትዝ ይለኛል። ወታደሮች አንዱ ጠባብ ክፍል ውስጥ አስገብተውን ለብቻችን ስንሆን ነው ለመጀመሪያ ጊዜ እርስ በርሳችን ማውራት የቻልነው። ስለነበርንበት ሁኔታ ስለማይቀረው ሞት ብቻ አልነበረም እናወራ የነበረው። ከውጭ የወታደሮች ኮቴ ሲሰማ ጆሮአችን ቀጥ ማለቱ ባይቀርም ለረዥም ጊዜ የሚተዋወቁ ጓደኛሞች በየትም ቦታ ሊያወሯቸው የሚችሉትን ወሬዎች ነበር የምናወራው። ጓደኛዬ ብራዘር አል የዚያን ዕለት ማታ ስለዲሲ ዲስኮ ያወራን አንድ ታሪክ ዛሬም ትዝ ይለኛል። እኔም ሞቴን እየጠበቅሁ የነበርኩበት ቦታ ካደግሁበት ሰፈር ድንጋይ በእጅ ወርውረው የሚያደርሱበት እርቀት ላይ ስለነበረ፣ ስለአራት ኪሎ ጀብዱዎች እያወራሁ “አንዝናና” ነበር። ሕይወት እስከመጨረሻው ሴኮንድ ለሞት እጅ አትሰጥም።





ደጋግሞ እንዳዩት ፊልም በአንጎሌ ተቀርጾ ያለው በተለይ ከጎጃም በር ኬላ እስከ ደርግ ጽ/ቤት ድረስ የነበረው የመኪና ጉዞ ነው። እንዳልኩት ከማንኛችንም ምንም ድምጽ አልተሰማም። ሁላችንም በየፊናችን ከሕይወት በመሰናበት ላይ ነበርን ማለት ይቻላል። የራሴ “ስንብት” ይህን ይመስል ነበር።

አንዱን ደቂቃ አይተህ ቶሎ መልስ የተባልኩት መጽሀፍ እጄ የገባ ይመስል የሕይወቴ ዋና ዋና ምዕራፎች (የሀያአምስት ዓመት አዛውንት ነበርኩ!)፣ በዓይነ ሕሊናዬ ፊት ውልብ እያሉ ያልፋሉ፤ በሚቀጥሉት ደቂቃዎች ደግሞ ገና ለመኖር ሀምሳ ዓመት ያለኝ ይመስል መሞቴ መሆኑን እረሳና ትርኪ ምርኪ ሀሳቦች ይመጡብኛል። ክረምትም ሆኖ ብዙ ሳር አይታይም፤ ወይ አዲስ አበባ መቼ ይሆን መንገዶችሽ ከገበጣ መጫወቻነት የሚወጡት፤ እቴቴ ይህኔ እማማ አዛሉ ጋ ቡና እየጠጣች ነው ወዘተ ዓይነት ነገሮች በአንጎሌ ያልፋሉ። (ይዞን በሾላ ቁልቁለት የሚወርደው መኪና ለምን እንደሆነ እንጃ አሁን ካሁን አቆመ በሚያሰኝ ዝግታ ነበር የሚሄደው)። በሚቀጥለው የጊዜ ክፍል ደግሞ ለራሴ ሞት መርዶ የተቀመጥኩ ያህል ከፍተኛ ሀዘን በድን ያደርገኛል። ለመያዝ ያበቁንን የተለያዩ መጥፎ አጋጣሚዎች በቁጭት እረግማለሁ። አልቅስ አልቅስ ያለኝ የደካማነት ደቂቃዎች ደግሞ ከምወዳቸው ሰዎች በተለይ ከእናቴና ከያኔ አፍላ ፍቅረኛዬ ለዘላለሙ መለየቴ ሲሰማኝ ነበር። ድምፄን ሳላሰማ ከስንት ጊዜ በላይ “እቴትዬ ደህና ሁኚልኝ፣ ሰፋኒትዬ ደህና ሁኚልኝ” እል ነበር። ወደ መገደያ ቦታ እየወሰደን ነው ብዬ ባመንኩት መኪና ውስጥ በዓይኔ ትይዩ ተቀምጦ የነበረውን አብሮ

ተገዳይ ጓደኛዬን ገዳዬቹ ሳያዩ ጣቴን አነቃንቼ "ባይ ባይ አቤ" የሚል ምልክት ስሰጠው ትዝ ይለኛል።

"የጀግንነት" ደቂቃዎችም ነበሩኝ፤ አቶ ሐጎስ። እንዲያውም አብዛኛውን ጊዜ ድብን አድርጎ ያናድደኝ የነበረው፣ ፍርድ ቤት ቀርበን "በፈርጣጭነት ሞት ተፈርዶብን በታሪክ ካሜራ ፊት ሳይሆን ተራ ነፍሰ ገዳዮች ማንም ሳያይ አንዱ ዋሻ ውስጥ ወስደው ሊገድሉን መሆኑ ነበር። ኃይሌ እንደ ካስትሮ ዓይነት "ታሪክ ከክስ ነፃ ያደርገኛል"[16] ለሚል ንግግር ዕድል ሳያገኝ፤ እኔም የጎርኪ "እናት"[17] ውስጥ ይሁን "ብረቱ እንዴት ጠነከረ (How the steel was tempered)"[18] የሚለው መጽሀፍ ውስጥ እንዳነበብኩት (ዛሬማ ደራሲውንም ዘነጋሁት፤ ታሪኩንም በደንብ አላስታውሰውም) በዛሪስት ሩሲያ የሞት ፍርድ ተፈርዶባቸው "ዓለም ዓቀፍን" እየዘመሩ ወደመሰቀያ በታቸው እንዳመሩት ወጣቶች "ተነሱ የረሀብ እስረኞች" ሳልል ወይንም ፋሺስቱ ሊገድለው ወደመግደያ በታ እየወሰደው ሳለ 'የምትናገረው የመጨረሻ መልእክት አለህ?" ቢለው "ደደብ ላንተ ስል ነው የምሞተው" እንዳለው የጀርመን ኮሙኒስት ታሪክ የሚመዘግብልኝ የአንድ መስመር ማስታወሻ እንኳን ሳይኖር መሞታችን ነበር የሚቆጨኝ።

አቶ ሐጎስ፣ ሞትን ሲመጣ መቀበል በደፈናው አብዮታዊ ትግል የሚባል ነገር ውስጥ ሲገባ በሩ ላይ የሚደረግ ቃለ መሀላ ብቻ

16. "History will absolve me" (1953).

17. Maxim Gorky. (1906). Mother.

18. Nikolai Ostrovsky. (1932). How the Steel Was Tempered.





አልነበረም ያደረግነው። በዚህች ከላይ በጠቀስኩት ሁኔታ ውስጥ እኛም መሀላችንን ለመፈፀም ዝግጁ ነበርን። ከዚህ ተነስተህ ኃይሌን በወኔቢስነት የከሰስከውን አንሳልኝ አልልህም። እኔኑ የባሰ እየሳቅህብኝ እንደሆነ ይሰማኛል። አንተ ስንት ዓመት ሙሉ በቀበሮ ጉድጓድ ውስጥ እየኖርክ፣ እነዚህን ሁሉ ጊዜያት በየቀኑ ከሞት ጋር እየተፋጠጥክ በአሸናፊነት አዲስ አበባ እንደደረስክ ስለምታውቅ፣ በጽሁፍህ ያልከውን ልጥቀስልህና "ለሕዝብ ተሰውተው ነፃነት ለመቀዳጀት መነሳቱ በርግጥም ቁርጠኝነትንና ጽናትን ስለሚጠይቅ፣ እየሞቱ ነው ትግል እየታገሉ ነው ድል።" ለምን እንዳዲስ ነገር ትተርከዋለህ ትል ይሆናል። እኔ ግን ካንተ አስራ አምስት ዓመት ጋር ለመወዳደር አትበቃም ብትለኝም፣ ከዚህ በላይ ካነሳሁዋቸው ሁኔታዎችና ከሌሎችም ከዚህ በታች ከማነሳቸው ጉዳዮች ጋር ተያይዞ እንኳን እራሴ ልመለስበት ቀርቶ ሰብዓዊ ፍጡር ላይ እንዳይደርስ የምመኝ አድርጎኛል። በአጭሩ፣ በዚህ ጽሁፍ መጀመሪያ ላይ በጠቀስኩልህ የፖለቲካ ትርጉሙ ፈሪ ሆኛለሁ። በዚሁ እንግዲህ በጀግንነት ይሁን በፈሪነት የሞቱትን በሰላም እንተውና በሕይወት ስላሉት ጀግኖች ስለእነአቶ ሐጎስና ስለፈሪው ደረጀ እናውራ። ምን ዓይነት በፈሪነቱ የማያፍር ፈሪ መጣብኝ ትል ይሆናል። ጀግንነት የብዙ ወንጀሎች መነሻ ትልቅ የኋላ ቀርነት ምልክትና ምክንያት ነው የሚለው እምነቴ ነው "ጎበዝ ፈሪ" ያደረገኝ።

አቶ ሐጎስ፣ ከአሸናፊነት ትዕቢታችሁ የተነሳ "ፈሪን" በዘላለማዊ ቤቱ እንኳን እንዳያርፍ እስከመቃብር ቤት የምታሳድዱ ጀግኖች መሆናችሁን

አይቼባት ካበገነችኝ ያንተ ጽሁፍ ሌላ እንዲሁ ስለእናንተ ጀግንነት ሰምቼ የዘገነነኝን ወሬ ልንገርህ። አብዛኞቹ ወታደሮቻችሁ እንደእናንተ ገና የተቃዋሚን ታሪክ አውቆ የማጉደፍ ወንጀል ለመሸረብ፣ እንዲሁም የሥልጣን ሽኩቻ ለማካሄድ የሚያበቃ እድሜና ስልጣን ላይ ያልደረሱ ልጆች መሆናቸው ይነገራል። እነዚህ ገና ተጫውተው ሳይጠግቡ ኩሺኔታ አስጥላችሁ ካላሺን አስታጥቃችሁ አዲስ አበባ ያስገቡዋቸሁ ወታደሮች አዲስ አበባ ልብሳቸውን አጥበው በየመንገዱ ነው የሚያሰጡት አሉ። ከእነዚህም ልብሶች መሀል አንዷት ብርድልብስ ዓይነት ነገር አለች አሉ። እርሷንም "ስኖር መከናነቢያዬ፣ ስሞት መገነዣዬ" ይሏታል ሲባል ሰማሁ። ይህ ሞት አይፈሬነት ይህ ቆራጥነት አስደነገጠኝ። እነ አቶ ሐጎስ "ይህ ጠላትህ ነው በለው" ያላችሁት ላይ ተወርውሮ የሚሰካ ጦር ሆነው ታዩኝ። ጀግና ሆነው ቢሞቱ ሀውልት ከሚያሰራላቸው ከእናንተ ድርጅት ስር ወጥተው ፈሪ ሆነው ቢሸሹም የምትወዳቸው እናታቸው ጋር እንዲመለሱ ተመኘሁላቸው። ("በመድፍ በመትረየስ ካላተራመሰው እኔ እናቱ ነኝ ወይ ሲሸሽ የምወደው" የሚለው የጀግና ሚስት ግጥም ትዝ ብሎኝ ነው)።

ከሞት ጋር በቀጥታ የመፋጠጥ ታሪኬ በግል ጠባዬ ላይ የለወጠው ነገር ይኑር አይኑር አላውቅም። እንኳን እንደዚህ ዓይነት አሰቃቂ ሁኔታ በሕይወት ውስጥ የደረሱ ብዙ አነስተኛ ነገሮችም ቋሚ ማህተም ሳይተዉ አያልፉም ይባላል። እኔ በግል ሕይወቴ እንደቀድሞዬ መኖር የቀጠልኩ ይመስለኛል። ይህ ባይሆንም የራሴ ጉዳይ ነው። አገርን፣ ፖለቲካን፣ ማንንም አይመለከትም። በፖለቲካ ሕይወቴ ግን አንድ





ትልቅ ምዕራፍ የተዘጋበት ታሪክ ነው። "ቅፅበታዊ ወኔ" ብቻ ሳይሆን ሙሉ ሕይወቴን የፖለቲካ ጀግንነት አጠግብ ላለመድረስ አስወስኖኛል። የግል ታሪኬን ለመዘርዘር ስላልተነሳሁ ባጭሩ ለምንም ዓላማ ለመሞት ዝግጁ መሆን የለብኝም፤ ለፈለገው ዓላማ ለመሞት ዝግጁ የሆነንም በአድናቆት ሳይሆን በጥርጣሬ ማየት አለብኝ የሚል እምነት ከያዝኩ ቆየሁ። በግልህ ለአንድ ሕይወትህ ፈርተህ ነው ብለህ ልትስቅብኝ ትችላለህ አቶ ሐጎስ። ሕይወትን በመውደድ ክስ ብትከሰኝ ክርክር ውስጥ አንገባም። በዚህ ወንጀል ለመጠየቅ ዝግጁ ነኝ:: መከራከር የሚኖረው ለእናንተ ጀግኖች "የመሞት ግዴታ" "መስዋእትነት" የመክፈል ዝግጁነት አድናቆት ሳይሆን ክስ ይዤ ስመጣ ነው። ሞት አይፈሬነታችሁ እንደ ቡዲስቶች ቤንዚን እራሳችሁ ላይ አርከፍክፋችሁ እንድታቃጥሉ የሚያስደርግ አሳዛኝ የግለሰብ ባለወኔነት ሳይሆን ሕዝቦችን የሚያፋጅ ወኔ ሲሆን ደግሞ ከክስም አልፎ ወደመወንጀል እሻገራለሁ። ለዚህ ውንጀላ መነሻ የሆነኝን ሞትን ለመቀበል ዝግጁ ከነበረ አብዮታዊነት የፖለቲካ ሞትን ለራሱ ብቻ ሳይሆን ሰው ለተባለ የማይመኝ ፈሪ ወደ መሆን የለወጠኝን የግል ታሪኬን አውርቼሀለሁ። አሁን ደግሞ ከአብዮታዊ ምሁርነት ወደ "ፖለቲካዊ ጴንጤነት" ያደረሰኝን ምሁራዊ ለውጥ ትንሽ ላብራራልህ።

ለነገሩ እንግዲህ "ምሁር ተብዬ" አይደለሁ? ቀደም ሲል ለድርጊት መመሪያ አብዮታዊ ርዕዩተ ዓለም ፍለጋ እንደሮጥኩ ሁሉ ለዚህ የግል ሽሽት "ፍልስፍናዊ ሽፋን" ለመስጠት መሞከሬ አልቀረም። በዚሁ ለመስዋእትነት ዝግጁ የመሆን ጉዳይ በተለይ አምስት ዓመት

የተሸናፊዎች ዩኒቨርሲቲ በሆነው እስር ቤት ቆይቼ ወደ ጀርመን አገር እንደገና ከተመለስኩ በኋላ ብዙ አንብቤአለሁ። ብዙ ክርክሮች ተከታትያለሁ። በመጀመሪያው የጀርመን ቆይታዬ ጊዜ የአሸናፊዎችን፣ የጀግኖችን ታሪክ ተስገብግቤ ያነበብኩትን ያህል በአሁኑ ቆይታዬ ደግሞ የተሸናፊዎችን፣ የፈሪዎችን ታሪክ አነበብኩ፤ እያነበብኩም ነው። የሩሲያ፣ የቻይና ወዘተ አብዮቶች ታሪክ ከተሸናፊዎች አንፃር ሲነበብ ተራ የወንጀሎችና የወንጀለኞች ታሪክ ነው የሚሆነው። ለዚህም ምሳሌ ለመስጠት ያህል በአሜሪካ ስታሊኒስቶች ስም የወጣውን "ታላቁ ሴራ" የሚለውን (በአማርኛ ተተርጉሞ ኩራዝ አሳታሚዎች አውጥተውታል) ወይንም የሩሲያ አብዮት ታሪክ የተባለውን የስታሊን መጽሀፍ (እርሱ አጻፈው እንጂ አልጻፈውም፤ ሆኖም ግን የወጣው እንደ ስታሊን ስብስብ ስራዎች ቅጽ 17 ነው!) ከአርተር ኮስትለር የቀትር ጨለማ (Darkness at noon[19]) ወይንም ከማኔሽ ስፐርበር "አንዲት ጠብታ እምባ ውቅያኖስ ስታርስ" (Wie eine Traene im Ozean[20]) ከሚሉት መጻሕህፍት ጋር ማወዳደር ይበቃል።

ሌኒን እንዳለው ሰንሰለት መጀመሪያ የሚበጠሰው የላላው ቀለበት ላይ ነው። እኔም ከዚህ በአብዮት ስም ወንጀል ካስቻለ ርዕዩተ ዓለም ጋር ካቆራኘኝ ሰንሰለት እራሴን ለማላቀቅ ቀለበቱ የላላልኝ በስታሊን በኩል ነበር።

19. Arthur Koestler. (1940). Darkness at Noon

20. Manès Sperber. (1976). Wie eine Träne im Ozean





ሌኒን ወደ ሥልጣን በሚያደርገው ሩጫ ተቃዋሚ የደቀነበትን መሰናክል ሲዘል፤ እራሱ በተራው መሰናክል ሲያስቀምጥ፤ እንኳን ጠላት ወዳጅ ሳይነቃ አቅጣጫ ሲለውጥ አፍ ስለሚያስከፍት ቆም ብሎ "ይኸ ሰውዬ ወዴት ለመድረስ ነው እንዲህ የሚሮጠው" ብሎ ለመጠየቅም ፋታ አይሰጥም። (በነገራችን ላይ በዚህ የሥልጣን ሩጫ አሸነፍክ ተባለ እንጂ እንዳላሸነፈ ያወቀ የመጀመሪያው ሰው ሌኒን ነበር ለማለት ይቻላል። ከሌኒን ''ስብስብ ሥራዎች ቅጽ 28" በኋላ ያሉት ጽሁፎቹ በጥንቃቄ ሲነበቡ "ለዚሁ ነበር እንዴ ይኸ ሁሉ ሩጫ' የሚል ይመስላል)። ማኦም ቢሆን ቀን ቀን በጎረቤቶቹ ላይ የፈለገውን ሴራ ሲሸርብ ቢውልም ማታ ማታ ጋያውን ይዞ "ልጆች እንግዲህ ዶሮ ድንጋይ ብትታቀፍ እንቁላል ስላልሆነ ጫጩት አትፈለፍልም" የሚል ዲያሌክቲካዊ ተረት የሚያወራ ሽማግሌ ገበሬ ስለሚመስል ተረቱ ይጥማል። ስታሊንን ግን "ምሁራዊ ውቃቢዬ" ከመጀመሪያውም አልወደደውም ነበር። በምን ሳበኝ ታድያ? ከቋንቋው ቋንቋው አይጥም፣ በቃሉ የሸመደደውን የሚተፋ ተራ የዲያቆን ሰበካ ነው የሚመስል።

ከሀሳብ ሀሳብ የለው አንድና አንድ ሁለት ነው የሚለውን ተራ ሂሳብ ካልኩለስ ያስተማረ ለማስመሰል የሚሞክር ግብዝ መሀይም ነው። የማርክስን "የአይሁዶች ጥያቄ" (The Jewish Question) "የጀርመን ርዕዩተ ዓለም (The German Ideology) የመሳሰለ ዶሮ ወጥ በተመገበ አእምሮዬ የስታሊንን የሌኒኒዝም መሰረተ ሀሳቦች ስበላ አሸር ባሸርነቱ ሳይታወቀኝ ቀርቶ አያውቅም ነበር።" ሆኖም ይህን ምሁራዊ አይስቤነቱን ተጋኖ ይወራለት በነበረው ቁርጠኛነትና

“ብረታዊ ዲሲፕሊን” ሸፈንኩለት፤ በገዛ ዳኝነቴ በታሪክ ካሜራ ፊት የሚውረገረግ ተዋናይ እንጂ ለሰፊው ሕዝብ ልዕልና አይደለም የቆመው ብዬ ከፈረድኩበት ቢያንስ ግን ቋንቋው ይጥመኝ ከነበረው ከትሮትስኪ ጋር ባላቸው ጠብ በትውልዱም በቋንቋውም ለሕዝብ ይቀርባል ያልኩት የስታሊን ወገን ሆንኩ። እነቡካሪንን መግደሉ ምንም ተውጦልኝ ባያውቅም (ሌኒን በኑዛዜው ላይ የፓርቲው ተወዳጅ አባል ስላለውም ጭምር ነው የቡካሪን ሞት በተለይ የተሰማኝ) ይህንንም ማኦ 70 በመቶ ጥሩ ሰርቷል፣ 30 በመቶ መጥፎ ሰርቷል ባለው መሰረት “ለአብዮቱ ሲል ከሰራቸው ሰላሳ በመቶ ስህተቶች” እንደ አንዱ ቆጠርኩለት። ረዥሙን ታሪክ አጭር ላድርገውና ከክሩስቾቭ የሀያኛው ጉባኤ የስታሊን ማጋለጫ ዲስኩርም አልፋ፣ በዚህ ክፍለ ዘመን ከተፈጠሩ ዋነኛ ነፍሰ ገዳዮችና የታሪክ ወንጀለኞች መሀል ከሂትለር ቀጥሎ የሚመጣ አረመኔ ሰው አደረግሁት። በኢትዮጵያ አብዮት ውስጥ የደረሰብን ሽንፈት ለስታሊን ወንጀሎች አይኔን ከፈተው። ከዚያ በፊት “የላይብረሪ መደርደሪያ ያጣበቡ ቁጥር የለሽ መጽሐፍት ያልቻሉትን! “መሸነፍ ብልህ ያደርጋል” ይላል ጀርመን ሲተርት።

ድሮም በታሪክ ዛሬም በኛ ዕድሜ የቀድሞ ስታሊኒስቶች ከሁለት “ድህረ ስታሊንስትነት” መንገዶች አንዱን ይመርጣሉ። እንደነ አንድሬ ግሉክስማን ከስታሊኒስትነት ወደ ሬጋን አፈ ቀላጤነት የሚዞሩ አሉ። ወይንም ደግሞ እንደትራፐር፣ አሥር ዓመት የስታሊን እስር ቤት እንኳ ከሶሺያሊስታዊ እምነት የማያዛንፋቸው ፑላንዛ እንዳለው ‘’ሶሺያሊዝም ወይ ዲሞክራሲያዊ ነው፤ ወይንም ደግሞ በፍጹም





ሶሺያሊዝም አይደለም” ብለው ለተለየና በተለየ መንገድ ሊመጣ ለሚችል ሶሺያሊዝም እንደቆሙ የሚፀኑ አሉ።

አቶ ሐጎስ፣ እስካሁን ከምጥላቸው አንዳንድ አስተያየቶች የነግሉክስማን ዓይነት ፀረ ኮሙኒስት መንገድ እንዳልያዝኩ አሁንም “ማርክሲስት ተብዬ” ዝንባሌዎች እንዳሉኝ ሳትገምት አትቀርም። ቢያንስ በተማርኳቸው ሁለት የትምህርት ዘርፎች (ኢኮኖሚክስና ሶሲዮሎጂ) ስለሕብረተሰቦች አሰራርና እንዲሁም ቅራኔዎች ከርሱ የተሻለ የሚያሳውቅ ስላላገኘሁ ነው። (በመጠኑም ስላለፉት በተለይ ግን ስላሉት የሕብረተሰብ ስርዓቶች ማለቴ ነው። ስለሚመጣው ማርክስም ክርስቶስም የሚያሳምኑኝ ነገር አይኖራቸውም። እነርሱም አያውቁትምና። የዛሬ መቶ ዓመት የሰው ልጅ ምን ዓይነት የሕብረተሰብ ሥርዓት ውስጥ እንደሚኖር ሊያውቅ የሚችል ሰው የለም። በእርግጠኛነት የሚታወቅ ነገር ቢኖር የዛሬ መቶም ሁለት መቶም ዓመት ካላሺን ሰው እንደሚገድል ብቻ ነው)።

ማርክስ እንግዲህ የሶሺያሊዝም አባት ነው። ርዕዩተ ዓለማዊ ልጆቹ የፈፀሙትን ወንጀል በስታሊን ምሳሌነት ከላይ ጠቁሜአለሁ። እንዲሁም የሰባ ዓመት ሶሺያሊዝም ታሪክ የማኦን ምሳሌ ትንሽ ላጣምና ለሰራው ሕዝብ ይሆናል ተብሎ የተሰራው ማ ሲጠብ ጊዜ ጫማውን ከመጣል ይልቅ የሕዝቡን እግር እዚህ ጫማ ውስጥ ለማስገባት እግሩን ሲገዘግዝ የኖረበት ስርዓት ነበር ባይ ሆኛለሁ። የተሞከረው ሶሺያሊዝም መጥፎ መሆን ግን የነበረውንና ያለውን ካፒታሊዝም ጥሩ አያደርገውም። በሶሻሊዝም ስም ወንጀል ስለተሰራ ካፒታሊዝም ባለፉት ብዙ ምዕተ

ዓመታት ለሰው ዘር በሙሉ እድገትና ብልጽግና ነው ያመጣው ብዬ ዛሬም ወደፊትም ማርና ወተት የሚፈስበት ስርዓት ይሆናል ብዬ ማመን አልችልም። አሜሪካ በቪየትናም ጫካ ውስጥ ውሀ ሲያጠጣ እንዳልነበረ በቅርቡም ለባግዳድ ሕፃናት ከአውሮፕላን ከረሜላ እንዳልወረወረላቸው የማውቀው ነገር ነው። እነዚህን መስመሮች በምጽፍበት ወቅት የኢትዮጵያ ዲሞክራሲ የክርስትና አባት የሆነው ጆርጅ ቡሽ ከአፍሪካ ምድር ከተወለዱ የእንጀራ ልጆቹ ላይ ምን እያደረሰ እንደሆነ እየሰማሁ ነው።

ዊንስተን ቸርችል በሀያ ዓመቱ ሶሺያሊስት ያልሆነ ሩህሩህ ልብ የለውም፤ በአርባ ዓመቱም ሶሻሊስት ሆኖ የቆየ ደግሞ የሚያስብ አንጎል የለውም ብሎ ቀልዶ ነበር ይባላል። እኔ ግን በአርባ ዓመቴም ማርክስን አስተማሪ ስታሊንን ወንጀለኛ አድርጌ ይህን እንዴት አስታርቀዋለሁ?

በመጀመሪያ ደረጃ እንድርያስ እሸቴ ከጥቂት ዓመታት በፊት ጽፎት ባነበብኩት ቆንጆ ጽሁፍ ውስጥ እንዳለው ሳይንሳዊውን ትቶ ሳይንሳዊ ያልሆነ ሶሽያሊዝም ተከታይ በመሆን ነው። ይህም ሳይንሳዊ ያልሆነ ሶሻሊዝም በኋላ የሰፊውን ሕዝብ እግር የሚያስቆርጥ ጫማ አያስነድፍም። የታሪክን አቅጣጫ ማስያዣ ካላሺን ሳይሆን "መዘባረቂያ" እርሳስ ብቻ ነው የሚፈቅድ። ዘባራቂው ባለእርሳስ ቢሳሳት በላጲስ ያጠፋል እንጂ ጣቱ ለመቀጣጫ ተብሎ አይቀነጠስም። ለተጨቆኑ፣ ለተበዘበዙ፣ እኩልነት ለተነፈጉ ተቆርቋሪነትን ያሳድጋል እንጂ አያስቀንስም እነዚህን ካስቻለ ስርዓት የሚያስወጣ ይህ ነው የሚል በትረ ሙሴን ሆነ





የስታሊንን ብትር የያዘ መሪ ግን አያስፈልገውም። የባህል የእውቀትና የእውነት ምንጭ የሆነና የጠማቸው ገብተው የሚዳክሩበት ረግረግ እንጂ ካላሺን ለካላሺን የሚያፋጩ "ወንዶች የሚፋለሙበት ጦር ሜዳ አይኖረውም"። ለቅዱስ ዓላማ እሞታለሁ እገድላለሁ የሚሉ ጀግኖችን የሚጠረጥሩ፣ በምንም ምክንያት ለመሞትም ለመግደልም የማይፈልጉ ለመኖር ብቻ ቁርጠኛ የሆኑ ፈሪዎች ሊከተሉት የሚችሉ ዓላማ ነው።

ሁለተኛው እርምጃ ደግሞ "ዓላማውና ግቡ ቅዱስ እስከሆነ ድረስ እዚያ ለመድረስ የሚያግዝ ዘዴ ሁሉ የራስን ሕይወት መስዋዕት ማድረግን ጨምሮ ቅዱስ ነው" የሚለውን መርህ ማውገዝ ነው። በአብዮት ስም ለተፈፀሙ ወንጀሎች ሁሉ መነሻ የሆነው ይህ መርህ ነው። እነ ሮብርስፒር መደበኛን ፍርድ ቤት ሳይሆን ታሪክን ፍርድ እያሰጡ እርስ በርስ ተራ በተራ የተረፋረፋት፤ የዛሩን ነጋሲ አገዛዝ ሲታገሉ "የሞት ፍርድ ይወገድ" ይሉ የነበሩት እነሌኒን ቃላቸውን አጥፈው በኋላ የስታሊንን ፍጅት ባስከተለው "አብዮታዊ ፍትህ" አማካይነት ተቃዋሚዎቻቸውን ያጠፉት፤ ባገራችንም ኢሕአፓና መኢሶን "አመፃ" "ቀይ ሽብር" እያሉ ሲለካከፉ 'ውሻ በከፈተው ጅብ ይገባል' እንዲሉ ለደርግ ፍጅት ፖለቲካዊና ርዕዩተ ዓለማዊ ንጣፍ የሰጡት በዚህ መርህ የተመሰረተ ታክቲክ ስለተከተሉ ነው። አቶ ሐጎስ አንተንም የዓላማ ቅዱስነት፣ የቅቡልነት፣ የወንድነት መለኪያ ምን ያህል ዓመታት ካላሺን አንግቶ ለመሞት ዝግጁ እንደተሆነ ነው የሚያስብልህ፤ ከ13 ዓመታት በፊት በግፍ የተገደለን ሰው ሬሳ አስወጥቶ እየፎከረ ወይስ እየፈራ ሞተ? የሚል ሰብዓዊነት የጎደለው

ጥያቄ የሚያስነሳህ የባሰውን ግን ኢትዮጵያ ውስጥ በሚያንዣብበው (ቢያንስ በደቡብ) የእርስበርስ ጦርነት "ትዕግስታችን አልቋል" የሚል ደም መፋሰስን ብቻ የሚያስከትል ፉከራ የሚያስፎክርህ ይኸው መርህ ነው። የዚህ መርህ ተከታይ ነህ ብዬ ከከሰስኩህ፣ ይህን መርህ ለምን ጠምጄ እንደያዝኩት ደግሞ ትንሽ ላስረዳ።

አንተ እራስህ መመዘኛ አውጥተህ ወይንም የምታምናቸው ባወጡልህ መመዘኛ መሰረት አንድን ዓላማ ቅዱስ ነው ትላለህ። ለዚህም ዓላማ ለመሞት ዝግጁ ትሆናለህ። ያንተን ዓላማ የሚቃወመው ደግሞ እርኩስ ነው። ወደ አንድ ቦታ ሲኬድ መንገድ ላይ ያጋጠመን እንቅፋት ማንሳት ያለ ነገር ነው። "ሁሉን እንደአመጣጡ የምትመልስ ጀግና" ስለሆንክ ወደ ቅዱስ ዓላማህ ስትገሰግስ ለመውደቅ ዝግጁ የሆንከውን ያህል እንቅፋት ለማንሳትም ዝግጁ ትሆናለህ። ለቅዱስ ዓላማ የመሞት ግዴታ እንዳለብህ የምታምነውን ያህል ለእርኩስ ዓላማ የቆመን የመግደል መብት ለራስህ ትሰጣለህ። ወንጀሉ የሚጀመረው መግደል ላይ ሳይሆን ለመሞት ዝግጁ መሆን ላይ ነው። ለቅዱስ ዓላማ መሞት ቅዱስ ይሆንና እርኩስ የተባለን ዓላማ ተከታይ መግደል ወንጀል መሆኑ ይቀራል። ለመሞት ዝግጁ የሆነ ለመግደል ዝግጁ ይሆናል ማለት ነው። እየፎከረ የሚሞት እየዘፈነ ቢገድል ምን ይገርማል?

በዚህ ሕይወት በተረሳችበት ሁኔታ መግደል ወይንም መሞት የአጋጣሚ ጉዳይ ይሆናል። ልዩነቱ ልትሞት የምትችለው አንድ ጊዜ ብቻ ሲሆን ብዙ ጊዜ መግደል መቻልህ ነው። ስለዚህም አንድ ሰው በመግደልና





መቶ ሰው በመግደል መሀል ያለው ልዩነት የስታቲስቲክስ ብቻ ይሆናል:: ሕይወት "ዲሞክራሲ ወይንም ሞት"፤ "የኢትዮጵያ አንድነት ወይንም ሞት"፤ "የኦሮምያ ሪፖብሊክ ወይንም ሞት" በሚሉ ሞት አምላኪ መፈክሮች ስር ትረገጣለች። እርስዋን መውደድ ፈሪነት ይሆናል።

ከዚህ ቅዱስ ዓላማ ለመድረስ መግደል ወንጀል ካልሆነ መዋሸት ታሪክ መጠምዘዝ የመሳሰሉት ምን አላቸው? ይህ ቅዱስ ዓላማ የማያጥበው ወንጀል አይኖርም። በእንግሊዝኛ "The end justifies the means" የሚለው ይህ መርህ በጀርመንኛ "ዓላማውና ግቡ እዚያ መድረሻ ዘዴዎችን ሁሉ ይባርካል" የሚል መንፈስ ነው ያለው። ከሀይማኖት የተወሰደ መርህ ነው። ችግሩ እንግዲህ ሁሉም ዓላማህ ቅዱስ ነው የሚለው የየራሱ አምላክ ከዚያ መድረሻ ዘዴዎቹን የሚባርክለት የየራሱ ካህን ይኖረዋል። ሶሻሊዝም የሚባለው አምላክ በአቡነ ማርክስ በቄስ ሌኒን አማካይነት ተከታዮቹን ለቅዱስ አምላካችሁ ይህን ያንን አድርጉ ብሎ ያዘቸዋል። በርሱም ስም የፈለጉትን ወንጀል ቢፈጽሙ በአቡነ ማርክስ ስብስብ ሥራዎች ቅጽ 14 ገጽ 212 መሰረት ሲታይ ዓላማውን የተባረከ ያደርገዋል። አምላካቸው (ቅዱስ ዓላማቸው) የኢትዮጵያ አንድነት ከሆነ የፈለገውን ወንጀል ቢሰሩ በአቡነ ሚኒሊክ ገድል ዘመነ 1888 መሰረት የተባረከ ነው። በኦሮሞ ነፃነት ስም የፈለገው ሰው ከወዲያም ከወዲህም ቢሞት አቡነ ገዳ የተባረከ ያደርጉታል።

አንደኛ ነገር የቡድሀውን አምላክ ከክርስቲያኑ አምላክ የበለጠ ቅዱስ የሚያደርገው ምክንያት እንደሌለ ሁሉ የኦሮሞው ነፃነት አምላክ

ከኢትዮጵያው አንድነት አምላክ የበለጠ ቅዱስ የሚሆንበት ምክንያት የለም። ሁሉም ለአማኞቹ "ቀናተኛ አምላክ ነኝ ከኔ ሌላ ቅዱስ የለም" የሚል አምላክ ነው። የየእምነቱም ካህናት ወደየአምላካቸው የሚወስደውን መንገድ የሚባርኩበት የየራሳቸው ወንጌሎች አላቸው

ሁለተኛ ይህ የአማኞች ጠብ በዚህ አያቆምም። በአንድም አምላክ ስር የተሰበሰቡ ምዕመናን ቢሆኑ፣ ወደ ቅዱስ ዓላማ የሚወስደውን ትክክለኛውን መንገድ የያዝኩት እኔ ነኝ፤ ካህን እገሌ የባረከው አንተን ሳይሆን እኔን ነው የሚል ፍጅት ያነሳሉ። የጣልያን ሰራዊት ኢትዮጵያን እንዲወር ባርከው የላኩት የሮማው ጳጳስና አቡነ ጴጥሮስም የክርስትና ሀይማኖት ተከታዮች ነበሩ። ኮሙኒስቱ ስታሊን ከሂትለር በብዙ እጅ የበለጠ ኩሙኒስቶች ፈጅቷል። ቅዱስ ሶሽያሊዝም ወይንም ቅዱስ የአገር አንድነት ከተፎካካሪ ምዕመኖቻቸው መሀል የትኛውን እንደሚያበልጡ መናገር አይችሉም። ማሸነፍ ወደ ቅዱስነት የመቅረብ ምልክት አይደለም ከሆነማ ከአቡነ ጴጥሮስ ይልቅ የሮማው ጳጳስ፡ ከነቡካሪን ይልቅ ስታሊን ወደ ቅዱስነት መቅረባቸው ነው።

ሌላው በቅዱስ ዓላማ ምክንያት በታሪክ የደረሰ ፍጅት ቅዱሱን ዓላማ ክደሀል እኔ ነኝ ትክክለኛ ወራሽ ወዘተ በሚለው መሰረት ላይ የተካሄደው ነው። አሸናፊዎች የቅዱስ ዓላማ ቀጣዮች አድርገው እራሳቸውን ያቀርባሉ። ተሸናፊዎች ደግሞ አሸናፊውን የተነሳንበት/የተነሳህበትን ዓላማ ከድተሀል፣ ሌላ ዓላማ መከተል ጀምረሀል ይሉታል። ከዚህ ሙግት አንፃር የኢትዮጵያን ሁኔታ ያየን እንደሆነ እናንተ የአስራአምስት





ዓመታት ኢሰብዓዊ የደርግና የኢሠፓ አገዛዝ የጣልን ኢትዮጵያ ውስጥ ዲሞክራሲንና ፍትህን የማስፈን ቅዱስ ዓላማ የምንከተል ነን ትላላችሁ። ተቃዋሚዎቻችሁ ደግሞ የትግራይን ሕዝብ፣ ከአማራ የበላይነት ስር ከደርግ እልቂት ነፃ ለማውጣት ያደረጋችሁት ትግል ቅዱስ ሊሆን ይችላል። ዛሬ ግን የትግራይን የበላይነት፣ የTPLFን ሥልጣን የማስፋፋት እርኩስ ዓላማ እየተከተላችሁ ነው። የአሁኑን እርኩስ ዓላማ በቀድሞው ቅዱስ ዓላማ መሸፈን የተለመደ ነው። ደርግም የተቃወሙትን ሁሉ የቀድሞው ፊውዳል ስርዓት ተከታዮች ያደርጋቸው እንደነበረ ሁሉ እናንተም የተቃወማችሁን ሁሉ (አገሪቷ እፍኝ የማይሞሉ የደርግ ደጋፊዎች ብቻ እንዳሉባት እየታወቀ) የኢሠፓ ቅሪቶች ትላላችሁ።

የሆነው ሆኖ አቶ ሐጎስ ቅዱስ ዓላማን ተከትሎ ለመሞት፣ እርኩስ ዓላማን የተከተለ ለመግደል ዝግጁ ሆኖ ዲሞክራሲን መገንባት አይቻልም። ተቃዋሚ የጠመንጃ ኃይል እስኪያደራጅ ድረስ በጉልበት መግዛት ብቻ ነው የሚቻል። ዛሬም አስተማሪዬ ነው ያልኩህ ማርክስ "ኃይል አዲስ ስርዓትን ያረገዘ ሕብረተሰብ የሚያገላግል አዋላጅ ነው" ብሎኝ ተቀብዬው ነበር። አሁን ግን የለም የኔታ፤ በኃይል አዋላጅነት የሚወለድ አዲስ ስርዓት ሁሉ ጭንጋፍ ነው የሚሆን እለዋለሁ። አቶ ሐጎስ በዘለቄታው ሲታይ ካላሺን በተለያየ አምልኮ እየማሉ የበላይነታቸውን የሚመሰርቱ ቡድኖችን ሥልጣን ላይ የሚያወጣ መሰላል እንጂ ሕዝብን ወደነፃነት ሰገነት የሚያስወጣ እርካብ ሊሆን አይችልም። መሞትንና መግደልን የሚያስችል የፖለቲካ ትግል እርኩስ

ነው። ሞት የሌላ ሞት ጠሪ ጣዕረ ሞት እንጂ የአዲስ ሕይወት አብሳሪ መልአክ ሊሆን አይችልም። ሞት ይሙት!

ይህን በዚሁ ላቁምና አቶ ሐጎስ አሁን ደግሞ ከግለሰብ ወደ ድርጅት ከፖለቲካ ወደ ታሪክ እንሂድ።

## 3. ታሪክ የአሸናፊዎች ተረት እንዳይሆን

"ታሪክ ሰው ታሪክ ነው ብሎ የተቀበለው ተረት ነው" ይላል ቮልቴር። ከፈረንሳይ አብዮት በኋላ ቢጽፍ ኖሮ ምናልባት "ብዙው ታሪክ አሸናፊዎች ተቀባይነት ያገኛል ብለው የሚተርኩት ተረት ነው" ባለ ነበር። ታሪክን የወቅቱ መድረክ ላይ በአሸናፊነት ከወጣ በኋላ የጀመረ ማስመሰል በናንተ አልተጀመረም አቶ ሐጎስ። የዘመናዊው (ቢያንስ የአውሮፓ) አዲስ ክፍለ ዘመን ከፋች የሚባለው የፈረንሳይ አብዮት የመጀመሪያ ዙር አሸናፊዎችማ ከጉራቸው ብዛት አዲስ ታሪክ በነሱ እንደተጀመረ በማያሻማ ሁኔታ ለማብሰር ዓመቶችን አንድ ብለው መቁጠር ጀመሩ። ማርክስም የርሱ ርዕዩተ ዓለም ተከታዮች አሸንፈው የኮሙኒስት ስርዐተ ማህበር ሲመሰርቱ "የሰው ልጅ ቅድመ ታሪኩ አክትሞ እውነተኛ ታሪኩ ይጀምራል" ብሎ ነበር።

ወደአገራችንም ስንመለስ ተርታው ሕዝብ ሲንገላታ አይቶ እንዲመሩት እግዚአብሔር ቀብቶ ያነገሳቸው ሥዩመ እግዚአብሔር፤ መሪ አጥቶ ሲንገዋለል የነበረን ሕዝባዊ እንቅስቃሴ እንዲመራ ከታሪክ አደራ





የተቀበለው "ጊዜያዊ ደርግ"፤ አሁን ደግሞ አቶ ሐጎስ ልጥቀስህና "ሕዝቡ ውስጥ ገብቶ ቅቡልነት በማግኘት መራራ መስዋእትነት ከፍሎ ለሥልጣን የበቃው ኢሕአዴግ" በኢትዮጵያ አዲስ ታሪክ ጀምረናል ባዮች ናቸው። ለኃይለ ሥላሴ እግዚአብሔር፣ ለደርግ ታሪክ፣ ለመለስ ዜናዊ ሕዝብ አደራ ሲሰጣቸው ያየ ምስክር የለም። የተለመደው ታሪክን የአሸናፊ ገድል የሚያደርገው ብዕር የሚጽፈው ታሪክ ነው። ምስክርስ ቢጽፈው ኖሮ ኃይለ ሥላሴን "ሥዩመ ሽኩቻ"፣ መንግስቱን "ሥዩመ አጋጣሚ"፣ መለስንም "ሥዩመ ካላሺን" ከማለት ባላለፈም ነበር።

አቶ ሐጎስ ይህ የምተቸው ጽሁፍህ የሚጠቁማቸውን ጉዳዮች ስንወስድ TPLF የኢትዮጵያን የቅርብ ጊዜ ታሪክ በሞተርነት ሲያንቀሳቅስ እንደነበር ልትነግረን ዳር ዳር እያልክ ነው። የዓይነ አፋርነቱ ዘመን ሲያልፍ ፕሬዚዳንት መለስ በምን ዓይነት ልዩ ችሎታና ዘዴ ይህን የታሪክ መኪና በዚያ ጠመዝማዛ የሊማሊሞና የአላማጣ መንገድ ሲያከንፉት እንደነበረ ይተረክልናል። ምን አለ በለኝ።

እንደተለመደውም የታሪክ አጻጻፍ ማሸነፍን የትክክለኛነት፣ የጀግንነት ማረጋገጫ፤ መሸነፍን የስህተተኛነትና የፈሪነት ውጤት ለማድረግ ትሞክራለህ። የመኢሶን መሪ "መቃብር አፋፍ ላይም ደርግን ተለማምጦ ለመትረፍ የሚሞክር አልባሌ"፣ በአንፃሩ የTPLF አባል "ለጠላቱ ሀቁን እየተናገረ የሚሞት ጀግና" መሆኑ ነው። መኢሶን ከሕዝቡ ጀርባ በቤተ መንግስት ሽኩቻ በአቋራጭ ሥልጣን ላይ ለመውጣት

የተዘጋጀ የሕዝብ አራጆች ጥርቃሞ! እናንተ ደግሞ ለሕዝብ መስዋዕት ለመሆን ቆርጦ በመነሳት በቅቡልነት ለሕዝብ ሥልጣን የጨበጣችሁ የሕዝብ ወገኖች። እነ ኃይሌ ስለተሸነፉ የፖለቲካ ሕይወታቸውን ሙሉ "ተማሪና ምሁር ከገበሬውና ከሰራተኛው ጋር ተዋሀድ፣ ከነርሱ ተማር፣ መልሰህም አስተምራቸው፤ አብረህም በመሰለፍ አዲሲቷን ኢትዮጵያ መስርት" በሚል ተደራጅተው ለማደራጀት ቢጥሩም ለቤተመንግስት ሽኩቻ ብቻ የኖሩ ፈሪዎች ይሆናሉ።

ለዛሬ የፖለቲካ ዓላማ ሲል የትላንት አካሄዱን ለማስተካከል ለሚነሳ የአቶ ሐጎስ ዓይነት አሸናፊ ታሪክ መጻፍ የካላሺን ምላጭ የመሳብ ያህል ቀላል ነው። በተቻለው ገለልተኛ ሆኖ ወጣ ገባና ጠመዝማዛ መንገዱ ጥሎ ያለፈውን ፈር ለመመርመር ለሚነሳ ግን በጣም አስቸጋሪ ነው። ታሪክ መጻፍን አስቸጋሪ ከሚያደርጉት ምክንያቶች አንዱ ታሪክ በየወቅቱ የተለያዩ ትውልዶችን የተለያዩ ዓላማዎችን የሚከተሉ የተለያየ ጥቅም ሕልምና ቅዠት የነበራቸውን ግለሰቦች፣ ቡድኖች፣ መደቦች ይዞ የሚፈስ የማያቋርጥ ወንዝ እንጂ እየተመላለሱ በባልዲ እየጠለቁ ይዘቱን መመርመር የሚቻል የተኛ ውሀ ባለመሆኑ ነው። እኔ ካንተ የበለጥኩ ጀግና ስለሆንኩ የኔ ዓላማ ካንተ ዓላማ የበለጠ ቅዱስ ስለሆነ ባገራችን ከዚህ ዘመን እስከዚህ ዘመን የፈሰሰውን የታሪክ ወንዝ ዓይነተኛ የሚያደርገው የኔ ገድል ነው ማለት አይቻልም። ለምሳሌ አቶ ሐጎስ እኔና አንተን እንውሰድ። የርዕሰ ብሄራችሁ እኩያ ከሆንክ እኔ በአራት ኪሎ አደባባይ በሰፊው ሕዝብ ስም ከጥቂት ሺህ የእድሜ እኩዮቼ ጋር የኃይለ ሥላሴን መንግስት በድንጋይ ሳርበደብድ አንተ እንደብዙ





የእድሜ እኩዮችህ ጢብጢብ ትጫወት ነበር። ሀያ ዓመታት ያህል ቆይተን ወደታሪክ መድረክ ብንመለስ ደግሞ አንተ በአሲምባ ተራራ ደርግን በጥይት ስታርበደብድ እኔ እንደብዙው ሚሊዮን የኢትዮጵያ ሕዝብ ሁሉ፣ ቀን በቀን ለእለት ጉርሴ እየሸቀልኩ ከግል ሕይወቴ ችግሮች ጋር እተናነቅ ነበር። (እዚህ ላይ የሸቀላው ዓይነት አስር አፎች የሚበሉትን ለማምረት ደፋ ቀና ሲሉ መዋል ይሁን በገበሬ ሕብረተሰብ ውስጥ የግጭት ምክንያቶች በሚል ርዕስ ዩኒቨርሲቲ ሴሚናር መስጠት፤ ማለት ለምፈልገው ልዩነት አያመጣም። የምንተናነቃቸው ችግሮችም ቢለያዩ እንደዚሁ)። እንግዲህ በሁለቱ ወቅቶች የኢትዮጵያ ሕዝቦች ታሪክ የሚባለው የማንኛችን ታሪክ ነው? የኢትዮጵያ ታሪክ ሲጻፍ ለየትኛው መቶ ገጽ ለየትኛው አስር መስመር ይሰጣል? አሸናፊው ለራሱ ሺህ ገጽ አውሎ ለተሸናፊ ለስድብ ያህል አስር ገጽ ቢተርፈው ነው። ተሸናፊው ስለአሸናፊው ግፎች አስር ገጽ መድቦ ስለራሱ እሮሮ መቶ ገጽ ይቸከችካል። "ነባሪያዊ" የተባለ የአንድ ሕዝብ ታሪክ ለመጻፍ በጣም አስቸጋሪ ነው።

ምናልባት በውል የሚታወቅና እንደዚህ ተኖረ ሊባል የሚችል የግለሰቦችና እስከተወሰነም ደረጃ የአንድ ወጥ ድርጅቶች ታሪክ ስለሆነ እርሱን መጻፍ ትንሽ ይቀል ይሆናል። ከነዚህ ግለሰቦች ወይንም ድርጅቶች መሀል አንዳንዶቹ የታሪክ ወንዝ አቅጣጫ ሲለውጥ ሕብረተሰባቸው ያለበትን መርከብ ይቀዝፉ የነበሩ መሪዎች ይሆኑና የነሱ ታሪክ ከራሳቸው አልፎ ስላለፉበት የታሪክ ወቅት ማዕበል ስለወከሏቸው መደቦች አፈጣጠርና እድገት ብዙ ፍንጭ ሊሰጥ ይችላል። የነሱ ታሪክ ለወቅቱ ለመደቡ

የተወሰነ ተወካይነት ሊኖረው ይችላል። ከአፄ ቴዎድሮስ እስከ ኃይለ ሥላሴ ያሉትን የኢትዮጵያ ነገሥታት በዚህ ዓይን ማየት ይቻላል።

ዳሩ ግን፣ የዚህ ዓይነት “ተወካይነት” ሊኖራቸው የሚችልም መሪዎችና ድርጅቶች ታሪክ አወዳሾች እጅ ገብቶ ይጨማለቅና እንኳን የሕዝብንና የአገርን የሚመለከታቸውን ግለሰቦችና ድርጅቶች ሕይወት ማሳየት የማይችል ይሆናል። (ወይንም በአስቂኝ መልኩ የዛሬ ሰላሳ ዓመት ማተሚያ ቤት ገብቶ እስካሁን መውጣት እንዳቃተው የቻይና ኮሙኒስት ፓርቲ ታሪክ ይሆናል። እዚያው ማተሚያ ቤት ሆኖ፣ እገሌ አጥፍቶ እንጂ አልምቶ ስለማያውቅ ከመጽሀፉ ውስጥ ይውጣ ሲባል፣ ትላንት ተስፈንጣሪ ተብሎ የተወገዘው መልሶ እራሱ አፈናጣሪ ሲሆን፣ ከስርዝ ድልዝ ብዛት ነው መሰለኝ እስካሁን ኦፊሴላዊ የሆነ የቻይና ኮሙኒስት ፓርቲ ታሪክ አልወጣም።)

በሌላ በኩል ደግሞ መሪ የተባለ ሁሉ አገዛዙ የግድ “ታሪካዊነት” አለው ማለት አይደለም። የታሪክን ወቅት ወይንም የመደብን ጥቅም ሳይሆን “አንድ እራሳቸውን” ወክለው “የታሪክን ሕግ” ተከትለው ሳይሆን የታሪክን ትርምስ ተጠቅመው በጀብደኝነት ወይንም የወቅቱ “የታሪክ ሰው አልባነት” አሳክቶላቸው በሎተሪ ስልጣን ላይ የሚወጡ መሪዎችም አሉ። ለኔ መንግስቱና መለስ እንደዚህ ዓይነት ሎተሪ አሸናፊዎች ናቸው።

መንግስቱ ኃይለማርያም የሚቀዝፋትን መርከብ እንኳን በታሪክ አቅጣጫ ወደፊት ሊያራምዳት ቀርቶ ካገኘው ጋር ሁሉ እያላተመ





ውልቅልቋን ነው ያወጣት። በሆነ መደብ ጥቅም ሕብረተሰቡን ሊያደራጅ ቀርቶ የመጣበትን የወታደር ክፍል እንኳ በናንተ ሰርጎ ገብነት በሚያስጠረጥረው ሁኔታ በውዞና አተራምሶ ሲሸነፍ ለዕለት ጉርሱ የምትሆነውን ይዞ ዚምባብዌው ገባ። ባለፉት አስራ አምስት ዓመታት ሲሞከር የነበረው የዚህን ሰውዬ ታሪክና ድርጊት የኢትዮጵያ ሕዝብ ታሪክ አንቀሳቃሽ ሞተር አድርጎ ለማቅረብ ነበር። ይህን በስልጣኑ ያጨበጨበ ቁማርተኛ።

ቁማርተኛ ሁሉ በገንዘቡ የሚያጨበጭብ አይደለም። በሎተሪ በሚያገኘው ገንዘብ በሚገባ ተጠቅሞ ለወዳጅ ለዘመድ የሚተርፍም ቁማር በላተኛ አለ። መለስ ዜናዊ የትኛው ዓይነት (የሥልጣን) ቁማርተኛ እንደሚሆን ገና አልለየለት ይሆናል። እርሱ ለራሱ ምን ዓይነት ሰው እንደሆነ አላውቅም። አቶ ሐጎስ እንዳንተ ዓይነት በቂም በቀል ሰክሮ ውሀ ሲሉት እሳት የሚሰጥ የባቢሎን ግንበኛ ይዞ ግን ወገኑን ለቁም ነገር የሚያበቃ ቁማርተኛ ይሆናል ብዬ ለመጠበቅ ያስቸግረኛል።

የዘመናችን የታሪክ ሰው አልባነት በአገር መሪዎች ደረጃ ብቻ የተወሰነ አይደለም። የትውልዳቸውን የተወሰነ ክፍል ዓላማዎችና ሕልሞች ከስማቸው ጋር ያያያዙትን እነ ኃይሌ ፊዳን እነ ብርሀነ መስቀል ረዳን መንግስቱ ኃይለ ማርያም ስለፈጃቸው ለታሪክ የግርጌ ማስታወሻ የማንበቃ የነበርነው እንደኔ ዓይነቱ ለታሪክ ነጋሪነት ቀርተናል። እንግዲህ ከኢትዮጵያና ከፖለቲካ ጋር በቀጥታ የማይገናኘው መደበኛ ሥራዬ ፋታ ሲሰጠኝ፣ “ከግል ታሪኬ የማስታወሻ ደብተር” በሚል

አንዲት ነገር እጽፍ ይሆናል። የማዘጋጃትም ጽሁፍ የታሪክ ጽሁፍ ሳትሆን፣ ግፋ ቢል ለታሪክ ጸሀፊዎች አነስተኛ ጥሬ ዕቃ ብትሆን ነው። ይህን ዘመን ማጥናት ለሚፈልጉ ልቤንና አንጎሌን ከፍቼ ለማሳየት ያህል ነው። በግሌ ስለመኢሶን፣ ስለኢትዮጵያ አብዮት፣ ስለራሴ ርዕዩተ ዓለማዊና ፖለቲካዊ ተሳትፎ ላወራ የምችለውን ያህል በዚህ ታሪኬ ውስጥ በሰፊው እመለስበታለሁ። ለአሁኑ አቶ ሐጎስ ስለአነሳሳሀቸው ሁለት ሶስት ክሶች አጠቃላይና አጫጭር አስተያየቶች ከመሰንዘር አላልፍም።

## 4. መኢሶን ላይ ስላሉህ ክሶች አንዳንድ አስተያየቶች

እዚህ ላይ የመኢሶንን ትክክለኛ ታሪክ በማብራራት ከክስ ነፃ ላደርገው ለመሞከር አልተነሳሁም። ድርጅቱን በተለይ በሚመለከተው በኩል ስለ ድርጅቱ ታሪክ ከኔ የተሻለ የሚያውቁት ከመስራች አባሎቹ በሕይወት የተረፉት በቅርቡ ይጽፉታል ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ። ስለ ድርጅቱና ስለ ኢትዮጵያ አብዮት ግንኙነት ገና ብዙ የሚያነታርኩ ክርክሮች መካሄድ ይኖርባቸዋል። ገና ያልሰከነ የታሪክ ወቅት ይቅርና በጣም ወደኋላ ርቀው ስለሚገኙትም ወቅቶች ብዙ ጉዳይ ላይ ስምምነት መድረስ አይቻልም። ሆኖም ለዛሬ ትምህርት ሰጪ በሆነ መንገድ እስከተካሄደ ድረስ እንደዚህ ዓይነቱ ክርክር በጣም ጥሩ ነው።

አቶ ሐጎስ ከላይ ያልኩህን ሀቅ ልድገምልህና መሸነፍ የስህተተኛነት ምልክት ማሸነፍ ደግሞ የትክክለኛነት ማረጋገጫ አይደለም።





የድርጅቶችንም ታሪክ በምናይበት ወቅት በርግጥ እያንዳንዱ ድርጅት ለራሱ ጥንካሬና ድካም፣ ለድሉና ለውድቀቱ የራሱ አስተዋጽኦ አለው። የድርጅቶችን የድልና የውድቀት ታሪክ በሚገባ ለማጤን ግን ከድርጅቶቹ አልፎ የወጡበትን ሕብረተሰብ ግንኙነቶችና ቅራኔዎች መመርመር የድርጅቶቹን ታሪክ ሕብረተሰቡ ውስጥ ከሚካሄደው የለውጥ ሂደት ጋር ማገናዘብ ያስፈልጋል። እኛ ጀግኞች ስለነበርን አሸነፍን ሌሎች ፈሪዎች ስለነበሩ ተሸነፉ የሚለው ሌላ የደስታ ምንጭ ለነጠፈበት መደሰቻ ይሆን እንደሆን እንጂ የአንድን አገር ትውልድ ትራጀዲ ለመመርመር ለሚፈልግ በቂ አይሆንም። እኔ እንደማምነው የናንተን ድል ሆነ የመኢሶንንና የኢሕአፖን ውድቀት በጠቅላላው የኢትዮጵያን አብዮት ያለፉትን መቶ ያህል ዓመታት የኢትዮጵያን ታሪክ ዓይነተኛ ከሚያደርጉት ሁለት ሂደቶች ጋር አያይዞ ማጥናት ያስፈልጋል። እነዚህም ሂደቶች የሚከተሉት ናቸው።

**አንደኛ** ከተለያዩ ውጥንቅጣቸው ከወጣ ብሄረሰቦች አንድ ወጥ አገር ለመመስረት የተጀመረው ሂደት፣ ይህ ሂደት ያስከተላቸው ለውጦችና ቅራኔዎች፣ የዚህም ሂደት ቢያንስ በተጀመረ መልኩ መክሸፍ

**ሁለተኛ** ከዚህ አንድ ወጥ አገር ለመፍጠር ከተጀመረው ሂደት ጋር ተጣምሮ የተካሄደው "ኢትዮጵያን ዘመናዊ የማድረግ ሂደት" ይህ ሂደት ያስከተላቸው ለውጦችና ቅራኔዎች፣ የዚህም ሂደት አሮጌውን ማበስበስ እንጂ አዲሱን ማለምለም አለመቻል

እነዚህን ነጥቦች ለማብራራት ብሞክር ይህንን እየረዘመ ያስቸገረኝን ደብዳቤ የበለጠውን ማለቂያ ያሳጣብኛል። ልጽፍ በማቅደው የብሄረሰቦች ጉዳይ እመለስበቸዋለሁ፤ ለአሁኑ ያህል ምን ማለቴ እንደሆነ እንዲታወቅ ያህል ብቻ ሁለት አስተያየቶችና ከነርሱ የሚከተሉ ሁለት መደምደሚያዎች ጠቀስ አድርጌ አልፋለሁ።

በኔ ግምት ባንድ ወገን ያለፉትን ሀያ ዓመታት የኢትዮጵያ የፖለቲካ መድረክ "የረቡ መደቦች" ሳይሆኑ በአመዛኝ የተማሪዎችና የወታደሮች መፈንጫ ያደረገው፣ እስካሁንም "ሲቪል ሕብረተሰብ" (በግራምሺ[21] ትርጉሙ) ለመመስረት ያልተቻለው፣ ለወደፊቱም አስቸጋሪ የሚሆነው በነዚህ ሁለት ሂደቶች መክሸፍ ምክንያት ነው። በሌላ በኩል ደግሞ ካለፉት ሀያ ዓመታት ትርምስና እልቂት የብሄረሰቦች ንቅናቄዎች (EPLF እና TPLF) አሸናፊ ሆነው የወጡት በዚህ ምክንያት ነው። ከዚህም በመነሳት የሚከተሉት ሁለት መደምደሚያዎች ላይ ደርሻለሁ።

**አንደኛ:** የኔ ትውልድ አባሎች በዚህ ኢትዮጵያን ዘመናዊ የማድረግ ሂደት ውስጥ ሶስትና አራት ፋብሪካዎች አይተን ካፒታሊዝም እያደገ ነው፤ በደንብ እንዳያድግ ግን እንቅፋቶች ይዘውታል ብለን እነዚህን እንቅፋቶች በሶሻሊዝም ለማስወገድ ስንሮጥ ነው ባፍጢማችን የተደፋነው። ለነገሩ ማርክስ በዘመኑ ኋላቀር የነበረችውን ጀርመንን አስመልክቶ የሚያሰቃየን የካፒታሊዝም ማደግ ብቻ ሳይሆን በሚገባ አለማደጉም ጭምር ነው ባለው

21.Gramsci, Antonio. (1971). "State and Civil Society." In Selections from the Prison Notebooks.. International Publishers: New York.





መሰረት ለዚህ ሥቃይ መፍትሄ ፍለጋ ነበር። ማርክስ እንኳን "የሕብረተሰብን የምጥ ስቃይ መቀነስ እንጂ የእርግዝና ዘመን ማሳጠር አይቻልም" ብሎም አስተምሮ ነበር። አሻሻሉት የተባሉት እነሌኒንና እነማኦ ናቸው አጣድፈውን አገራችንን ያላረገዘችውን ሶሻሊዝም ውለጂ ስንላት ከነካፒታሊዝሙ ያስወረዳት። የሆነው ሆኖ ከዚህ ሁሉ የዛሬ መደምደሚያዬ፤ አገራችንን ከድህነት ማውጣት ከተፈለገ የሶሻሊዝም ህልም ብቻ ሳይሆን የካፒታሊዝምም ተስፋ መቀበር አለበት።

**ሁለተኛ:** ኢትዮጵያ የብሄረሰቦች እስር ቤት እንደነበረች ተቀብላችሁ "ለአንድነት በእኩልነት" ቆመናል የምትሉትም ብትሆኑ፣ በመጠኑም ቢሆን የብሄረሰቦች ማቅለጫ የሆነችውን ዲባባዎች ደበበ፣ ጦናዎች ጠና የሆኑባትን፣ "ንፁህ ጦቢያኖች" የሚበዙባትን አዲስ አበባን እያየቻሁ፣ አገራችን የታጠረችበት መቶ ዓመት የማይሞላው ካብ ሲሚንቶው አልይዝ ብሎ ሲሰነጣጠቅ እያየን ጥቂት ተንኮለኞች በመዶሻ ሊያፈርሱት የሚጥሩት፤ በራሱ ግን የሶስት ሺህ ዓመታት ማዕበል የተቋቋመ ጽኑ አጥር አድርጋችሁ የመውሰድ ስህተት እየፈጸማችሁ ነው። ኢትዮጵያን ከመበታተን ልናድናት የምንችለው ያልነበረን አንድነት ለመመለስ በመነሳት ሳይሆን የሌለን አዲስ አንድነት ለመመስረት በመታገል ነው። አፄ ዮሐንስ ሳያገባድዱት ቀርተው ሚኒሊክ ያጠናቀቁት የግንብ አጥር በየቦታው መሰንጠቅ ሲጀምር፣ አጼ ዮሐንስ ተመልሰው መጥተው

ሊያድሱት ቢሞክሩ ሌላ መቶ ዓመት ይቅርና አስር ዓመት መያዙንም እንጃ። ሌላ ለ21ኛው ክፍለ ዘመን የሚሆን በአጥንት የማይማገር፣ በደም የማይለሰን አዲስ የግንብ አጥር መስራት ነው የሚበጅ። የብሄረሰቦች ጥያቄ ካላሺናዊ "መፍትሄ" እያገኘ እንዳይሄድ አስተዋጽዖ ለማድረግ ይህን ሀቅ መቀበል ያለባችሁ ይመስለኛል። (ሌላው አስተዋጽዖ ደግሞ ስለኦሮሞ ብሄረሰብ ጭቆና ሲነገራቸው ስለአማራ ገበሬ ድህነት ማውራት ለሚጀምሩት ወንድሞቻችንና እህቶቻችን ስለብሄረሰብ ጭቆና ምንነት የማስረዳት ኃላፊነት መውሰዱ ነው። የአባት ወይም የአያታችን ስም በ"ሳ" ለሚያልቀው ይህን ማስረዳቱ አስቸጋሪ እየሆነ መጥቷል። የአንዳንዱ የኢትዮጵያ ፍቅር ከፍተኛ ከመሆኑ የተነሳ አቅፋለሁ ብሎ አንቆ እንደሚገድል ስለማይታወቀው በጥርጣሬ ዓይን ነው የሚያየን)።

አቶ ሐጎስ፣ ይህንን እኔም በአመዛኝ ጥያቄ እንጂ መልስ ያላገኘሁለት ውስብስብ ጉዳይ እዚሁ ላይ ላቁምና ወዳንተና መኢሶን ላይ ወደ ሰነዘርካቸው ክሶች ልመለስ። ካላሸኗ ነች እንጂ አቶ ሐጎስ በብዕርስ የማትጎዳ እንዲያውም የምታመች ባላጋራ ነህ። እዘርራለሁ ብለህ የምትሰደው የብዕር ቡጢ የኮረኮርከውን ያህል ነው የሚያስቅ። ለምሳሌ በጽሁፍህ ላይ ረዥም ቦታ የሰጠኸውን ኃይሌ፣ ለሆኑ ወታደሮች የሰጠውን ቃል እንውሰድ።





(እንደማስታውሰው ይህን ያገኘኸው ኃይሌ መጀመሪያ የሰጠው ቃል ውስጥ ሳይሆን ትንሽ ቆይቶ የመኢሶን መዝገቦች ውስጥ ከተገኘ ማስታወሻ ተነስተው ኃይሌ ስለዚህ ጉዳይ የሚያውቀው ነገር እንዳለ ጠይቀውት የሰጠው መልስ ውስጥ ነው)። ያቀረብከው የመኢሶንን ወታደሩ ውስጥ የመግባት ጉጉት (ስለዚህም በአቋራጭ ስልጣን የመያዝ እቅድ) ለማጋለጥ ነው። ኃይሌ መልስ ውስጥ ግን ኩዴታ አንፈልግም ለአብዮቱ መስራት ከፈለጉ በየሄዱበት ሁሉ በሕዝቡና በሰራዊቱ መሀል አንድነት ይመስርቱ አልናቸው ነው የሚል። መኢሶን ከደርግ ጋር ስልጣን ተቀራምቶ ለመግዛት መነሳቱን ለማጋለጥ የኃይሌን ቃል ትጠቅሳለህ። የኃይሌ መልስ ውስጥ ግን ደርግ የፖሊት ቢሮ ስሩልንና ስልጣን ተጋሩ ሲላቸው፣ በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ አንድ ፓርቲ ማቋቋም ትክክል ስላልመሰለን መጀመሪያ ዲሞክራቲክ መብቶች ተፈቅደው ተራማጆች ሁሉ እንዲደራጁ ማገዝ ነው አልን የሚል ነው የሚነበብ።

አንድ ትልቅ የተፈፀመ የመኢሶን ወንጀል "ግብዙ መኢሶን ለመፈርጠጥ በሚዘጋጅበት ወቅት" ከTPLF የቀረበለትን የአቋም ማብራሪያ ጥያቄ በቀላሉ ተመለከተው የሚል ነው። ኃይሌ ቃል ውስጥ ለተነሱት ጥያቄዎች የመኢሶን ስም ሳይነሳ መልስ እንዲሰጥ መወሰኑ ተጠቅሷል። ከዚህ የበለጠ ለመጀመሪያ ግንኙነት ምን መደረግ ነበረበት? በሕጋዊ መድረክ ላይ ከመንግስት ጋር የሚሰራ ድርጅት በመንግስት ላይ ጠመንጃ ካነሳ ድርጅት ጋር በጽሁፍ ለመገናኘት ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ እንዳለበት ግልጽ ይመስለኛል። ይህ ክስህ ከድሮ የመጽሀፍ

ቅዱስ ንባቤ አንድ ታሪክ ትዝ አሰኘኝ። እምዬ ማርያም ክርስቶስን አርግዛ ሳለች፣ የነማርያም መቅደላዊት ጵንስ ሳይቀር በመለኮት እርዳታ የእግዚአብሄር ልጅ መፀነስዋን አውቀው ለክርስቶስ ገና እናቱ ሆድ ውስጥ እያለ ሰገዱለት ይላል። አቶ ሐጎስ የያኔው የመኢሶን አመራር መልስ ካነሰብህ፣ በትግራይ ተራሮች ውስጥ ኢትዮጵያን የሚያድን ድርጅት ተፀንሷልና ሂዱ ስገዱለት የሚል መለኮታዊ ራእይ ገና አልታየው ስለነበረ ነው ትግራይ ድረስ መጥቶ ለእናንተ ያለመስገድ ስህተት የፈፀመውና ይቅርታ አድርግለት።

አቶ ሐጎስ፣ እንደዚህ ዓይነቶቹን ማጋለጫዎች እስቲ ጨምርልን። ለምሳሌ ያህል ከደርግ የወረስከው መዝገብ ውስጥ ኃይሌ ቃሉን ሰጥቶ ከጨረሰ በኋላ መርማሪው ስለኤርትራ ያለህን አቋም ጻፍና ስጠኝ ብሎት የጻፈለት ጽሁፍ ሳይኖር አይቀርም። እስቲ አትምና ኃይሌን አጋልጥበት። ዶክተር በረከት የሚባል ለስሙ የሕግ ምሁር የጻፈው መጽሀፍ ውስጥ «መኢሶኖች ሚሊሽያ አሰልፈው ኩዴታ ሊያደርጉ ሲሞክሩ ተነቅቶባቸው ተሰወሩ» ይላል። ሲወራ ሰማሁ ሳይሆን በርግጠኝነት! እስቲ መዛግብቱን ስጠውና አንዲት ማረጋገጫ አግኝቶ ያጋልጠን። አንተም አቶ ሐጎስ ከነዚህ መዛግብት ውስጥ “ውጋጋን” የሚል የመኢሶን የውስጥ ጋዜጣ ሳታገኝ አልቀረህም። እስቲ ለምሳሌ ከደርግ ጋር እንስራ አንስራ የሚለው የውስጥ ክርክር የተካሄደበትን አትምና መኢሶን በቤተ መንግስት ሽኩቻ በአቋራጬ ዙፋን ላይ “ቂጥ ለማለት የተነሳ ድርጅት” መሆኑን አጋልጥበት፤ አትመህ እንድታጋልጠን የምለምንህን ያህል ይህን ሕዝብ አረደ





የምትለውን ድርጅት ሊታረድ የቀረበ ያህል የዋህነቱን ያረጋግጣሉም ብለህ እንዳታጠፋቸው እማጸንሀለሁ።

የጽሁፍህ ማሳረጊያ የክስህ ማያያዣ ሀረጎች የሚቋጠሩበት ቦታ ነው። ስለዚህም በሰፊው ልጥቀሰውና አስተያየቴን ልስጥበት።

> **ከ1969 ዓ.ም ጀምሮ ደርግ መኢሶን ላይ ፊቱን አዞረበት። ያኔ ታዲያ መኢሶን ምን ይዋጠው? ወደ ሕዝቡ እንዳሄድ ሲያርደው ነው የከረመ። እንደተለከፈ ውሻ ሲባዝን ከርሞ እምጥ ይግባ ስምጥ ሳይታወቅ ደርግ ሲፈረጥጥ ብቅ አለ። ከወደዋሺንግተን ኢዲኃቅ የተሰኘ መለመኛ ስልቻውን አስፍቶ የሥልጣን ነገር አትርሱኝ ጌቶቼ ይላል አሁንም።መንግስቱ ጌታቸው ይርዳቸው፣ እርሱ ይስጣቸው እንጂ የኢትዮጵያ ሕዝብ እንደሆነ ያረዱ ያሳረዱትን መቼ ይዘነጋቸዋል?**

ስልቻው መለመኛ፣ የሚለመነው ደግሞ ስልጣን፣ ተለማኞቹ መንግስቱ አሜሪካና የኢትዮጵያ ሕዝብ መሆናቸው ነው። መንግስቱ የሚሰጠው ስልጣን ስለሌለው እናስወጣው። የዋሺንግተኑም ጌታ በመምሪያ ሀላፊው አማካይነት የማንን ስልቻ በስልጣን እንደሞላ ለማወቅ ለንደን ስብሰባ ላይ መገኘት አያስፈልግም። የኢትዮጵያ ሕዝብ ይቀራል። ደርግም የጨፈጨፋቸው ጓደኞቼን ገበሬ ፈጃቸው ብሎ ነበር ያስወራው። አንተም እንግዲህ መኢሶን ሕዝብ ሲያርድ ስለኖረ ሕዝቡ አልተቀበለውም ነው የምትለው። ለዚህ ያለኝ ምኞታዊ መልስ፣ እስቲ ካላሺንህን ቁጬ አድርግና የአቃቂ ወዘደር፣ የአርሲ፣ የኢሉባቦር፣

የወለጋና የሲዳሞ ጭሰኛ እኔን በመኢሶንነቴ አርዶኛል ብሎ ሲተፋኝ አንተን ነፃ አውጭዬ ብሎ ዘሎ ሲያቅፍህ እንደ የሚል ይሆናል።

አቶ ሐጎስ፣ በትግራይ ብቻ አይደለም "ትግል የነበረው"። መሬት ለአራሹ የሚባል አዋጅ ነበር። ይህም አዋጅ በተለይ በደቡብና በምዕራብ ኢትዮጵያ በጭቁን ገበሬዎች ላይ ለዘመናት ጭሰኝነት ያሰፈረን የመሬት ሥሪት ያስወገደ አዋጅ ነበር። መኢሶኖች ይህን አዋጅ ሥራ ላይ ለማዋል ከበሬው ጎን ተሰልፈው በግንባር ቀደምትነት ታግለዋል። ያኔ ገበሬ ለማረድ ተነሱ የሚባሉት አዋጁን የተቃወሙት ነፍጠኞች ነበሩ። ስለዚህም ቢያንስ ለዛሬው ፖለቲካህ የሚጠቅምህ ነፍጠኞች አረዱ ብትል ነው። የኦሮሞና የሌሎች ጭቁን ብሄረሰቦች በጠቅላላው ጭሰኝነት በሰፈነባቸው አካባቢ መኢሶን ሕዝብ አረደ የሚለው እነማን ጋ ተቀባይነት ያገኝልኛል ብለህ እንዳሰብክ አልገባኝም።

እንደኔ፣ እንደኔ ይህን በአገር ውስጥ ፈርጣጩን መኢሶን፣ አስገንጣዩን ወያኔና ተገንጣዩን ሻዕቢያ ከማውገዝ አልፎ ባህር ማዶ በመሻገር ከጊዜ ወደ ጊዜ እያዘቀጠ የሄደውን የቻይና ኮሙኒስት ፓርቲ ሲኮንን የኖረ ሕዝብ ትንሽ እረፍት ብንሰጠው ደስ ባለኝ ነበር። ይህ እኛ መኢሶኖች አርደነው የተፋን ሕዝብ እናንተ ላይ ፍቅር እንደጣለው የሚያሳይ ግጥም መጽሄታችሁ ይዟል።





የዓይኔ ብርሀን አለኝታ መኩሪያዬ እድሜ ለኢሕአዴግ ሞላ ጎተራዬ

የአፍሪካ ሕዝብ መቸም የመጣን ገዥ አሞጋሽ አዝማሪ እንዲሆን ተፈርዶበታል፤ ይሁን። ግን ምናለ የኢትዮጵያ ገበሬ ጎተራው ሞልቶ ከስንዴ ልመና እስክንወጣ መቆየቱ ቢርቅባችሁ "ነፃ ካወጣችሁት" ወዲህ የዘራውን እስኪያስገባ የአንድ ዓመት መከር እንኳ ብትጠብቁ?

አቶ ሐጎስ፣ የኢትዮጵያን ሕዝብ ከዚህም የተሻለ ግጥም ልታዘፍነው ትችላለህ። ነገሩ ሥልጣን እስከያዝክ ድረስ ብዙም ሞያ የሚጠይቅ አይደለም። አሁንም ሌላ ውርርድ እንግባ። ለአንድ ሳምንት ሥልጣን አውሰኝና ወታደራችሁ ከመቀሌ እስካዲስ አበባ ሕፃናትና ሽማግሌዎች እየፈጀ ነው የመጣ። አዲስ አበባን ይዛችሁ ወደ ደቡብ ካለፋችሁ ወዲህ ደግሞ በአፍሪካ ውስጥ ያሉ መኪናዎች ቢሰበሰቡ ሊሸከሙት የማይችሉት እህል እያስጋዛችሁ ነው እያልኩ "ታሪካዊ ማጋለጫዎቼን" እደረድርልሀለሁ። በየመሸታ ቤቱ ዛሬ የሚወሩትን በሬዲዮና በቴሌቪዥን የማስወራት ጉዳይ ነው። ሰልፍም ቢያስፈልግ የማደራጀት ችግር አይኖርብኝም ነበር፤ ሕዝቡ ራሱ በቁጣ ገንፍሎ ሲወጣ ለትራፊክ የተዘጉ መንገዶችን ዝርዝር በሬዲዮ መግለጽ ብቻ ይበቃል።

አቶ ሐጎስ ትንሽ ቁም ነገር እናውራ ካልን፤ ለመኢሶን መሸነፍ ምክንያቱ የወኔ መጥፋት ወይንም በሕዝብ የመተፋት ጉድይ አልነበረም። መኢሶን በትልልቅ ከተሞች በተለይ በአዲስ አበባ ወጣቶች ብዙሀን ዘንድና ቢሮክራሲው ውስጥ በጠቅላላው በከተማው ንዑስ ከበርቴ

ዘንድ ተቀባይነቱ ይህን ያህልም እንዳልነበረ ከላይም አንስቻለሁ። (በነገራችን ላይ አቶ ሐጎስ፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ ለኢሕአዴግ የፍቅር ዘፈን መዝፈን ጀምሯል ትላለህ እንጂ፣ እናንተንማ አዲስ አበባ የጠላት ግዛት ውስጥ ያላችሁ ያህል ሆኖ እንደሚሰማችሁ ምን ብናደርግለት ይወደናል የሚለው ጥያቄ ጭንቅላታችሁን እየበጠበጠ እንደሆነ መገመት እችላለሁ። ከላይ የጠቀስኩት የጀርመን ጋዜጠኛ ይህንኑ ተረድቶ ዓይን የሚገድል ቢሆን ኖሮ አዲስ አበባ ያለው የኢሕአዴግ ሰራዊት ይሄኔ አልቆ ነበር" ብሎ ጻፈ)።

መኢሶን አዲስ አበባም ቢሆን በተለይ በንፋስ ስልክና በአቃቂ ወዘደሮች አካባቢ በተለይ የኦሮሞ ገበሬዎች በሚበዙበት የኢትዮጵያ ክፍል እውነተኛ የሕዝብ ድጋፍ እንደነበረው መኢሶንንም ጠልቶ መጠራጠር የሚቻል አይመስለኝም። ቢያንስ እናንተን በትግራይ የትጥቅ ትግል ካስጀመረ የሕዝብ ድጋፍ ይበልጥ ነበር። ለመኢሶን ቢያንስ በቶሎ መሸነፍ ዋነኛው ምክንያት ይህንን ፖለቲካዊ ድጋፍ ወደ ድርጅታዊና ትጥቃዊ ጥንካሬ መለወጥ አለመቻሉ ነበር። ታዲያ ይህን ለማድረግ ለምን አልቻለም? ይህን ጥያቄ በሚገባ ለመተንተንና ለማስረዳት የድርጅቱን የራሱን ታሪክ የድርጅቱንና የኢትዮጵያን አብዮት ግንኙነት አብሮ ማጤን ያስፈልጋል። ለአሁኑ እዚህ ውስጥ ሳልገባ ሁለት ምክንያቶች በጣም ባጭሩ እጠቁማለሁ።

የመጀመሪያው ምክንያት፣ የመኢሶን ለሕቡዕና ለትጥቅ ትግል ድርጅታዊ መዋቅራዊና እውነቱን ለመናገር ስነ ልቦናዊም ዝግጅት





የሌለው መሆን ነበር። እነ ተኮላ የብዙዎቹን መኢሶኖች የውስጥ እግር ሲተለትሉ እየለሰለሰባቸው "ይህ ነበር ለረዥሙ ጉዞ የተዘጋጀው?'' እያሉ ይቀልዱ ነበር። ኢሕአፓ ገና ግድያ ሳይጀምር በፊት በጎህ መጽሄት ላይ "ባንዳ ሁሉ ትግል በብዕር ብቻ መስሎሀል" ሲለን ገና ለአመጽ እንዳልተዘጋጀን ነቅቶብን ነው። የሸጉጥ ኢላማ ተለማመድ የተባለ አንድ የኔ ቢጤ የመኢሶን አባል "እግዜር ይጠብቀኝ እንጂ ተታኩሼ ልተርፍ ነው?'' ያለው መሀላችን ብዙ የሳቅንበት ቀልድ ነበር። አቶ ሐጎስ፣ እነዚህ እጅህ የሚገኙትን የመኢሶን መዛግብት በቅንነት ብትመረምር መኢሶን የሕዝብ ፍቅር የሚባል የማይጨበጥ ገመድ በጓደኝነት አስተሳስሮአቸው የሚጓተቱ ወንድምና እህቶች ያሰባሰበ እንጂ፣ ለትጥቅ ትግል ቀርቶ በሌኒን "ለአንድ ጓድ የተጻፈ ደብዳቤ" ውስጥ ባሉት መመሪያዎች መሰረት እንኳ የተዋቀረ ድርጅት እንዳልሆነ በቀላሉ ማየት በቻልክ ነበር።

በሌላ በኩል፣ ይህን ሀቀኛ የሆነ የሕዝብ የሆታ ድጋፍ "ሕዝብ ውስጥ ገብቶ ቅቡልነት ማግኘት" ወደሚያስብል የሥልጣን መሰረት የሆነ ድጋፍ ለማሳደግ በተለይ ለገበሬው ማርክስ በግልጽ እንደሚያስቀምጠው "አጋርም ጌታም" ሆኖ መቅረብ ያስፈልጋል። የተወሰነ ድርጅታዊ ጥንካሬ ያስፈልጋል ማለት ነው። ከዚህ አልፎ በገበሬው ላይ የተደገፈ የትጥቅ ትግል ለማካሄድ ደግሞ ማኦ በጽሁፎቹ ብዙም ሳይሸፋፍን ደጋግሞ እንደሚያስተምረው "እንዳይከዳህ የምታስፈራራበት እንዲያግዝህ የምታገለግልበት፣ የተወሰነ የትጥቅ ኃይል ያስፈልግሀል" ከዚያ አሁንም ማኦ እንደሚገልጸው "የጠላት ቦምብ አንተን ከመደገፍ

በቀር ሌላ ምርጫ እንዳይኖረው ያደርግልሀል”። (አቶ ሐጎስ፡ ማኦ ጽሁፎች ውስጥ በምቦች ሰለጣለለት የጃፓንን ኢምፔሪያሊዝም የሚያመሰግንባቸው በታዎች ትዝ ይሉሀል? እናንተም “በሆዳችሁ” ደርግን ታመሰግኑ ነበር?) ያም ሆነ ይህ ሕዝባዊ ጦርነት ምን ያህል ሕዝባዊ ነው የሚለው ክርክር ውስጥ ለመግባት አይደለም። እርሱን ማካሄድ አለመቻል በሕዝብ የመተፋት ምልክት እንዳልሆነ ሁሉ በርሱ ምክንያት ማሸነፍም በምንም ዓይነት የሕዝባዊነት ማረጋገጫ አለመሆኑን ለመጠቆም ያህል ብቻ ከናንተ ጋር ተያይዞ ስማቸው በኢትዮጵያ የተነሳውን እነ ፖል ፖትን እጠራለሁ። እነሱም በዚሁ የትጥቅ መንገድ “ቅቡልነት” አገኙን ባዮች ነበሩ።

ሁለተኛም፡ መኢሶን ከመጀመሪያ ውድቀቱ በኋላ እንደገና አንሰራርቶ የትጥቅ ትግል ለመጀመር ላለመቻሉ አንዱ ምክንያት፤ የድርጅቱ መዋቅራዊ ችግሮች ብቻ ሳይሆኑ፣ ከብዙ የኢትዮጵያ ብሄረሰቦች የተውጣጡ አባሎች ያቀፈ ድርጅት መሆኑ ይመስለኛል። (እስር ቤት ስለነበርኩ ያልተሳተፍኩበት የመኢሶን የታሪክ ምእራፍ እንደመሆኑ የግል ግምቴ ነው)። በአብዛኛው የኢትዮጵያ ገጠር ውስጥ አባሎቹ ከመላ ኢትዮጵያ የመጡ ድርጅት በግራ ከየብሄረሰቡ ድርጅቶች ጋር ታግሎ፣ በቀኝ ለኢትዮጵያ አንድነት ቆመናል ከሚሉ ትምክህተኞች ጋር ታግሎ መሀል ላይ በምትቀረው ጠባብ ቦታ ላይ የመላ ኢትዮጵያ ነፃ አውጭ ንቅናቄ ለማካሄድ በጣም አስቸጋሪ ነው የሚሆንበት። የየብሄረሰቡ ድርጅት የራሴን ብሄረሰብ ነፃ የማውጣ እኔ ነኝ ምን አገባህ ብሎ ይጣላሀል። የትምክህተኛው ሰፈር ደግሞ ተገንጣዮችን





የጎሳ ንቅናቄዎችን ካላወገዝክ ዓይንህን ላፈር ይልሀል። ለእንደዚህ ዓይነቱ ድርጅት ትንሽ መፈናፈኛ የሚሰጥ አዲስ አበባ ነበር።

እሱ ደግሞ የጠላት ዋና መናሀሪያ ስለሆነ ማኦ እንደሚያስተምረውና እናንተም በተግባር እንዳሳያችሁት ገጠሩን ነፃ አውጥተህ ጠላትን ድባቅ ከመታህ በኋላ እጅህ የምታስገባው የመጨረሻ ምሽግ ነው። መኢሶን በደቡብ፣ በደቡብ ምዕራብና በምሥራቅ የራሱን የመጀመሪያ የመዋቅር ድካሞች አስወግዶና ትንሽ አገግሞ የትጥቅ ትግል ልጀምር ቢል ኖሮ በሰሜን እናንተ ኢህአፓ ላይ ካደረሳችሁት ያልተለየ እድል ያጋጥመው ነበር ባይ ነኝ። ኢሕአፓን እናንተ ብዙ ከትግራይ ብሄረሰብ የመጡ አባሎቹን ዘርፋችሁና በጉልበትም አሸንፋችሁ ከትግራይ ልታስወጡት የቻላችሁት በዚሁ እኔ ለማሳየት በሞከርኩት ምክንያት ይመስለኛል። (እዚህ ላይ መኢሶን የትጥቅ ትግል ለመጀመር የነበሩትን ችግሮች ለማሳየት ስሞክር አለመቻሉ የሚቆጨኝ እንዳይመስልህ። የሚቆጨኝ ከማንችለው ባላጋራ ጋር ባደረግነው ግብግብ ያለቁት ተተኪ የለሽ ጓደኞቼ ሕይወት እንጂ ካላሺንማ በመኢሶን እጅ ከሰው ገዳይነት ወደ “ሕዝብ አድንነት” በተዓምር ስለማይለወጥ አለመሳካቱ በበኩሌ የሚያሳዝነኝ አይደለም)።

እናንተ እነዚህ የመኢሶንና (የኢህአፓም) ችግሮች ያልነበሩዋችሁ አስቀድማችሁ በአንድ ብሄረሰብ ውስጥ እንደዚህ ብሄረሰብ ነፃ አውጭ ስለተደራጃችሁ ነው። በአንድ ወጥ ብሄረሰብ መሰረትነት ላይ ተደራጅቶና ተጠናክሮ ከዚያም እስረኛን አሰባስቦ “የመላ ኢትዮጵያ

ነፃ አውጭ" መሆን ቀለልና ለየት ያለ አካሄድ ነው።አቶ ሐጎስ፣ ያንተ ቢጤዎች ሳይሆኑ ብዙም ከሳይንስ ጋር ያልተጣሉና የሚመስል ነገር የሚያወሩ የናንተ ሰዎች ስለእናንተ ድል የሚሰጡትን ምክንያቶች ለማወቅ፣ የሚያሳምኑም ከሆነ ለመቀበል ዝግጁ ነኝ። ከአሁኑ ያንተ ቢጤዎችን አልቀበልም ስል የደረሰብኝ ታሪክ ስላለ ነው። የግል ጭውውት ስለነበረ ሰውዬውንና ቦታውን ለራሴ አስቀርቼ ይዘቱን እንደሚከተለው ልተርክልህ።

የዛሬ ሶስት ዓመት ግድም ነው፤ እንኳን ኢትዮጵያን ነፃ ልታወጡ ስሙንም ገና በደንብ አልያዛችሁም ነበር። አንድ እኔ መኢሶን እርሱ የኢሕአፓ አባል ሆነን ከምንተዋወቀው ሰው ጋር ከ13 ዓመት በኋላ በአጋጣሚ ተገናኘን። ያኔ ሁለት ተቃራኒ ድርጅቶች ውስጥ ሆነንም የግል ወዳጅነታችንን ይዘን ቆይተን ስለነበርና ኃይሌንም በግል ስለሚያውቀው በኃይሌ ሞት ማዘኑን ገልጾልኝ ከኔም ጋር እንደገና በሕይወት ተገናኝተን በሰላም እንደድሮው ለመጨቃጨቅ መብቃታችን ደስ ብሎት እውነትም ጭቅጭቃችንን ወዲያው ጀመርን። ያስቀመጡት ቦታ የሚገኝ ድንጋይ ብቻ እንደመሆኑ እርሱም ከቀንደኛ አሕአፓነት ወደ እሳት የበላ TPLFነት ተዛውሮ፣ ድሮ "በቡርዥዋ ዝንባሌዎቹ" አበሽቀው የነበረ ሰውዬ እሳት የላሰ ማርክሲስት ሌኒኒስት ሆኖ ጠበቀኝ። እኔ ደግሞ ከቀንደኛ የመኢሶን አባልነት ፖለቲካ ትቼ ቀዝቀዝ ወዳለ የመኢሶን ደጋፊነት ወርጄ፣ እሳት ከላሰ ማርክሲስት ሌኒኒስትነት ወደለዘብተኛ ማርክሲስትነት ተለውጬ ነበር።(የማጨሰውም ሲጃራ





ከፊልተር የለሽ ጎልዋዝ ወደ ለስላሳ ማልቦሮ ተለውጦ ነበር። የተያያዘ ምክንያት ይኖርበት ይሆን?)

ያኔ እንግዲህ እንዳልኩት ገና ኢትዮጵያን "ነፃ" አላወጣችሁም ነበር። ሆኖም ከመኢሶንም ከኢህአፓም የበለጠ ጠንካራ እንደሆናችሁ ከሁለቱም የተሻለ የማሸነፍ ተስፋ እንዳላችሁ እኔው ያቀረብኩት "ትንተና" ስለነበረ እዚህ ጉዳይ ላይ ቶሎ ሙሉ ስምምነት ላይ ደረስን። ክርክር የተነሳው የዚህን የጥንካሬአችሁን ምክንያት መተንተን ስንጀምር ነው። እኔ የናንተ የማደራጀት ችሎታና ወኔ ለዚህ ጥንካሬ ትልቅ አስተዋፅኦ እንደነበረው አልካድኩም። የጥንካሬአችሁ ዋና መሰረት አድርጌ የወሰድኩት ግን የብሄረሰብ ንቅናቄ መሆናችሁን ነበር። ከአማራ ጋር ባለው የረዥም ጊዜ የታሪክ ፉክክር በመሸነፉ የተቆጣ እንጂ መሸነፉን ያልተቀበለ ብሄረሰብ፣ የደርግ ግጨው አጋጨው አገዛዝና የተፈጥሮ ችግር አስመርረውት ሳለ፣ እንደብሄረሰብ አደራጅታችሁ አዲስ ተስፋ መስጠት መቻላችሁ ነበር ወሳኙ። ከድርጅታችሁ ስራ ውጭ የሆኑ ሁኔታዎችም በጣም አግዘዋችኋል። የአካባቢው ሁኔታ (በጎን ሱዳን፣ ከጀርባ ኤርትራ መኖራቸው) ዓለም ዓቀፋዊው ሁኔታ (የደርግ የሶሺየት ቁልቁላ መሆን፣ የአሜሪካኖች ፀረ ሶቪየት ለሆነ ሁሉ ሆደ ሰፊ መሆን)፣ ደርግን የመሰለ የግጨው አጋጨው መንግስት ኢትዮጵያን እየገዛ መሆን ትልቅ አስተዋጽኦ አድርገዋል ባይ ነበርኩ። በተለይ አስተዋጽኦ የለውም ያልኩት የምትከተሉትን ርእዩተዓለም ነበር። አጋንኜ ሳቀርበው የጠቀሰኳቸው ሁኔታዎች እስከተሟሉ ድረስ

የጆሆቫን ምስክርነት እንኳ ብትከተሉ የዛሬ ጥንካሬአችሁን ከማግኘት አያግዳችሁም የሚል አቋም ያዝኩ።

እርሱ ደግሞ ኢሕአፓም በትግራይ ሕዝብ የተተፋው እርሱም ኢሕአፓን የተፋው ኢሕአፓ ማርክሲዝም ሌኒኒዝምን በሚገባ ስላልተከተለ መሆኑንና የናንተም ጥንካሬ ማርክሲዝም ሌኒኒዝምን በሰፊው የትግራይ ሕዝብ ውስጥ ሰርጾ እንዲገባ ያደረጋችሁት ጥረት ውጤት መሆኑን ገለፀልኝ። ፈጣሪዎቹ ራሳቸው አልረባንም እያሉ የተውትን ማርክሲዝም ሌኒኒዝም እናንተም እያሰረፃችሁ ነው ብዬ ብቀበል እንኳ የትግራይ ገበሬ ፈረደበት፤ ይኸው አሁንም ለማርክሲዝም ሌኒኒዝም ታማኝ ነኝ የሚለው የቻይና ኮሙኒስት ፓርቲ አይደለም ወይ ድንጋይ ያልያዙ ሰላማዊ ሰልፈኞችን በታንክ የሚጨፈጭፍ አልኩ።(የቴናሜን አደባባይ ፍጅት ወቅት ነበር የምንጨቃጨቀው)። ያገኘሁት መልስ፣ ጓድ ደረጀ፣ አንደኛ የምዕራብ ኢምፔሪያሊዝምን ዜና ማሰራጪያዎች አትመን።ሁለተኛ የቻይና ኮሙኒስት ፓርቲ ሳይቀር ኮሙኒዝምን ቢከዳም በትግራይ ሜዳ የተቀጣጠለው የኮሙኒዝም ችቦ ለዓለም ሁሉ ያበራል የሚል ነበር። ያኔ እየጠጣሁት የነበረው ቢራ ትን እስኪለኝ ድረስ ሳቅሁኝ! ይህን ተረት ተረት ባምን ኖሮ፣ የትግራይ ገበሬ "ማርክሲዝም ሌኒኒዝምን ከዳችሁብኝ" ብሎ አዲስ አበባ ድረስ ዘልቆ መጥቶ እናንተን አለመቅጣቱ በገረመኝ ነበር።

አቶ ሐጎስ፣ መኢሶን የተሸነፈው በወኔ ቢስነት ምክንያት በተለይ በደፈናው የሕዝብ ድጋፍ በማጣት ምክንያት አይደለም የምለው ከምን





ተነስቼ እንደሆነ ለመጠቆም የራሴን "ትንተና" ባጭሩ ለማቅረብ ሞክሬአለሁ። ጦር ሜዳ ብቻ የሚረጋገጠውን ወኔ፣ በካላሺን ድጋፍ ብቻ የሚገኘንም "ቅቡልነት" መቸውንም በተግባር ላረጋግጥልህ አልችልም። የመኢሶንን ወኔ ቢስነት እያጋለጥክ ባንተ ጀግንነት እየኮራህ መደሰትህን ቀጥል። ሁሉም ንቃቱና የባህል ደረጃው በሚፈቅድለት መጠን የመደሰት መብት አለው። ይህቺ ከትግራይ ውጭ ያለች "ቅቡልነት" ግን ያለ ካላሺን መቆም አትችልም የሚል ጥርጣሬ እኔ ብቻም ሳልሆን አንተም ስላለህ "ወሰን የለሽ ደስታ" እያገኘህበት ነው ለማለት አልችልም። ይህን ጊዜ ያሳየን ብለን ወደሚቀጥሉት ውንጀላዎችህ እንለፍ። እነሱም የመኢሶን ከደርግ ጋር መስራትና ቀይ ሽብርን የሚመለከቱ ናቸው። አሁንም አጫጭር አስተያየቶች ለመሰንዘር እንጂ ዝርዝር ውስጥ ገብቼ ለመከራከር አልሞክርም።

## 4.1 የመኢሶንን ከደርግ ጋር መስራት በሚመለከት

የድርጅቶችን ታሪክ በተሟላ ሁኔታ ለማጥናት የድርጅቶቹን ድሎችና ውድቀቶች ከድርጅቶቹ የውስጥ መዋቅር ብቻ ሳይሆን ከሕብረተሰብ መሰረታቸው ተነስቶ መመርመር እንደሚያስፈልግ ሁሉ፣ ታሪክ የታሪክ ፍትህ እንዳይጎድለው አንድን ወቅት በዚያን ወቅት ውስጥ የነበሩትን ግለሰቦችና ድርጅቶች በሚዳኝበት ጊዜ በወቅቱ የነበሩትን አስተሳሰቦችና የጨዋታ ሕጎች መነሻ ማድረግ አለበት። የማርክስን አንድ ምሳሌ ለመጠቀም በዘመነ ካላሺን መመዘኛ አቺሊስን ብንዳኘው፣ ጀብዱዎቹን

ሁሉ ለመፈጸም ባልቻለም ነበር። በሌላ በኩል ደግሞ አንድ የታሪክ ወቅት ካለፈ በኋላ ወደኋላ መለስ ተብሎ የሚደረግ እይታ የተለየ እይታ ነው፤ የ"ብልህ" እይታ ነው። ላለመሳሳት የሚያስችል እይታ ነው።

እውነትን ፍለጋ የተነሳ፣ የመኢሶንን ስህተት በሂሳዊ ድጋፍ ከደርግ ጋር አብሮ ለመስራት ከመወሰኑ መጀመር የለበትም ባይ ነኝ። ይህን ማድረግ፣ ፍራንኩ ሌላ ጋ ወድቆበት ሳለ የመንገድ መብራት ስር የፈለገው ሞኝ ዓይነት ስህተት መፈጸም ነው። ፍራንኩ የወደቀበት ጨለም ያለ ቦታ ቢፈለግ የመኢሶን ብቻ ሳይሆን የኛ ትውልድ የኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆኑ አሮጌውን ጠልተው ወደአዲሱ ለመሄድ መንገድ ሲፈልጉ ባዝነው የቀሩ የብዙ አገር ወጣቶች ስህተት፣ አቅመ ቢስነትና ለውጥ የማምጣት ጉጉት ተጣምረው ያስከተሉትን ጀብደኝነት ምክንያቶች ማግኘት ይቻላል። መብራቱ ጋር ቢፈለግ ለሀሜትና ለሀሰት ውንጀላ የሚመቹ ቅራፊዎችን መለቃቀም ነው የሚቻል።

ዋናውን ስህተት መጠቆም ከተቻለ በኋላ ከዚያ የመነጩት ስህተቶች ከሞላ ጎደል የግድ መከተል የነበረባቸው መሆኑን መረዳት ይቻላል። አማኝ አይደለሁም፣ ለመሆንም አላስብም። ለምሳሌው ያህል ብቻ ለሁለተኛ ጊዜ ለመጠመቅ ወስኜ ቄስ ውቤ ጋር ሄድኩ እንበል። ትልቁ ስህተቴ የእግዚአብሔርን መኖር መካዴ መሆኑን ነግሬ ይፍቱኝ እላቸዋለሁ።

ቄስ ውቤ ታዲያ "ማርያም በድንግልና ኢየሱስን ልትወልድ አትችልም ብለሀል"፤ "ተሰቅሎ የሞተ ሊነሳ አይችልም ብለሀል"፤ "መላኩ





ገብርኤል ለማርያም ወንድ ልጅ ትጸንሺያለሽ ያላትን ተሳልቀህበታል አያሉ መዘርዘር ቢጀምሩ፣ ምነው አባ ይህን ሁሉ መነሻ ኃጢአቴ ላይ ያገኙት የለም ወይ፤ ምን የሚሰጠውን ጉቦ ከፍ ለማስደረግ ኃጢአት እንደሚያበዛ የአፍሪካ ባለሥልጣን ይሆኑብኛል እላቸው ነበር።

በዚህ አንፃር የመኢሶንን ስህተት መፈለግ የምጀምረው "ማርክሲዝም ሌኒኒዝም የማኦዜዱንግ ሀሳቦችን" የያዝንበት የተማሪ ንቅናቄ ውስጥ ነው። ከዚህ ርዕዬተ ዓለም ተነስቶ በዚህ ርዕዩተ ዓለም መሰረት ይደረስበታል የሚባለው ዓላማ ላይ ለመድረስ በነደፈው የትግል መስመር አኳያ ከደርግ ጋር ጊዜያዊ ህብረት የመፍጠሩን ትክክለኛነት ማሳየት ይቻላል። ይህንንም እንኳን ያኔ ዛሬም ሳየው በራሱ ክፋት አልነበረውም ነው የምለው። ከመኢሶን ወዳጆቼ ጋር ዛሬም ስለዚህ ጉዳይ ስናነሳ የምጠይቀው ከደርግ ጋር ያኔ መስራቱ ያዋጣ ነበር ወይ? የሚል እንጂ ይገባ ነበር ወይ የሚል ጥያቄ አይደለም። ከናንተ ጋር መሥራት የፈለገ ብዕር እንጂ ካላሺን የሌለው ድርጅት አማክረኝ ቢለኝ ከዚህ የተለየ ጥያቄ አላቀርብም። የምጠላውን መንግስት ጥላችሁልኛል። ለመኢሶን ሂሳዊ ድጋፍ የመሬት አዋጅና ብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም መነሻ እንደሆነ ሁሉ እናንተም በፕሮግራምና በመግለጫ ደረጃ ስለዲሞክራሲና ስለብሄረሰቦች ጉዳይ የምትሉት ለሂሳዊ ድጋፍ በቂ ሊሆን በቻለ ነበር። ይህቺን ሂሳዊ ድጋፍ ያዝ የሚያስደርገኝ፣ ፖለቲከኛ ብሆን ኖሮ አብሬ ከመሰራት የሚያስቆጥበኝ የካላሺኑ ጉዳይ ነው።

በተፈጥሮው ክፉ ወይንም ደግ የሚሆን ሰው እንደሌለ ሁሉ፣ ሲፈጠር ዲሞክራት ለመሆን የተመረቀ፣ ፋሺስት እንዲሆን የተረገመ መሪ የለም። በካላሺን የፖለቲካ አቅጣጫ ማስወሰን የሚያስችል የፖለቲካና የህብረተሰብ ግንኙነት እስከሰፈነ ድረስ በካላሺን ላይ የሚያዝ ሁሉ፣ በአንድም ሰው ሬሳ ላይ ተራምዶ ከፈለገው ዓይነት "ቅዱስ" ዓላማ ላይ ለመድረስ የተነሳ መሪ ሁሉ መንግስቱ ኃይለማርያምን የመሆን እድል አለው። መንግስቱም ቢሆን ሰው ሳይገድል ቢገዛ፣ ገድሎ ይገድሉኛል ብሎ ከመሥጋት ይልቅ ሹሞ አብሮ ውስኪ ቢጠጣ ይመርጥ እንደነበረ መገመት ይቻላል። ለርሱም የስንዴ ለማኝ ከሆነ አገር ይልቅ ሀብታም አገር ቢገዛ ይሻለው ነበር። የኛ እግር ኳስ ተጫዋቾች ሌጎስ ላይ የናይጀሪያ ጥጋበኞች ዳቦ ሲወረውሩባቸው ከኛ ያነሰ የበሸቀ አይመስለኝም። ደርግን የተቃወመ የቀድሞው መንግስት ደጋፊ ነው ሲል፣ ሰደድን የተቃወመ የአብዮቱ ጠላት ነው ሲል፣ እኔን የተቃወመ የኢትዮጵያ ጠላት ነው ሲል ግራ ቀኙን እየጨፈጨፈ ኢትዮጵያን ለእናንተ ዳረጋት።

እናንተም አቶ ሐጎስ "እኛን የሚቃወም የደርግ ደጋፊ ነው" ባዮች ናችሁ። TPLF ሥልጣን ሰለያዘ የድርጅት ብቻ ሳይሆን የባዮሎጂ መታወቂያ የያዙ "ገኘ መደቦች" በየቦታው እየተፈጠሩ መሄዳቸው አይቀርም። የትግራይ ብሄረሰብ አባሎች ድሮውንም ከየትኛውም ብሄረሰብ የበለጠ በወገናዊነት እንደሚጠቃቀሙና በዚህም ምክንያት በሌሎች ዘንድ በጥርጣሬ ዓይን ይታዩ እንደነበረ አንተም የምታውቀው ነው። በናንተ ስልጣን መያዝ ምክንያት ይህ ጥርጣሬ ወደ ስጋት





ይለወጣል። ትግሬ በተራ እድር ሲገናኝ "እንኳን ሥልጣን ይዘው ድሮውንም አልተቻሉ" ይባልለታል። በተራ ጠብ ትግሬ የተባለ ከገላመጠው "ሥልጣን ይዘናል ብለህ ነው?'' የሚል ሆደባሻ ይበዛል። ከዚህ የባዮሎጂ መታወቂያ እያሳየ ወደ ደብረ ብርሀን ስትደርሱ የድል መኪናችሁ ላይ ከተሳፈረው መሀል ስንቱ የናንተን የታክቲክ ዲሲፕሊን እንደሚጠብቅላችሁ አላውቅም። እኔ እዚህ አውሮፓ ያጋጠመኝን ብታይ አቶ ሐጎስ አንተም ከሳሙኤልሰን ጋር "የናንተን ዓይነት ወዳጅ ያለው ጠላትም አያስፈልገው" ትላቸው ነበር። ለማንኛውም የTPLF ተቃዋሚ የደርግ ደጋፊ፤ የትግራይ ብሄረሰብ የበላይነት ተቃዋሚ የትግሬ ጠላት፤ በትግሬ የበላይነት ሥር የኢትዮጵያን "አንድነት" ለማረጋገጥ የሚደረግን ጥረት ተቃዋሚ የኢትዮጵያ ጠላት ይሆንና"ሁሉንም እንደአመጣጡ የመመለስ" ጀግንነት ይከተላል። ማለት የፈለግሁት ይገባሀል:: ምኞቴን ሳይሆን ፍርሀቴን ነው የማጫውትህ።

ከመኢሶን ከደርግ ጋር አብሮ መስራት የቀመስኩት ትምህርት፣ ካላሺን ሳይሆን ብእር ይዞ ከባለ ካላሺን ጋር መደራደር፣ ባዶ እጅ ሆኖ ሽጉጥ ከያዘ ጋር ካርታ እንደመጫወት እንደሚቆጠር ነው። መበላት ሲጀምር አፍሮ "እጅ ወደላይ" ሊል ስለሚችል እንኳን በሕጋዊ መንገድ የተጀመረውን ጨዋታ ለመቀጠል ቀርቶ "በቃ አልጫወትም" ለማለትም ዋስትና የለም።

መኢሶን ይህ አደጋ እንደነበረበት አስቀድሞም አውቆታል። ከላይ ባነሳሁት የውስጥ ጋዜጣ ብቻ ሳይሆን፣ እራሴ እንኳ በተለያዩ

የውይይት ክበቦች አደርጋቸው በነበሩ “ገለጣዎች” “በበኩሌ ደርግ በፈቃዱ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ሥልጣን ይለቃል የሚል እምነት የለኝም” ያላልኩበት ገለጣ አልነበረኝም:: መኢሶን ደርግ ሊያፍር እንደሚችል እያወቀ አብሮ የሰራው ከሚከተሉት ግምቶች በመነሳት ነው።

**አንደኛ:** መኢሶን እራሱ በጨዋታው ጊዜ እስከተቻለው ድረስ ተጠናክሮ ደርግ አፍሮ “እጅ ወደላይ” ሲል “አንተ እራስህ “እጅ ወደላይ” ለማለት የሚያስችለው ኃይል ባያገኝ እንኳ፣ ንቃትንና ድርጅትን በሚመለከት ሕብረተሰባዊውን መሰረት አመቻችቶ ደርግን ‘እጅ ወደላይ ብዬ የምገባበት አይኖረኝም” የሚያስብለው ሁኔታ ለመፍጠር ይቻል ይሆናል የሚል ግምት ነበር።

**ሁለተኛ:** መኢሶን ከደርግ ጋር ለመስራት በወሰነበት ጊዜ ይሁን አብሮ መስራት ባቋረጠበት ጊዜ በቀኝ በኩል በአሜሪካ የተደገፈ፣ እነ መሬት ላራሹን ዓይነት የአብዮቱን ድሎች የሚቀለብስ ፀረ አብዮት ይመጣል የሚል ግምት ስለነበረው መውደቁ ከማይቀር ደርግ ጋር ለጊዜው እየሰራ ለማይቀረው ከሶስቱ የኢትዮጵያ ሕዝብ ዋና ጠላቶች ጋር ለሚደረገው ረዥም ትግል መዘጋጀት ይገባል በሚል እምነት ጭምር ነበር።





ዛሬ ይህ “ትንተና” ስህተት መሆኑ ያኔ ከመኢሶን የታክቲክ መሰረቶች አንዱ እንደነበር አያስክድም። አሜሪካ በግራ ቀድሞን ከዓለም የመጨረሻዎቹ ግንባር ቀደም ኮሙኒስቶች ጋር እንደሚተባበር ማን ሊያስበው ይችል ነበር?! ሶሺየት ሕብረትስ የፀረ አሜሪካ ቱልቱላዎቹ አሳዳሪ መሆኑ ቀርቶና እራሱ ፈርሶ ወደአሜሪካ ቱልቱላነት እንደሚለወጥ ማን ሊያውቅ ይችል ነበር?!

የሆነው ሆኖ፣ መኢሶን ከደርግ ጋር ያደረገው ጊዜያዊ ትብብር፣ ሁለት የፖለቲካ ወገኖች ለተወሰነ ጊዜ ለተወሰነ የአጭር ጊዜ ዓላማ ሊያደርጉት የሚችሉት ትብብር ነው። መሬትን ላራሹ ያደረገው አዋጅ ተማሪ ንቅናቄ ውስጥ አንስተናቸው ከነበሩት የመሬት ስሪት ለውጦች ሁሉ የላቀ ስር ነቀል አዋጅ ነበር። የደርግ ብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ ፕሮግራም የመኢሶን መለስተኛ ፕሮግራም ግልባጭ ነው። በረቂቅነት የቀረው የዲሞክራሲያዊ መብቶች አዋጅም ዛሬም የቆምንለት የመብት ጉዳይ ነው። በተወሰነ ጊዜ ትብብር እነዚህን የተቻለውን ያህል በስራ ላይ ለማዋል መሞከር በራሱ ምንም ጥፋት አይደለም። ኋላ ቀር የፖለቲካ ባህል ጥቁርና ነጭን ብቻ ለመለየት የሚችል ያልነቃ ዓይን ብቻ ነው ጊዜያዊ ትብብርን ከዘለቄታ የዓላማ አንድነት ጋር የሚያምታታ።

ለማንኛውም የኢትዮጵያ አብዮት መኢሶን በገመተው መንገድ አልተራመደም። ታሪክ አስቀድሞ የተቆፈረለትን ቦይ የሚከተል የመስኖ ውሀ አይደለም፤ የራሱን አዲስ መንገድ እየቀደደ የሚሄድ ወንዝ ነው።

የውስጥና የውጭ ሁኔታዎች ከመኢሶን ቁጥጥር ውጭ በሆኑ ምክንያቶች ተለዋወጡ። መኢሶን ከደርግ የፖለቲካ ድርጊቶች ሊሸከማቸው ፈቃደኛ የሆኑት እንደመሬት ላራሹ ዓይነቶቹ ወደኋላ እየተገፉ፣ ከመኢሶን ዓላማ ጋር የሚቃረኑት እየጎሉ መጡ። (በረቂቅነት የቀረውን የዲሞክሪሲ መብቶች ጉዳይ እየገነነ የመጣውን የሰደድ ፈላጭ ቆራጭነት፣ የብሄረሰብ ጥያቄን… እንደምሳሌ መጥቀስ ይቻላል)። በዚህን ጊዜ መኢሶን የትግል ስልት ለውጥ አደረገ። የጉልበተኛ አገር እንደመሆኑ መኢሶን አብሬ አልሰራም ሲል ደርግም እንካ ቅመስ አለው። መኢሶን ሊመክተው የማይችለው የጭቆና በትር አረፈበትና ተመታ:: ከዚያም በኋላ ደርግ አስራ አራት ዓመታት ያህል በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ሊፈነጭ የቻለው መኢሶን "ስላጠናከረው ነው" የሚል ውንጀላም ሰምቻለሁ። አይጥ ከድመት የበለጠ አውሬ ያለ አይመስላትም ይባላል። በመኢሶን ጥላቻ ለተጋረደ ዓይን ብቻ ካልሆነ ደርግ ከተወለደ ጀምሮ የውስጥ መቆሚያው ካላሺን የውጭ ምርኩዙ ሶቭየት ሕብረት እንደነበረ ግልጽ ነው።

ያም ሆነ ይህ ብዕር ይዞ ካላሺን ከያዘ ጋር መተባበር ያዋጣል ወይ ከሚለው ጥያቄ ቀጥዬ የተቃዋሚ መብት ባልተረጋገጠበት ሁኔታ ከጉልበተኛ ጋር መስራት ምን ይዞ ጉዞ አይሆንም ወይ የሚለውን ነው የማነሳው። በደርግም ዘመን በናንተም አገዛዝ ሥር፤ ካላሺን ከአገር የውስጥ ፖለቲካ ይውጣ፤ የተሸናፊ መብት ዋስትና ባለው ሁኔታ ይረጋገጥ የሚለው ጥያቄ አብሮ መስራት ይገባል አይገባም የሚለውን





ጥያቄ መቅደም አለበት። ከመኢሶን ውድቀት የተማርኩት ሁለተኛው ሀቅ ይህ ነው።

## 4.2 ስለ "ቀይ ሽብር" ጉዳይ በአጭሩ

በኤርትራና በሰሜን ኢትዮጵያ የተካሄደው ለብዙ መቶ ሺህ ሕዝብ እልቂትና ለሚሊዮኖች ስደትና ስቃይ ምክንያት የሆነው የረዥም ዓመታት ጦርነት በተለይ የአዲስ አበባን ከተሜ በቀጥታ አልነካም። በሁለት የታጠቁ ወገኖች መካከል የሚካሄድ ጦርነት ውጤት ስለሆነ፣ ምናልባትም የመገንጠልና የብሄር ነፃ አውጭ ንቅናቄዎች ከየብሄረሰባቸው አባሎች ውጭ ብዙም አዘኔታ ስላላተረፉ፣ ይህ አስከፊ ጦርነት የፈጠረው ምሬትና ያስከተለው ተቃውሞ ከጦርነቱ መጠንና እርዝማኔ ጋር ሲተያይ በጣም አነስተኛ ነበር ማለት ይቻላል። ከዚህ የረዥም ጊዜ እልቂት የበለጠ በ1969 ተጀምሮ በ1970 የተባባሰው በተለይ የአዲስ አበባው ቀይ ሽብር በአሰቃቂነቱ የበለጠ ነው የተወራለት፤ ያሳደረውም ምሬት በጣም ከፍ ያለ ነው። "ከጦር ሜዳ ውጭ" መካሄዱ፣ የሚዘገንኑ አፈፃፀሞቹ፣ የፖለቲካ ተሰሚነቱ የሚያይለውን የከተማ ኗሪ ይበልጥ መንካቱ ይሆናል:: የ1970ው ሽብር እስር ቤት ሆነን ነው የተካሄደው። ወላፈኑ እዚያ ድረስ ያቃጥል ነበር። ጠባቂ ወታደሮች ሳይቀሩ እናንተ በመታሰራችሁ ታድላናል በሉ አዲስ አበባ ወጥቶ ለመግባቱ እርግጠኛ የሆነ ወጣት አይኖርም ይሉን ነበር።

ኢትዮጵያ ውስጥ በተለይ አዲስ አበባ የዚህ የሚዘገንን ዘመን ታሪክ እየተጎለጎለ ነው አሉ። እናንተ እንኳ የዚያን ዘመን ጥላቻ ለአሁኑ ዘመን ፍቅር ያስገኝ እንደሁ ብላችሁ ነው፤ ደርግ በወሎ የረሀብ ፊልም ሊጠቀም እንደሞከረው። ቤተሰቦች እንደአዲስ መርዶ እየተቀመጡ ነው ሲባል እሰማለሁ። የፖለቲከኛው ክፍል "ጥፋተኛ" የሚለው ማንን እንደሆነ፣ ውንጀላዎች ሲደረጉ የመረጃዎች ጉዳይ እንዴት እንደሆነ አላውቅም። እናንተ ቀይ ሽብርን የመኢሶን ሥራ አድርጋችሁ ለማቅረብ ሳትሞክሩ አትቀሩም።

መጀመሪያ ነገር ቀይ ሽብርን በሁለት ወቅቶች ከፍሎ ማየት ያስፈልጋል። በ1969 በኢሕአፓ የተካሄደው ሽብር፣ የደርግ ዘመቻ መምሪያ (በተለይ መንግስቱ እነዓለማየሁ ኃይሌን ካሸነፈ በኋላ) ይህቺማ የምናውቅብሽ ብሎ የሰጠው አፀፋና የተመረጡ ቀበሌዎችና መኢሶን እስከተወሰነ ደረጃ እራሳቸውን ለመከላከል የተሳተፉበት "ቀይ ሽብር" አለ። በ1970 (እኛ እስር ቤት እያለን) የተካሄደው "ዋነኛ ቀይ ሽብር" ደግሞ አለ። ይህ "ቀይ ሽብር" በሰደድ የተመራ የነለገሠ አስፋውና የነ ሻለቃ ብርሀኑ ታማኝ የነበሩ ቀበሌዎች በግንባር ቀደምትነት የተሳተፉበት፣ በኢሕአፓ የርስበርስ ጦርነት (አንጃና ቦልሸቪኮች መሀል) ታግዞ በኢሕአፓና በመኢሶን ላይ የተካሄደው ሽብር ነበር። (ከጳጉሜ 1969 በኋላ እስር ቤት ሆኜ ከነ ተኮላ እኩል ሲገርፉና ሲገድሉ የነበሩ የቀድሞ ኢህአፓ አባሎች እንደነበሩ በዓይኔ ያየሁት ነው)።





መኢሶን የፖለቲካ ተጠያቂነት ካለበት በ1969 ውስጥ ለተካሄደው "መለስተኛ ቀይ ሽብር" ነው። ይህንንም ስል ከዛሬ አቋሜ አንጻር ሳየው መኢሶንም በፖለቲካ እምነት ምክንያት መጋደልን ላስቻለ የፖለቲካ ሂደት የራሱ አስተዋጽኦ አለው ከሚለው ተነስቼ እንጂ፣ መኢሶን የጀመረው ሽብር ነው ለማለት አይደለም። ያኔም ዛሬም ያለአንዳች ማመንታት የመጀመሪያውን ጥይት የተኮሰ ብቻ ሳይሆን ሁኔታውን ወደዚያ የገፋፋው ኢሕአፓ ነበር እላለሁ። ገና በተማሪ ዘመቻ ጊዜ የተቋቋሙት "ፊዲስቶችን የሚያጠቁ ጠራቢ ቡድኖች' ባንዳ ሁሉ፣ ትግል በብዕር ብቻ መሰሎሀል" የሚለው ዛቻ፣ ከዚያም በከተሞች ግድያ ለማካሄድ የተደረገው ድርጅታዊና ትጥቃዊ ዝግጅት የሚያሳዩት ይህንኑ ነው። ፊሳ መቁጠር ከተጀመረም በኢሕአፓ ነፍሰ ገዳዮች እጅ የተገደሉት የመኢሶን አባሎችና ደጋፊዎች በጣም ብዙ ናቸው።

እስቲ ከመኢሶንና ከኢህአፓ የትኛው የተሻለ ሰብአዊ ነበር፣ የትኛው አብዮታዊ ነበር ወዘተ ከሚሉ ጥያቄዎች የሚነሱና በፍቅርና በጥላቻ ላይ ሊመሰረቱ የሚችሉ ፍርዶችን እንተውና የሽብሩን ጉዳይ ከያኔው የፖለቲካ ጥቅሙ አንፃር እንየው።

መኢሶን በዚያን ወቅት ቅድሚያ የሰጠው ዓላማ ሕዝብ ውስጥ መግባትና ቅቡልነት ማግኘት የሚል ነበር። ይህን ዓላማ በተግባር ለመተርጎም (ከፈለግህ ያንተኑ ቃላት ልጠቀምና) የደርግን እንቅፋትነት "በቤተ መንግስት ሽኩቻ" የኢሕአፓን እንቅፋትነት ደግሞ በብዕር ለማስወገድ

ነበር። የቤተ መንግስቱን በውስጥ ጋዜጣና መኢሶን አመራር ውስጥ የነበሩ ጓደኞቼ ከሚያወሩኝ እንጂ በቀጥታ አልተሰተፍኩበትም። ለምሳሌ ያህል መኢሶን እነመንግስቱና እነዓለማየሁ ኃይሌ ሲፋጠጡ፣ ሁለቱም ወገኖች እንዳይማቱ ለማድረግ የተቻለውን ያህል ይሞክር እንደነበረ አውቃለሁ። "መንግስቱ የኛ ሰው እንዳልሆነ አሳውቀን እነዓለማየሁ ኃይሌን ማረጋጋት" የሚል አቋም ተከትሎ ነበር የመኢሶን አመራር። (በዚህ ወቅት የወጣውን "ውጋጋን" የሚለውን የመኢሶን የውስጥ ወረቀት ከመዛግብትህ አውጥተህ ልታይ ትችላለህ አቶ ሐጎስ)። ዓለማየሁም ሆነ መንግስቱ ለቁርስ ይሁን ለምሳ የሚለው ላይ እንጂ መኢሶንን "ለመብላት" እንዳቀዱ አውቀነው ነበር። አንዱም እንዳይበላን ሁለቱም በተቻለ እንዳይባሉ ለማድረግ መሞከርን ነበር የመረጥነው፤ የእራት ሰዓት እስኪደርስ። ያኔ ሕዝቡን የሙጥኝ ብለን እንተርፋለን የሚል እምነት ነበር።

ወደ ኢሕአፓ እንመለስና እራሴም የማውቀው ነገር ስለሆነ ትንሽ ላጫውትህ። ዲሞክራሲን በሚመለከት የተሸናፊን ሙብት ማስጠበቅ በሚለው መልኩ ምን ያህል ገብቶን እንደነበረ እኔ እንጃ። በዚያን ጊዜ ስለዲሞክራሲ የጻፍኳቸውን ዛሬም "ሳላፍር" ላወጣቸው እችላለሁ። ቢያንስ ቢያንስ በዲሞክራሲያዊ መንገድ ለማሸነፍ እርግጠኛ የሆነ ድርጅት ሊሆነው የሚችለውን ያህል ዲሞክራት እንደነበርን አልጠራጠርም። በበኩሌ ለዚህ እርግጠኛነቴ መሰረቱ ለኢትዮጵያ ሕዝብ በሚኖር ፍቅር የሚበልጠንና በብዕር "ጦርነት" የሚስተካከለን የለም የሚለው እምነት ነበር። የሕዝብ ፍቅር ስለሚለው እንግዲህ ያለ ካላሺን ማስመስከር



ታዝቤ ዝም ከምል

የማይቻልበት አገር ሆነና፤ እኔ እሱም መልሶ ሊወደን ጀምሮ ነበር ስል አንተ ጭራሽ አርዳችሁታል ትለን ገባህ።

የብዕሩ ነገር ግን ዛሬም ያልለቀቀኝ "ጉረኝነት" ነው። ይኸው አንተንስ "ይዋጣልን" እያልኩህ አይደል? ኢሕአፓን በብዕር እንደምናሸንፍ እርግጠኛ ከመሆኔ የተነሳ እነ ኃይሌን ኢሕአፓን ለኛ ተውና እናንተ ሌላ ስራ ስሩ ለማለት ትንሽ ነበር የሚቀረኝ። የአምስት አመት የተማሪ ንቅናቄ ኢሕአፓ ቀላል የብዕር ባላጋራ እንደሆነ አሳምኖኛ ነው። በርሊን ስኖር መካከለኛ ብቻ ሳይሆን አመራር ድረስ ያሉ የኢሕአፓ ሰዎች በግል ለማስተናገድ ጭምር አጋጣሚዎች ነበሩኝ። ከማርክስ እስከማኦ ባለው ትምህርት ቤት ስንተኛ ክፍል ሊመደቡ እንደሚችሉና ምን ያህል እንደገባቸው ለመገመት አስችሎኛል፤ የሚጽፉትንማ ተወው። አንዳንድ ዲሞክራሲያ በጣም ቆንጆ በሆነ አማርኛ ከመጻፉ በቀር እንመላኩ[22] የሚቸከችኩት ስህተተኛ የፖለቲካ መስመር የሚያንፀባርቅ ብቻ ሳይሆን፣ ከተራ ሎጂክ፣ ከተራ የቋንቋ ሕግጋት ጋር የተጣላ ትርኪ ምርኪ ነበር።

ያም ሆነ ይህ "ሌኒን ስብስብስ ሥራዎች ቅጽ 13' በሚመዘዝበት የብዕር ጦርነት ኢሕአፓን እንደምናሸንፍ እርግጠኞች ነበርን። ዛሬም እንደያኔ ደርግ አብረን መስራት ከጀመርን ከአመት በኋላ መኢሶን በሕዝቡ ዘንድ "ቅቡልነት" እያገኘ መምጣቱ ስላላማረው ሊመታን እንደወሰነ ሁሉ፤ ኢሕአፓም በ1969 መጀመሪያ ላይ በንዳ ሁሉ "ትግል በብዕር ብቻ

22. መላኩ ተገኝ - "ከሰንጋ ተራ እስከ አምስተርዳም" የሚል መጽሐፍ የደረሰና በአውሮፓ ተማሪዎች ማኅበር ውስጥ ይሳተፉ ከነበሩ የኢህአፓ መሪዎች መሃል አንዱ ነበር።

መስሎሀል” ብሎ መኢሶኖችን መግደል የጀመረው በብዕሩ ጦርነት ብዙም እድል እንዳልነበረው ስላየ ነው ባይ ነኝ። አዲሱ ኢሕአፓ የከፈተብን ጦርነት ግን የማናውቀውና ያልተዘጋጀንለት ጦርነት ነበር። ለዚህ ነው ፍቅሬ መርዕድ ሲገደል፣ በግል የምናውቀውን ከማሳዘን አልፎ በጠቅላላው በመኢሶን ውስጥ ድንጋጤንና በተጀመረው ሰላማዊ መንገድ ሶሻሊዝምን ለማስፋት የነበረውን ምቹ ሁኔታ በማደፍረሱ ብሽቀትን ያሰፈነው።

ኢሕአፓ መንግስቱ ኃይለማርያምን ለመግደል ካደረገው ሙከራ በኋላ የግድያው ዒላማ መኢሶን ብቻ ነበር። እዚህ ላይ በግልጽ ከደርግ ጋር የምንሰራው እኛ ብንሆንም ኢሕአፓ ይህን ሽብር በሚያካሄድበት ጊዜ፣ በደርግ መዋቅር ውስጥ ከኛ የበለጠ ተሰሚነት እንደነበረው መረዳት ያስፈልጋል። መኢሶን የራሱ አባሎች እየተገደሉበት፣ በርሱ አበረታችነት የተመረጡ “አገርና አብዮት ወዳድ” የቀበሌ ተመራጮች እየተገደሉ በሕጋዊ መድረክ ላይ ተጋልጠው የሚሰሩ አባሎቹንና ደጋፊዎቹን ከኢሕአፓ ግድያ የሚከላከልበት የራሱ የትጥቅ ሆነ የድርጅት ጥንካሬ አልነበረውም። ስለዚህም የግዱን እራሱ የማያዛቸውን የደርግ የመጨቆኛ መሳሪያዎች ተገን ማድረግ ነበረበት። በነርሱ በመጠቀም እራሱን ለመከላከል ሞክሯል። ግን ደግሞ እዚህ ላይ በማተኩርበት የ1969 መኢሶንና ኢህአፓን የሚመለከት “ነጭና ቀይ ሽብር” አብዛኛው ፍጅት ኢሕአፓ ወጣቱን አስገድሎ የደርግን ፋሺስታዊነት ማረጋገጫ ሊያስደርገው የፈለገ በሚያስመስለው ሁኔታ ከደርግ ቋሚ ተጠሪዎች ጋር እያጋፈጠ የደረሰው ፍጅት ነው። ለነዚህም





ወንጀሎች መኢሶን ተጠያቂ ሊደረግ ነው? በበኩሌ ኢሕአፓ በመኢሶን ላይ ላካሄደው “ነጭ ሽብር” ብቻ ሳይሆን ለዚህ ሀላፊነት ለጎደለውና ወጣቱን ላስመታ የትግል ዘዴም ጭምር ተጠያቂ ነው እላለሁ።

በዚህ ወቅት ለተካሄደው ሽብር ለመኢሶን የድርሻውን የፖለቲካ ሀላፊነት ለመስጠት አላመነታም። መመለስ የማልችለው ምን ምርጫ ነበረው የሚለውን ጥያቄ ነው። እስር ቤት ሆነን ኃይሌ አንድ ቀን ኢሕአፓ በ1968 መጨረሻ ግድም አቅርቦ ስለነበረው የግንባር ጥሪውና እኔው ለዚሁ ጽፌያት ስለነበረው መልስ አንስተን ስናወራ “እንደዚያ መቀለጃ ከማድረግ ጥሪውን ተቀብለናል ብለን ለመደራደር ብንሞክር ይሻል ነበር ይሆናል” ብሎኝ ነበር። በነበረው መካረርና በኢሕአፓ ግትርነት ይህ ድርድር ምን ውጤት ያመጣ እንደነበር አላውቅም። ደግሞም ኢትዮጵያ ውስጥ ካላሺን የያዘና “በራሱ የሚተማመን” የፖለቲካ ድርጅት እንደራደር ሲል “እጅህን ስጥ” ነው የሚል። ኢሕአፓም ኢሕአሠን አለኝ ባይ ነበር።

ለማንኛውም መኢሶን ተገዶ የገባበት ማጥ መሆኑን ባውቅም ከዛሬው አቋሜ ተነስቼ ሳየው “ነጭ ሽብርን በቀይ ሽብር” የሚል (ከማርክስ የተወሰደ) “አብዮታዊ መፍትሄ” ማንሳቱ ስህተት ነበር እላለሁ። አብዛኛው የቢሮክራሲ መዋቅር የኢሕአፓ ድጋፍ ሰጭ ስለነበረ ተፈፃሚነቱ ምን ያህል ይሆን እንደነበር ባላውቅም፣ “ነፍሰ ገዳዮች ለሕግ ይቅረቡ” በሚል ሕጋዊ መድረክን ባልለቀቀ መንገድ የኢሕአፓን ሽብር ለመቋቋም መሞከሩ ይሻለን ነበር። ዛሬ ይህን አብዮታዊ

መፍትሄ ስህተት ነው ስል ይህን ያህልም ለ1970ው ፍጅት መንገድ ከፈተ በሚል አይደለም። ጅብ ሁሌ ውሻ በከፈተው ቀዳዳ መግባት የለበትም። ደርግን የመሰለ ጅብም ሰው ለመብላት የመኢሶንን ርእዩተ ዓለማዊ ድጋፍ አይጠብቅም። ከመኢሶን ጋር ከመስራቱ በፊትም ሆነ በኋላ ፋሺስትነቱን አረጋግጦ የሚጎዳውን ጎድቷል። እኛ ለሕዝብ የሚጠቅሙ እርምጃዎቹን ለመጠቀም የሞከርነውን ያህል ፋሺስታዊ እርምጃዎቹም ተጠቃሚ አላጡም።

በኔ ግምት የፈለገው ገለልተኛ አጣሪ ቡድን "ቀይ ሽብርን" ቢመረምር፣ መኢሶን በአመዛኝ ሽብር የተካሄደበት እንጂ ሽብር ያካሄደ ድርጅት እንዳልሆነ ሊመሰክር የሚችል ይመስለኛል። ስለዚህም ለተጨባጭ ወንጀል ተጠያቂ መሆንና ለስህተተኛ መፈክር የፖለቲካ ሀላፊነት መውሰድ ይለያያሉ። መኢሶን ለዚህ መፈክር የፖለቲካ ሀላፊነት መውሰድ አለበት ስል፣ ቢቀር ቢቀር የራሱን የፖለቲካ አመራርና ዲሲፕሊን ሊሰጠው ለማይችለው መፈክር ጥሪ በማድረጉ፣ በተለይም ሰብዓዊ ሕይወትና የሕግ ልዕልና ክብር አግኝተው በማያውቁበት አገር ይህን ለዘፈቀደ አገዛዝ የሚያመች ወንጀለኛ መፈክር በማንሳቱ ነው። በግሌ ዛሬ ሳትባንን ተኛ ሲለኝ በኢትዮጵያ አብዮት ውስጥ እንኳን ልገድልና ላስገድል የገላመጥኩት ባይኖረኝም፣ የጊዜውን መንፈስ ተከትለው እሳት ይተፉ ለነበሩ "አብዮታዊ" ጽሁፎቼ ተጠያቂነቴን፣ ጀግና ባልጠፋበት አገር ለፈሪነት፣ አብዮታዊው በበዛበት ሁኔታ ለሕጋዊነት ባለመቆሜ ስህተተኛነቴን እቀበላለሁ።





የሰው ህይወት ተሰስቼ ከጄ ወድቆ ተሰበረ የሚባል ብርጭቆ አይደለም። ስለዚህም የምመኘው ነገር ቢኖር፣ መኢሶንና ኢሕአፓ ለዚህ እልቂት ታሪካዊ መነሾና ፖለቲካዊ ምክንያት በየፊናቸው ስለአደረጉት አስተዋጽኦ ከእንግዲህ እንደዚህ ዓይነትን እልቂት ላለማስቻል በተፈጠረ ቁርጠኝነት ቢወያዩና ከዚያም ከሁለቱ የተውጣጣና ከሁለቱም ያልሆኑ በገለልተኛነታቸው የታወቁ ሰዎችን የጨመረ ኮሚቴ ተቋቁሞ ብዙውን ነገር ቢያጣራ ነው። ለንግስት አዳነ እኛ፣ ለዮሴፍ አዳነ[23] ኢሕአፓዎች የሚያለቅሱበት ሁኔታ አልፎ ለሁለቱም ሁላችንም የምናዝንበት ሁኔታ እንዲፈጠር ነው። የዛሬ ፍርደ ገምድል አሸናፊዎች ለፖለቲካ ግባቸው ሲሉ ስለቀይ ሽብር የሚያደርጉት ውጣ ውረድ የታሪክ ስህተቶችን ለመመርመር፣ በፖለቲካ ትግል ውስጥ የተፈጸሙ ወንጀሎችን ለማጣራት አያስችልም። ይህ የታሪክ ፍትህ ፍለጋ ሳይሆን፣ ሌላውን በቂም በቀል ዳግማዊ ፍጅት እንዲያካሄድ ጋብዞ በግርግሩ ለመደላደል የሚሞክር የአድዋ ጮሌነት ነው።

መኢሶንና ኢሕአፓ የኢትዮጵያን የፖለቲካ አቅጣጫ ለመወሰን ከእንግዲህ "ግንባር ቀደም ታሪካዊ ሚና" አይኖራቸው ይሆናል። አገራችን ካለችበት አዘቅት እንድትወጣ ሊያደርጉት ከሚችሉት የፖለቲካ አስተዋጽኦ ዋነኛው ሁለቱም ከውድቀታቸው የቀሰሙትን ትምህርት ለተከታዩ ትውልድ ማስተላለፍ መሆን ይኖርበታል። ኢህአፓና መኢሶን

23. ንግሥት አዳነ (ዶ/ር) እና ዮሴፍ አዳነ ሁለቱም በደርግ የተገደሉ እህትና ወንድም ሲሆኑ፣ ንግሥት የመኢሶን ዮሴፍ ደግሞ የኢህአፓ አመራር አባሎች ነበሩ።ከሁለቱ ሌላም ቢንያም አዳነም በኢህአፓ አባልነት እነ ብርሃነ መስቀል ረዳ ጋር ለትጥቅ ትግል ሜዳ ገብቶ የሞተ ሌላ ወንድማቸው ነው።

ኢዴፓቅ ውስጥ መተባበር መጀመራቸውን ስሰማ ደስ ያለኝ ይህን ያህልም ከTPLF ጋር በጋራ ለመታገል ስለሚያስችላቸው አይደለም። ይህን አሳዛኝ የኛን ትውልድ የታሪክ ምዕራፍ ምናልባት አብሮ ለመገምገም ይበቃሉ የሚል ተስፋ ነው። ከTPLF ጋር በሚያደርጉት ትግል ተቃዋሚነታቸውን ከመደገፍ አልቆጠብም፤ አቋማቸውን ሁሌ ለመደገፍ አንዳንዴ ሆዴን የሚያሳምሙኝ ቅመሞች አሉበት። አዲሱ ትውልድ እኛ ባለፍንበት መንገድ እንዳያልፍ የተቻለውን ያህል ለመጣር እስከሞከሩ ድረስ ግን በሙሉ ልቤ አብሬአቸው ነኝ። እኔም የሚደርስብኝን ''ወርተራ" ገብቼ ዘብ ለመቆም ዝግጁ ነኝ።

ምናልባት ለዛሬ የፖለቲካ "ጴንጤነቴ" አስተዋጽኦ ካደረጉት ምክንያቶች አንዱ ደርግ ጽህፈት ቤት ታስረን በመጀመሪያዎቹ ሳምንት ውስጥ ያጋጠመኝ የሚከተለው ሁኔታ ነበር። እኛ ፋሲካ ሊደርስ ሲል ተገዝቶ እርዱን እንደሚጠባበቅ በግ የመገደያችንን ቀን ስንጠብቅበት የነበረው እስር ቤት ውስጥ በየቀኑ ከተለያዩ እስር ቤቶች ተለቅመው ማታ ማታ የሚገደሉ እስረኞች የሚታጎሩበት አንድ ክፍል አለ። ብዙውን ጊዜ ድምጽ መስማት እንጂ ውስጡ ማን እንዳለ ማየት አንችልም:: አንዱን ከሰዓት በኋላ የዚህን ክፍል ቁልፍ የያዘው ወታደር ባለመኖሩ ነው መሰለኝ፤ ሁለት ከፖሊስ ጣቢያ ያመጧቸውን እስረኞች ውጭ ልናያቸው የምንችል ቦታ አስቀመጧቸው። ሁለቱንም አውቃቸው ነበር። ደሳለኝና አክሊሉ ይባላሉ። ደሳለኝ እርሱ የዩኒቨርሲቲ እኔ ሚኒሊክ ተማሪ ሆነን የመጀመሪያውን ማርክሳዊ ጽሁፍ ያስነበበኝ፣ እንደነገሩ የመጀመሪያዋ "ሕዋስ' ውስጥ ያደራጀኝ ሰው ነበር። አክሊሉን ደግሞ





ስዊዘርላንድ ሲማር ነው የማውቀው። እርሱ የኢሕአፓ እኔ የመኢሶን አባል ሆነን በአውሮፓ የተማሪዎች ማህበር ውስጥ ተሳትፈናል። ሁለቱም ማታ እንደሚገደሉ አውቀውታል። ከሰዓት በኋላ በአስር ሰዓት እስረኛ ለምን እንደሚወሰድ የታወቀ ነበር። መነጋገርም ብንችል ኖሮ ለመወቃቀስ ይቅርና ሰላምታ ለመለዋወጥም የሚቻልበት ሁኔታ አልነበረም። ከጥቂት ሰዓታት በኋላ ወደሞት የሚሄድን "እንደምነህ" ቢሉት ምን ዋጋ አለው? ላይኛው ቤት ቀጠሮ ወስዶን አንቀጥለው ነገር። "ክርክርስ" ቢጀመር ምን ሊጠቅም። "ወንድም ሲጃራ አለህ?" ብቻን ነበር ከአክሊሉ የሰማሁት። የጋራ አራጅ እጅ ልንወድቅ ነው እንደዚያ ስንራገጥ የከረምን? የሚል ቁጭት እያበገነኝ ያለችኝን ሲጃራ ለወታደሩ ሰጥቸለት ከእንባ ጋር እየተናነቅሁ ወደሞት መጠባበቂያ ክፍሌ ውስጥ ገባሁ።

በል እንግዲህ አቶ ሐጎስ አሁን መጨረሴ ነው። አንተን እየረሳሁ በፖለቲካና በእንጀራ ምክንያት ባንድ አገር ለመኖር ያልቻልን ወዳጆቼን እያስታወስኩ ስለፃፍኩት ረዘመብኝ። ካንተ ስሰናበት ከነዚህ ወዳጆቼም ልሰናበትና ምናልባት ይህቺን ጽሁፍ ሲያነቡ በኢትዮጵያ የዛሬ የፖለቲካ ካርታ ውስጥ የት እንደሚመድቡኝ እንዳይቸገሩ ስላለሁበት ቦታ ትንሽ ልንገራቸው።

## 5. መደምደሚያ

